# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 012 መስከረም 12 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




# ለጎርፍ ተጋላጭ የነበረው አካባቢ በጥጥ እርሻ እያጌጠ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአንድ ወቅት በጎርፍ የመጥለቅለቅ አደጋ ተጋላጭ የነበረው የአፋር ክልል የመካከለኛው አዋሽ አካባቢ፣ በ20 ሺህ ሄክታር ላይ በጥጥ እርሻ ማጌጡ አዲስ ነገር ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ እንዳሰፈሩት ፤በዙሪያችን ያለውን እምቅ አቅም መለየት ወሳኙ ዕውቀት ነው ፡፡ አካባቢው ፍራፍሬን

ለጎርፍ ተጋላጭ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት




አምባሳደር ዘነበ ከበደ

# ኢትዮጵያ የተመድ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን "ሪፖርት"ን እንደማትቀበለው አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ያወጣውን "ሪፖርት" ኢትዮጵያ እንደማትቀበለው በጄኔቭ የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ዘነበ ከበደ አስታወቁ።

ሪፖርቱን በተመለከተ ለፈረንሳዩ የዜና ወኪል አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ የተናገሩት በጄኔቭ የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ዘነበ ከበደ፣ "ሪፖርቱ"ን ያወጣው ኮሚሽን መንግሥት ርሃብን በጦር መሳሪያነት ስለመጠቀሙ አንድም ማስረጃ አላቀረበም ብለዋል።

አምባሳደር ዘነበ በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ በኢትዮጵያ ስለተፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት በተመለከተ ኮሚሽኑ ያወጣው "ሪፖርት"

ኢትዮጵያ የተመድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- አሸናፊ ጉዴታ

# የኮሚሽኑ "ሪፖርት" የፖለቲካ ፍላጎትን ለማስፈጸም የተዘጋጀ በመሆኑ መንግሥት አልተቀበለውም

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የተመድ የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት ያቋቋመውን የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን "ሪፖርት" ለሰብዓዊ መብት ከመቆርቆር ሳይሆን የፖለቲካ አጀንዳ ያነገበና የፖለቲካ ፍላጎትን ለማስፈፀም የተዘጋጀ በመሆኑ መንግሥት እንደማይቀበለው ተገለጸ።

የወንጀል ተጠያቂነትን ለማስፈን በፍትህ ሚኒስቴርና በፌዴራል ፖሊስ የተቋቋመው የሚኒስትሮች ግብረኃይል በትናንትናው ዕለት መግለጫ ሲሰጥ የግብረ ኃይሉ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ዶክተር ታደሰ ካሳ እንዳስታወቁት፣ በያዝነው ሳምንት መባቻ ላይ የወጣው የተመድ የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት ያቋቋመው የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን "ሪፖርት" ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር የተደረገ ሳይሆን የፖለቲካ አጀንዳ ያነገበና የፖለቲካ ፍላጎትን ለማስፈፀም የተዘጋጀ በመሆኑ መንግሥት አይቀበለውም።

የኢትዮጵያ መንግስትም ኮሚሽኑ ከመቋቋሙ ጀምሮ ሲቃወም መቆየቱን ያነሱት ዶክተር ታደሰ፤ "ሪፖርቱ" የድርጅቱ የአሠራር ቅደም ተከተልና ሥርዓት ካለመከተሉ አንስቶ ችግር ያለበት እና መደምደሚያውም በዚያው ልክ የተሳሳተ እንደሆነ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ታደሰ ገለፃ፣ "ሪፖርቱ" ከሦስቱም ክልሎች ቁንፅል በሆነ ሥፍራ ላይ ያነጣጠረ እና ስለ ሂደቶችም ቁንፅል መረጃ ያለው ነው። ኮሚሽኑ ሥራዎቹን

የኮሚሽኑ "ሪፖርት" ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- በሃዱሽ አብርሃ

# ኮሚሽኑ ይፋ ያደረገው የሐሰት ድርሰት አሸባሪውን ቡድን ማዳንም ሆነ የጎደፈ ስሙን ማደስ አያስችልም

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ላይ ተመስርቶ ያወጣው "ሪፖርት" የሐሰት ድርሰት በመሆኑ አሸባሪውን ቡድን ሊያድንበትም ሆነ የጎደፈ ስሙን ሊያድስበት እንደማያስችለው በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ ገለጹ፡፡

አቶ እንዳለ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ በአሁኑ ሰዓት ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በኢትዮጵያ ላይ አካሂጃለሁ ብሎ ይፋ ባደረገው ሪፖርት ተስፋ ባለመቁረጡ ነው እንጂ የአሸባሪውን ሕወሓት ቡድን ማዳን አይቻለውም፡፡ የጎደፈ ስሙንም በሪፖርቱ ማቃናት አይቻለውም፡፡ ኮሚሽኑ ይፋ ያደረገው "ሪፖርት" ልክ እንደ አሸባሪው ሕወሓት ሁሉ በኢትዮጵያ

ኮሚሽኑ ይፋ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


# የአውሮፓ ሕብረት የፓርላማ አባላት ከለውጡ ወዲህ በኢትዮጵያ ያለውን ለውጥ አደነቁ

- ኢትዮጵያ ምንጊዜም ለሰላም ዝግጁ መሆኗን አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ ተናግረዋል

ገጽ 3

# ኢሬቻን ያለምንም የጸጥታ ችግር ለማክበር በቂ ዝግጅት ተደርጓል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የሆራ ሀርሰዴ የኢሬቻ በዓልን ያለምንም የጸጥታ ችግር በደማቅ ሁኔታ ለማክበር በቂ ዝግጅት መደረጉን የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የቢሾፍቱ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ አብዱልሰላም መሐመድ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በዓሉን ለማክበር ወደ ከተማው የሚመጡ እንግዶችን በጥሩ መስተንግዶ ለመቀበል በቂ ዝግጅት ተደርጓል። ከበዓሉ ጋር ተያይዞም በሁሉም አገልግሎቶች የሚደረግ የዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር ከከተማው ነዋሪዎች ጋር መተማመን ላይ ተደርሷል።

ለእንግዶች በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት ከመስጠት ጎን ለጎን ወደ ከተማው ለሚገቡ የበዓሉ ታዳሚዎች ምግብና ውሃ በነጻ ለማቅረብ የከተማው ነዋሪዎች እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን የተናገሩት አቶ አብዱልሰላም፣ በተጨማሪም ሕብረተሰቡን በማስተባበር ከተማውን ውብና ጽዱ የማድረግ ሥራ በስፋት እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

እሬቻ ከቂም በቀል በጸዳ መልኩ በፍቅርና በአንድነት ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት ክብረ በዓል ነው ያሉት ምክትል ከንቲባው፣ ከዚህ አንጻር ታዳሚው በሰላምና በፍቅር ፈጣሪውን ለማመስገን መቅረብ እንደሚጠበቅበትና የፎሌና የጸጥታ አካላት በቂ ዝግጅት እንዳለ ሆኖ ሕዝቡም ሰላሙን ለማስጠበቅ የተለመደውን ትብብር እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

በጸጥታ አከባበር ዙሪያ የአካባቢው ሕብረተሰብ በቂ ልምድ መኖሩን የገለጹት ምክትል ከንቲባው፣ ሕብረተሰቡን ለማገዝም የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንደሚሰራም አመልክተዋል።



በተመሳሳይ መልኩ ከኦሮሚያ ጤና ቢሮ ጋር በመሆን በቀኑ ነጻ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት 50 የሚሆኑ ድንኳን በየቦታው እንደሚተከልና 25 አምቡላንሶች እንደሚሰሩ የገለጹት አቶ አብዱልሰላም፣ ከግልና ከመንግሥት የጤና ተቋማት የተውጣጡ የጤና ባለሙያዎች አገልግሎት እንደሚሰጡም ጠቅሰዋል።

ኢሬቻ ከባህላዊ ጠቀሜታ ባሻገር የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ በዓለም ለማስተዋወቅ ትልቅ ድርሻ አለው ያሉት ምክትል ከንቲባው፣ ሕዝቡን ለማቀራረብ ካለው ማሕበራዊ ፋይዳው በተጨማሪ ትልቅ ገቢ በማመንጨት ከተማውንና አገርን የማሳደግ ሚናውን በአግባቡ እየተወጣ ይገኛል ብለዋል።



# በ2014 በማዕድን ዘርፍ ከግማሽ ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ ከቀረቡ የወርቅ፣ የጌጣጌጥና የኢንዱስትሪ ማዕድናት ከ543 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ መገኘቱን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ሚኒስቴሩ የ2014 በጀት ዓመት ማጠቃለያ ሪፖርቱን እና የ2015 እቅዱን አስመልክቶ በድረገፁ ላይ ባሰፈረው መረጃ እንደጠቀሰው፣ በ2014 በጀት ዓመት አስራ አንድ ወራት በባህላዊ አምራቾችና በኩባንያዎች 8,073.05 ኪ.ግ ወርቅ፣ 102.1 ቶን ታንታለም፣ 12,657.92 ኪ.ግ ጥሬና 148.69 ኪ.ግ እሴት የተጨመረበት ኦፓል፣ 3,174.02 ኪ.ግ የጌጣጌጥ ማዕድናት፣ 13,838.71 ቶን አዳዲስ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ወደ ገበያ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች የአቅም ውስንነት፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የፀጥታ ችግሮች መከሰት፣ በክልሎች የዘርፉ አደረጃጀት ወጥነት የሌለውና የተሟላ አለመሆን ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች እንደነበሩም አስቀምጧል፡፡

የክፍለ ኢኮኖሚው አቅም በመገንባት ተቋማዊ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ ከክልሎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትብብርና ትስስር ማጠናከር፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ያሉትን የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ምርትና ምርታማነት ማጎልበት፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ማዕድናትን በዓይነትና በመጠን ማሳደግ በቀጣይ በልዩ ትኩረት የሚሰራባቸው ጉዳዮች መሆናውንም ሚኒስቴሩ አስታውቋል፡፡

ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ማዕድናት በአገር ውስጥ መተካት፣ የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንቶች የአካባቢና ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ያረጋገጡ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በዘርፉ አቅምና ልምድ ያላቸው ኩባንያዎችን እንዲሰማሩ ድጋፍ ማድረግ እና የእሴት ማበልፀግ ሥራዎች የቀጣዩ እቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡

በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ የሚገቡ ማዕድናትን፣ የማዕድን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የውጭ ምንዛሬ ጫናን ለመቀነስ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ተቋማት ጋር ከተሰሩ ስራዎች መካከል የብረት፣ የማዳበሪያና የግንባታ ግብአት ማዕድናት በልዩ ሁኔታ ለማልማት በፕሮጀክት ደረጃ በማደራጀት በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውም ተጠቁሟል፡፡

በዚህም በየዓመቱ በአማካይ ከ300 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ ከውጭ ይገባ የነበረውን የድንጋይ ከሰል ለማስቀረት ለስምንት ኩባንያዎች በተለያዩ ክልሎች የከፍተኛ ደረጃ ምርትና ፕሮሰሲንግ ፈቃድ መሰጠቱን የጠቆመው የሚኒስቴሩ ሪፖርት፣ እነዚህ ኩባንያዎች የድንጋይ ከሰል በብዛት በማምረት የጥራት ደረጃውን በማሳደግ ከውጭ ሀገር የሚገባውን በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት እንዲቻል እየተሰራ መሆኑን አብራርቷል፡፡

የማዕድን ሚኒስቴር በየአመቱ ለብረት ግዢ የሚወጣውን አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ ወጪ ለመተካት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያሉ የብረት ፋብሪካዎች በግብአት እጥረት ምክንያት ስራ እንዳያቆሙ በጊዜያዊነት ከመከላከያ ሚኒስቴርና ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት 386 ሺህ ቶን ስብርባሪ ብረቶች በመጠነኛ ዋጋ እንዲሸጡላቸው በማመቻቸት በበጀት ዓመቱ ከ409 ሺህ ቶን በላይ ብረት ሊመረት እንደተቻለ ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም የብረት ምርት አቅርቦትን በዘላቂነት በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት፣ በአገር ውስጥና በውጭ ኩባንያዎች በተደረጉ ጥናቶች በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች የብረት ማዕድን ክምችት እንዳለ በመታወቁ ማዕድኑን ማምረት እንዲቻል ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት ለሚያከናውነው አማካሪ ግብዓት የሚሆን የቅድመ አዋጭነት ጥናት እየተከናወነ ይገኛል ብሏል፡፡

በዚህም ማዳበሪያ ለማምረት ዋነኛ ግብአት የሆኑትን ካልሺየም ፎስፌት፣ ሰልፈርና ፖታሽ የክምችት መጠናቸው የተለየ ሲሆን ዋነኛ ግብአት የሆነውን አሞኒያ ለማምረት የነዳጅ እና የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት ግምትና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትን ግምገማ ለማካሄድ ዓለምአቀፍ የአማካሪ ግዥ ጨረታ ወጥቶ ፍላጎት ያሳዩትን የብቃት ሁኔታቸው በልየታ ላይ ይገኛል ተብሏል፡፡

በጥናት የተረጋገጠውን የተፈጥሮ ጋዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰርቲፋይ ለማድረግ ጨረታ ወጥቶ በአራት ወራት ውስጥ ስራውን አጠናቆ የሚያስረክብ ኩባንያ ጋር ውል ተፈፅሟል፡፡

ሲሚንቶን በሚመለከት የፋብሪካዎችን የምርት አቅም ለማጎልበት የነበሩባቸውን የጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት፣ የመለዋወጫና የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት በጊዜያዊነት ለመፍታት የተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 10 ነጥብ 2 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ምርት ለማቅረብ ታቅዶ በፀጥታ ችግር እንዲሁም በኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ምክንያት 6 ነጥብ 2 ሚሊዮን ቶን ተመርቷል ተብሏል፡፡

የዕብነ በረድና ግራናይት ማዕድናትን የጥራት ደረጃቸውን ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚችል የሰለጠነ ባለሙያ ለማፍራት የሚያስችል የፋይናንስ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ለሥልጠና የሚያስፈልጉ የሥልጠና ሰነዶችም እየተዘጋጁ እንደሆነና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የዕብነ በረድ ልህቀት ማዕከል ለመገንባት የቅድመ ዝግጅት ስራ መጠናቀቁ ታውቋል፡፡

# የሃይማኖት ተቋማት 5ኛ ቅርንጫፉን በደቡብ አፍሪካ ከፈተ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በሠላም ግንባታና በአብሮነት እሴቶች ዙሪያ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጋራ እንዲሰሩ ለማስቻል አምስተኛ ቅርንጫፉን በደቡብ አፍሪካ መመሥረቱን ገለጸ።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በሠላም ግንባታ ፣ በአብሮነት እና በመከባበር የጋራ እሴቶች ዙሪያ የሚሰራውን ሥራ አጠናክሮ ለመስራት፣ ተቋማዊ ጥንካሬ እንዲፈጠር ከማስቻል በተለያዩ ሀገራት ቅርንጫፎች እየመሰረተ መሆኑን የጉባኤው ጠቅላይ ጸሐፊ ቀሲስ ታጋይ ታደለ ለኢዜአ ተናግረዋል።

በዚህም ከኢትዮጵያ ውጭ አምስተኛ እና በአፍሪካ ደረጃ ሁለተኛውን ቅርንጫፍ በደቡብ አፍሪካ ፣ፕሪቶሪያ መከፈቱን ገልጸዋል።

ፕሪቶርያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከሁሉም ቤተ እምነት ከተወከሉ የሃይማኖት አባቶች ጋር በአስፈላጊነቱ ዙሪያ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ መስከረም 10 ቀን 2015 ዓ.ም የጉባኤው ምስረታ ተካሂዷል ብለዋል።

በመመስረቻ መድረኩ የጉባኤውን ቅርንጫፍ የሚመሩ የቦርድ አባላት ከሁሉም ቤተ እምነት የተወከሉ አባቶች መመረጣቸውን አክለዋል።

በተጨማሪ በመድረኩ ላይ በደቡብ አፍሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሙክታር ከድር በወቅታዊ የሀገር ጉዳይ ላይ አጀንዳ ቀርቦ ውይይት መካሄዱን ጠቁመዋል።

የተፈናቀሉ ዜጎችን ለማቋቋም በሚደረገው ጥረትም እስከ መስከረም 30 ቀን 2015 ድረስ በአጭር ጊዜ ሀብት ለማሰባሰብ አዲሱ የተቋቋመው ቦርድ በዚህ ሀገራዊ ሥራ ለመጀመር ቃል በመግባት ተጠናቋል ብለዋል።

ዜና

# የአውሮፓ ሕብረት የፓርላማ አባላት ከለውጡ ወዲህ በኢትዮጵያ ያለውን ለውጥ አደነቁ

## - ኢትዮጵያ ምንጊዜም ለሰላም ዝግጁ መሆኗን አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ ተናግረዋል

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- የአውሮፓ ሕብረት የፓርላማ አባላት ከለውጡ ወዲህ በኢትዮጵያ ያለውን ለውጥ አደነቁ። በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተከሰተውን ግጭት በሰላም ውይይት ለመፍታት መንግሥት ምንጊዜም ቁርጠኛ መሆኑንም አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ ተናግረዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቋሚ ኮሚቴ አባላት አቻ ከሆነው አውሮፓ ሕብረት የፓርላማ አባላት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተወያዩበት ወቅት የአውሮፓ ሕብረት የፓርላማ አባል ሮበርት ቤድሮን እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ እየታየ ያለው ለውጥ የሚደነቅ ነው። በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ለሶስተኛ ጊዜ የተቀሰቀሰው ግጭት በማቆም ሁሉም ወገኖች ወደ ሰላም ውይይት እንዲመጡ ሕብረቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

ሌሎች የሕብረቱ አባላትም የኢትዮጵያ ፓርላማ ያመጣው ለውጥ አድንቀው፣ ባላቸው ተሳትፎ ከሕብረቱ ፓርላማ የሴቶች ተሳትፎ በአንድ ቁጥር የሚበልጥ መሆኑ የሚደነቅ ነው። የሴቶችን በኢኮኖሚና በፖለቲካ ዘርፍ ተሳትፏቸው ለማሳደግ ከተቋቋመው ‹‹ኮከስ›› ጋር በአጋርነት ሕብረቱ እንደሚሰራም ገልጸዋል።

የሕብረቱ ተወካዮች የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት አድንቀው፣ አሁንም ወደ ትግራይ የሰብአዊ ድጋፍ ያለገደብ እንዲደርስ፣ በአፍሪካ ሕብረት አደራዳሪነት የተጀመረው የሰላም ሂደት ውጤት ላይ እንዲደርስ ድጋፍ እናደርጋለን ብለዋል።

አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ በበኩላቸው፣ ስለ የኢፌዴሪ ፓርላማ አወቃቀር፣ የኢትዮጵያ አጠቃላይ የዴሞክራሲና ልማት እንቅስቃሴ ፣ ስለ ሴቶች የፓርላማ ተሳትፎ፤ ለአውሮፓ ሕብረት ምክር ቤት ልዑክ በዝርዝር አስረድተዋል።

አቶ ታገሰ የአውሮፓ ሕብረት የፓርላማ አባላት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ስላለው ሁኔታ፣ ኢትዮጵያ ብዝሃ ባህል፣ ቋንቋ፣ ብዝሃ ፖለቲካ ያላት አገር ናት። በየትኛውም ሁኔታ ልዩነት ሊኖር ይችላል፣ ልዩነት የሚፈታው ግን በጦርነት ሳይሆን በውይይት መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔው ምክክርና ውይይት ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ወሳኝና አስፈላጊ በመሆኑ ፓርላማው ብቁ የሆኑ የምክክር ኮሚሽን ሰይሞ እየሰራ ነው። በሁሉም የአገሪቱ አካባቢ የሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥያቄዎች አሏቸው። በብዝሀነታችን ምክንያት በታሪክ፣ ፖለቲካዊ ፍላጎቶች፣ በኃይማኖት፣ በመሰረተ ልማትና ሌሎች ጥያቄዎች አሏቸው። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ውይይትና ምክክር አስፈላጊ በመሆኑ ኮሚሽን መቋቋሙን አፈጉባኤው አብራርተዋል።

እኛ ለምክክርና ለውይይት በራችን ክፍት ነው ያሉት አፈ ጉባኤው፤ አሸባሪው ሕወሓት ግን ራሱ የነደፈውን ሕገ መንግሥት ሳይቀር በመጣስ የምርጫ ቦርድ ሰይሞ ምርጫ ከማካሄድ አልፎ የአገር መከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት አደርሷል። ይህም መንግሥት ሳይወድ ተገዶ ወደ ሕግ ማስከበር መግባቱን አብራርተዋል።

ግጭት ውስጥ እንድንገባ ያደረጉን ወንድሞቻችንና ጓደኞቻችን ናቸው ያሉት አፈ ጉባኤው፤ በውይይት ችግሮቻችን በጠረጴዛ ዙሪያ የመፍታት ቁርጠኝነቱና ፍላጎቱ ስላለን ግጭትን በማቆም ችግሮቻችን በውይይት እንፍታ ብለን በተደጋጋሚ ጥሪ አቅርበናል ሲሉ ገልጸዋል።

በጾታዊ እኩልነት፣ በግጭት ዙሪያና በሰብአዊ መብት ጉዳይ ላይ የተነሱ ጉዳዮችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንና የተባበሩት መንግሥተታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በጋራ ያካሄዱት የምርመራ ውጤት ተከትሎ የመልሶ ማቋቋም ስራ እየተሰራ መሆኑን አመልክተው፤ ነገር ግን ከሰሞኑ የወጣው የሀሰትና ለአንድ ወገን ያጋደለ ሪፖርት አሳዝኖናል ነው ያሉት አፈ ጉባኤው።

የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ዲማ ኖጎ፣ የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ አብራርተዋል። የኢትዮጵያ ፓርላማም ሆነ መንግሥት ግጭት ለችግሮች መፍትሄ እንዳልሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። ትልቁ መፍትሄ በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት ችግሮችን መፍታት ነው። ለትግራይ ክልል ያልተገደበ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲደርስ መንግሥት በከፍተኛ ትኩረት ሰርቷል ብለዋል። ድርድሩም በአፍሪካ ሕብረት ጥላ ስር እንዲደረግ ፓርላማው ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ዶክተር ዲማ አብራርተዋል።

የጤና፣ የማህበራዊ፣ ባህል፣ ስፖርትና ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ወርቅሰሙ ማሞ በበኩላቸው ከለውጡ ወዲህ በመንግሥት ቁልፍ ቦታዎች ውስጥ 50 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። በምክር ቤቱ 42 በመቶ ሴቶች መሆናቸውን ገልጸዋል። በተለይም የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ‹‹ኮከስ›› የተሰኘ አደረጃጀት ተፈጥሮ እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

# ማዕከሉ የጦር አውሮፕላኖችን የመጠገን አቅሙን ማሻሻሉ የሠራዊቱን ወታደራዊ ዝግጁነት አሳድጓል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አቪየሽን ከባድ ጥገና ማዕከል የጦር አውሮፕላኖችን የመጠገን አቅሙን ማሻሻሉ የሠራዊቱን ወታደራዊ ዝግጁነት ከፍ ማድረጉን የኢትዮጵያ አየር ሃይል አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አየር ሃይል ዋና አዛዥ ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ ለሀገር ውስጥ ሚዲያዎች እንደተናገሩት፣ የሠራዊቱን ወታደራዊ ዝግጁነት ከፍ ለማድረግ ከዚህ በፊት በነበሩ መንግሥታት የተገዙ የጦርና የመለማመጃ አውሮፕላኖችን በብቃት በመጠገንና በማደስ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።

ማዕከሉ በ2014 ዓ.ም የአገልግሎት እድሜያቸው ያጠናቀቁ አምስት L39 አውሮፕላኖችን የማሻሻልና የመጠገን ስራ በመስራት የአገልግሎት ዘመናቸውን መጨመር ተችሏል ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይልማ፤ እነዚህ አውሮፕላኖች በአየር ሃይሉ ከአርባ ዓመት በላይ የቆዩ በመሆናቸው አጠቃላይ የጥገና ሥራቸው አስቸጋሪ ነበር ብለዋል። ነገር ግን በተደረገው የማሻሻያና የጥገና ስራ ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ተችሏል መቻሉን ተናግረዋል።

ሀገራችን ያላትን ሀብት በአግባቡ የምትጠብቅና የምትጠቀም ከሆነ ከአፍሪካ ቀዳሚው የአየር ሃይል መሆን ትችላለች ብለዋል።

የአቪየሽን ማዕከሉ የመጠገንና የማደስ አቅም እያዳበረ ሲሄድ ኢትዮጵያ ለሚገጥሟት ስጋቶች የሚያስፈልገውን የጦር አውሮፕላን በዘመናዊና በሳይንሳዊ መንገድ ማምረት ትችላለች ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይልማ፤ ማዕከሉ የጠገናቸውንና የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያሻሻላቸው የጦር አውሮፕላኖች እኤአ ከ1986 እስከ 1989 የተመረቱ መሆናቸውን አውስተዋል።

እንደ ሌተናል ጄኔራል ይልማ ገለጻ፣ አየር ሃይሉ በአሁኑ ዘመን የሚመረቱ አውሮፕላኖች ያላቸውን ደረጃ እና ቴክኖሎጂ የሚመጥኑ አውሮፕላኖችን ለማምረት እየሰራ ነው። ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት የተመረቱ አውሮፕላኖችን በዚህ ዘመን ከሚመረቱ አውሮፕላኖች እኩል አቅምና ቴክኖሎጂው ያላቸው ለማድረግም ጥረት እየተደረገ ነው።

አውሮፕላኖቹ ተጠግነው በመውጣታቸው ብቻ ለውጊያ፣ ለመለማመጃና የአየር ክልልን ለመጠበቅ እየተገለገልንባቸው እንገኛለን ያሉት ሌተናል ጀነራሉ፤ አውሮፕላኖቹ ከመጠገናቸው በፊት ለአየር በአየር ውጊያ ብቻ ይጠቀሙባቸው እንደነበር አውስተዋል።

እንደ ሌተናል ጄኔራል ይልማ ገለጻ፣ ጥገናው ሳይንሳዊ በመሆኑ ሀገራዊ ግዳጃችንን በሚገባ መወጣት ችለናል። ከውጭ እንገዛቸው የነበረን አውሮፕላኖች በሀገራችን እንዲመረቱ ማድረግ እንደሚቻልም ያሳየ መሆኑን ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት አውሮፕላን ጠግኑልን የሚሉ ጥያቄዎች እያቀረቡ ነው ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይልማ፤ አቅማችንን በአስተማማኝ መልኩ ካረጋገጥን በኋላ ጎን ለጎን የሚመጡ ገበያዎች የምንጠቀም ይሆናል። በዚህም ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ገቢ የምናገኝ ይሆናል ብለዋል።

እንደ ሌተናል ጄኔራል ይልማ ገለጻ፣ በመጀመሪያ ዙር ወደ ጥገና ማዕከል ከገቡ 6 የ L39 ማሰልጠኛ አውሮፕላኖች ውስጥ አምስቱ ሥራቸው ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆና የፍተሻ በረራ ተደርጎላቸው ለአገልግሎት በቅተዋል። አንዱ ማዕከሉ ጥገና እየተደረገለት ነው ።

እነዚህ ተበላሽተውና በየቦታው ቁመው የነበሩትን አውሮፕላኖች የጥገና ስራ በማካሄድ የቴክኖሎጂ አቅማቸውንና የአገልግሎት ጊዜያቸውን ማሻሻል መቻሉን ጠቁመው፤የተበላሹ አውሮፕላኖች ወዲያው ተጠግነው አገልግሎት በመስጠታቸውም የሀገሪቷን ሀብት በአግባቡ መጠቀም መቻሉን ገልጸዋል፡፡

እንደ ሌተናል ጄኔራል ይልማ ገለጻ፣ በአቬየሽን የጥገና ማዕከሉ ከገቡ አውሮፕላኖች 50 መቶ አውሮፕላኖች ተጠናቀው ወደ ሥራ ገብተዋል። ይህም በማዕከሉ ታሪክ ዓለም አቀፍ መስፈርታቸውን በጠበቀ መልኩ አውሮፕላኖቹ በመጠገናቸው የአየር ሃይሉን የዝግጁነት ደረጃ ከፍ ማድረግ ተችሏል።

ማዕከሉ ከሪፎርሙ በፊትና አሁን ያለው ሁኔታ ጭራሽ የማይገናኝ ነው ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይልማ፣ ማዕከሉን ሌሎች ተመሳሳይ ዓለም አቀፍ ተቋማት የደረሱበት ደረጃ እንደምናደርሰው ምንም ጥርጥር የለኝም፤ ግዳጃችንን እየተወጣን ያለነውም አመርቂ በሆነ መንገድ ላይ ነው ብለዋል።

እንደ ሌተናል ጄኔራል ይልማ ገለጻ፣ በቅርብ ጊዜ የሀገራችንን ድንበር ጥሶ የገባውን አውሮፕላን መትተን መጣላችን የአየር ሃይላችንን ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን የሚያሳይ ነው። ይህንንም ጠላቶቻችን በደንብ ይረዱታል። አሁን የምንገነባው ተቋም በቅርብ ላጋጠሙን ትንንሽ ችግሮች ሳይሆን ታላቋን ኢትዮጵያ በሚመጥን መልኩ መሆኑን አመልክተዋል።

ሌተናል ጄኔራል ይልማ፣ ሀገራችን ያለችበት ምስራቅ አፍሪካ ችግር የማይጠፋው ቀጠና ነውና እያንዳንዱ የምንሰራው ሥራ አሁንና ወደፊት የሚፈጠሩ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም ሊገጥመን የሚችለውን ጠላት ታሳቢ አድርገን ነው ብለዋል።

# አንዳንድ የውጭ ሃይሎች አሸባሪውን ትህነግ ከሞት አትርፈው ኢትዮጵያ ላይ ለመጫን ይፈልጋሉ

**አዲሱ ገረመው**



አቶ ምዑዝ ገብረህይወት

አዲስ አበባ፡- አንዳንድ የውጭ ሃይሎች የአሸባሪውን ትህነግ ከሞት በማትረፍ እና ወደሥልጣን በመመለስ ዳግም የአሻንጉሊት መንግሥት ለመመስረትና በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እንደፈለጉ ለማዘዝ እንደሚፈልጉ የሰብዓዊ መብትና የመልካም አስተዳደር ተሟጋች አቶ ምዑዝ ገብረህይወት ገለጹ።

አቶ ምዑዝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አንዳንድ የውጭ ሃይሎችና ተቋማት ከሚዲያዎቻቸው ጭምር በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡትና የሽብር ቡድኑን የሚደግፉት ለትግራይ ሕዝብ አስበው ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ነው።

እነዚህ ሃይሎች አሁን ያለው መንግሥት እነሱ በሚፈልጉት መልኩ የሚነዳና የሚሸከረከር ባለመሆኑና የሕዝቡን ልማትና እድገት በማስቀደም ውጤት እያስመዘገበ በመሆኑ ምቾት አልሰጣቸውም። በዚህ የተነሳ ይህንን መንግሥት በማንሳት በምትኩ የራሳቸውን አሻንጉሊት መንግሥት መፍጠር ይፈልጋሉ። ለዚህ ምቹ ሆኖ ያገኙት ደግሞ አሸባሪውን ትህነግ ነው።

አቶ ምዑዝ እንዳሉት፤ አሸባሪው ትህነግ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ነዳጅና ሌሎች የእርዳታ ግብዓቶችን እየዘረፈ እያዩ አሁንም ከሽብር ቡድኑ ጎን በመሰለፍ እውቅና ሲሰጡት ይስተዋላል። የነዚህ ሃይሎች ወያኔን መደገፍ ለትግራይ ሕዝብ ምንም ጠቀሜታ የለውም። ለትግራይ ሕዝብ የሚደርስለት ሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ እንጂ የውጭ ሃይሎች አይደሉም።

እንደ አቶ ምዑዝ ገለጻ፤ የሕወሓት ምሽግ ሲደረመስ የተገኘው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የእርዳታ ከረጢት ነው። የሽብር ቡድኑ ለሕዝብ የመጣውን ንብረት ለራሱ ተጠቅሟል። ሆኖም ሕብረተሰቡን ሳያግዙ፤ ለተወረረው የአማራና አፋር ሕዝብ ድምጽ ሳይሆኑ ወያኔን መደገፋቸውን በተለያዩ ተግባራት እያሳዩ ይገኛሉ።

አሸባሪውን ቡድን አጠናክረው ኤርትራንና ኢትዮጵያን በማተራመስ ቀይ ባህርን ለመቆጣጠር እንዲችሉ ዛሬም ኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር እየሰሩ ይገኛሉ ያሉት አቶ ምዑዝ አካሄዳቸው ትላልቅ ወደቦችን ለመቆጣጠር ነው ብለዋል። ፍላጎታቸው እነርሱን የሚታዘዝ አሻንጉሊት መሪ ማግኘት ማስቀመጥ እንደሆነና ለዚህ ደግሞ ሕወሓትን ምርጫቸው ማድረጋቸውንም ጠቁመዋል።

“ሥራቸውን ለመፈጸም የሚንቀሳቀሱት በአሸባሪው ሕወሓት በኩል ነው። በየጊዜው የሚያሳዩት ያልተገባ ጣልቃገብነትም ይህንኑ ያመላክታል” ነው ያሉት አቶ ምዑዝ።

አቶ ምዑዝ የሽብር ቡድኑ የሰላም ፈላጊ በመምሰል ዛሬም ወጣቶችን በመመልመል እያሰፈጀ እንዳለም ጠቅሰዋል። የውጭው ማህበረሰብ ይህንን እያወቀ ቡድኑ ላይ ጫና ከመፍጠር ይቅል በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት እየሞከረ እንደሆነ በመግለጽ፤ እነ ሶርያን በጥቂት ጊዜ ያፈረሱት አካላት ዛሬ ላይ ሕወሓት እንዲጠነክርና ኢትዮጵያን ለማፍረስ ቢጥሩም፤ ጠንካራ የመከላከያ ሠራዊትና ጠንካራ መንግሥት ስላለ ሊሳካላቸው እንዳልቻለ ወደፊትም እንደማይሳካላቸው አስታውቀዋል።

የአሸባሪው ትህነግ ሰዎች ከኢትዮጵያ ይልቅ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት መልማት የሚያስደስታቸው ናቸው በማለት፤ እንዲህ አይነትን የአገር ከሃዲ ይዞ መጓዝ አያስፈልግም፤ ወደፊትም ቢሆን ቡድኑ ወደ ድርድር የሚመጣ ከሆነ ትጥቁን አስቀድሞ መፍታት እንዳለበት ነው የገለጹት።

አቶ ምዑዝ አክለውም በዲፕሎማሲው ረገድ በተገቢው መንገድ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል። አሸባሪው ትህነግ የውሸት ፕሮፓጋንዳን በማራገብ የሚታወቅ ነው፤ ብለዋል። ከትግራይ በሽብር ቡድኑ የሚለቀቀውን ውሸት አባዝተው ወደ ውጭ የሚዘረጉት የኢትዮጵያ ከሃዲዎች በርካቶች እንደሆኑ ጠቅሰው፤ በሽብር ቡድኑ የሚራገበውን የውሸት ፕሮፓጋንዳ በእውነተኛ መረጃ መመለስ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ለዚህም ጋዜጠኞችና ምሁራንን ጨምሮ ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጎች ሌት ተቀን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል።

ዲፕሎማሲው የጥቂት ግለሰቦች ሥራ አይደለም ያሉት አቶ ምዑዝ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የአገሩን ሀቅ ለውጭው ማህበረሰብ በማሳወቅ ረገድ ሚናውን ሊወጣ እንደሚገባ አስታውቀዋል። ስለ አገር ጉዳይ ገንዘብ ከማዋጣት ባሻገር የሽብር ቡድኑን የውሸት ፕሮፓጋንዳ በማጋለጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን ያስፈልጋል ብለዋል።

ዜና

# ቦይንግ-737 ማክስ አውሮፕላን ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውል የኢንሱሌሽን ብላንኬት ማምረቻ ሾፕ ተመረቀ

**ሞገስ ጸጋዬ**



ፎቶ ፡- በፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በስድስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ቦይንግ-737 ማክስ አውሮፕላን ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውል የኢንሱሌሽን ብላንኬት ማምረቻ ሾፕ አስመረቀ፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው በምረቃ ሥነሥርዓቱ ወቅት እንደገለጹት፤ ከጣሊያኑ ጀሸን ስካይ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ጋር ስምምነት በማድረግ ለቦይንግ-737 ማክስ አውሮፕላን የኢንሱሌሽን ብላንኬት ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውል ሾፕ እውን ሆኗል፡፡ ያስመረቅነው ምርት አውሮፕላን ለማምረት ከሚያስፈልጉት እቃዎች መካከል አንደኛው ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ተመርቶ ለቦይን ኩባንያ ቦይንግ 737 ማክስ አገልግሎት የሚሰጥ ምርት ነው ብለዋል፡፡

ሾፑ የተቋቋመው በስድስት ሚሊዮን ዶላር መሆኑን የገለጹት ስራ አስፈጻሚው፤ የኢንሱሌሽን ብላንኬት በማምረት ለአገራችን ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል፡፡ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የስራ እድልንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ይከፍታል ብለዋል፡፡

በቀጣይ ተጨማሪ ገንዝብ ኢንቨስት በማድረግ የሾፑን አቅም በማሳደግና በስፋት እንዲያመርት ወደ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ለማሸጋገር እቅድ ተይዟል፡፡ ከሲንሱሌንሽን ብላንኬት በተጨማሪ ሌሎች እቃዎችን በማምረት ለአገራችን ብዙ የውጭ ምንዛሬ ለማምጣትና ለብዙ ኢትዮጵያውያን የስራ እድል ለመፍጠር እቅድ ስለመኖሩም ተናግረዋል፡፡

እንደ ስራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ የኢትዮጵያ አር መንገድ መንገደኞችንና እቃዎችን ከማጓጓዝ በተጨማሪ ወደ ቴክኖሎጂው ዘርፍ በመግባት ላይ ነው፡፡ ሾፑ በገቢ ደረጃ ከመት አመት እየጨመረ ይሄዳል፤ በሚቀጥለው አመት ወደ ሁለት ሚሊዮን ዶላር የሚሆን ገቢ ይኖረዋል፡፡ ከዛ በኋላ በየአመቱ እያደገና እየተስፋፋ ይሄዳል ብለዋል፡፡

ኢንሱሌሽን ብላንኬት አውሮፕላኑ ከፍታውን እየጨመረ በሚሄድበት ወቅት የበረራ አስተናጋጆችና መንገዶኞችን ከከፍተኛ ቅዝቃዜና ከሞተር ድምፅ የሚከላከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የጣሊያን አምባሳደር አጎስቲኖ ፓልሴ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ቴክኖሎጂው ዘርፍ መሰማራቱን አድንቀው አየር መንገዱና የጣሊያኑ ስካይ ቴክኖ ግሮቭን ተስማምተው በጋራ መስራታቸው ቆየውን የሁለቱን አገራት ትብብር የበለጠ እንደሚያሳድገው ገልጸዋል፡፡

በቀጣይም ጣሊያን የኢትዮጵያን እድገትና ብልጽግና በመደገፍ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ይሰራል፡፡ እንዲሁም ጣሊያን ለኢትዮጵያ የምታደርገውን ትብብር አጠናክራ ትቀጥላለች ብለዋል።

## የኮሚሽኑ "ሪፖርት" ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ሲሠራ በኮሚሽኑ የአሠራር ሥርዓቶች ላይ አለመመስረቱ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመሰል ጥናቶች መሠረታዊ እሳቤዎች እና ደረጃዎች ላይ ተመሥርቶ አለመሆኑ ከገለልተኝነት ጋር የተያያዘ ጥያቄ ጭምር የሚያስነሳ ነው። የማረጋገጫ ደረጃዎችን በተመለከተም ዝርዝር የሆኑ ደረጃዎችን ባላሟላ መልኩ የተዘጋጀ ነው።

ከመረጃ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ብዙዎቹ የኮሚሽኑ መደምደሚያዎች ምንም ዓይነት ማስረጃ ባልጠቀሰበት ሁኔታ ወይም ተዓማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባ መልኩ መንግሥትና ተቋማት ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ላይ መደምደሚያ ላይ የደረሰበት ነውም ብለዋል ዶክተር ታደሰ።

በመሆኑም በተጠቀሱት ተአማኒነትን በሚያጎድሉ እና ገለልተኝነትን ጥያቄ ውስጥ በሚያስገቡ ሂደቶች የተጠናው ጥናት የፖለቲካ ፍላጎትን ለማስፈፀም የቀረቡ ሰነዶች እንጂ ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በመፈለግ መንፈስ የተዘጋጀ ሙያዊ "ሪፖርት" አለመሆኑን መንግሥት ያምናል ብለዋል።

መንግሥት፣ የኮሚሽኑ "ሪፖርት" የተወሰኑ ኃይሎች ከኋላ የሚያራምዱትን አጀንዳ ለማስተግበር ሥራ ላይ እንደዋለ መረጃ እና ያን ሂደት ተከትሎ እንደተዘጋጀ "ሪፖርት" ይመለከተዋል ሲሉ ገልጸዋል።

የፍትህ ሚኒስትር ዴኤታ ፈቃዱ ፀጋ በበኩላቸው መንግሥት በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት በአጠቃላይ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ምርመራ መደረጉንና ሂደቱም እንደቀጠለ ገልጸው፣ በዚህም የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ሲሠራ መቆየቱን አክለዋል። በሕግ ማስከበር ሂደቱ ጀምሮ ጥፋት የፈፀሙ የሠራዊቱ አባላት በወታደራዊ ፍርድ ቤት የፍርድ ውሳኔ እንደተሰጠም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ምክትል ኮሚሽነር ዘላለም መንግስቴ በበኩላቸው ከሕወሓት ሁለተኛ ዙር ወረራ በኋላ የሚኒስትሮች ግብረሃይል ውስጥ በተቋቋመ ንዑስ የምርመራና ክስ ኮሚቴ በአማራና አፋር የደረሱ ጥፋቶችን ምርመራ ማከናወኑን ተናግረዋል።

በምርመራው ከ26 ሺህ በላይ ሕዝብ መኖሪያ ቤቶች መጎዳቱን፣ 28 ሺህ ሱቆች፣ 2 ሺህ 500 ጤና ጣቢያዎች መውደማቸውን ገልጸው ለዝርዝር ሂደቱ የምስክሮች ምርመራ እየተካሄደ መሆኑንና በሌሎች አካባቢዎችም ተመሳሳይ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አብራርተዋል።

## ለጎርፍ ተጋላጭ የነበረው አካባቢ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የማብቀል አቅሙን እንዲገልጥ ደግሞ፣ የተሻሻለ የመስኖ አሠራር በመተግበር ላይ ይገኛል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትናንት በአፋር ክልል አሚባራ እና ሀሩክ ወረዳዎች በ20ሺ ሄክታር ላይ በኩታ ገጠም እየለማ የሚገኝ የጥጥ ምርት ጎብኝተዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አነሳሽነት በተካሄደው አረጓዴ አሻራና የበጋ ስንዴ አመርቂ ውጤት መገኘቱ ይታወቃል፡፡ ባለፈው ዓመት ከውጭ የሚገባን ስንዴ በአገር ውስጥ ምርት ለመተካትና በምግብ ራስን ለመቻል በበጋ መስኖ 600 ሺህ ሄክታር መሬት በማልማት 26 ሚሊዮን ኩንታል ማምረት ተችሏል፡፡

በያዝነው ዓመትም የስንዴን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፤ በበጋ ስንዴ የተገኘውን ውጤታማ ስራም በወተት፣ በእቁላል፣ በዶሮና በማር ምርት ለመድገም በዘንድሮው ዓመት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ባለፈው ዓመት መጨረሻ ወር ላይ ከወጣቶች ጋር በነበራቸው ውይይት መናገራቸው የሚታወስ ነው፡፡

## ኢትዮጵያ የተመድ ሰብዓዊ መብት...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አስቀድሞ የታቀደ እና ፖለቲካዊ ዓላማ ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

ኤክስፐርቶቹ የመጀመሪያ ግኝት ብለው ያወጡት "ሪፖርት" ለምርመራ ወደ ክልሎቹ በእግራቸው ሳይረግጡ ያወጡት መሆኑ እና የሪፖርቱ ድምዳሜዎችም እርስ በርስ የሚጋጩ እና አድሏዊ ናቸው ሲሉ አምባሳደሩ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን ከመረጃ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ያጋጠመውን ተግዳሮት እንደሚገነዘበው በመጥቀስ "ሪፖርቱ" ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶችን እና የጦር ወንጀሎች መፈጸማቸውን በተመለከተ ፍጹም የተሟላ አለመሆኑን ያሳያል ብሏል።

ኮሚሽኑ "በሪፖርቱ" በአፋር ክልል ላይ ተፈጽሟል ስለሚባለው የከፋ የሰብአዊ መብት ጥሰትና ወንጀል ምንም አለማለቱ አንዱና ትልቁ ጉድለቱ መሆኑን ነው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በመግለጫው ያብራራው።

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር በመሆን በጥምረት ያካሄዱት ምርመራ ውጤት የተሟላና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ምክር ቤትም ተቀባይነት ያገኘ፤ ምርመራው ገለልተኛና ግልጽኝነትን ባሰፈነ መልኩ የተሰራ መሆኑን በመጥቀስ ምስጋና ያተረፈ እንደሆነ ጠቅሷል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በጋራ በተሰራው የምርመራ ውጤት ላይ ለተደረሰባቸው ግኝቶች የተቀመጡ ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል።

በሪፖርቱ መሰረት በሁሉም ወገኖች ያሉ ሃይሎች ምክረ ሃሳቡን ተቀብለው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀረበው ኮሚሽኑ፤ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ሚኒስትሮች የተካተቱበት ግብረ ሃይል በማቋቋም የሄደበትን ርቀት እንዲያጠናክር ጠይቋል።

ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽንም የጋራ ምርመራ ውጤቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ እንዲደግፍና ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ አቅርቧል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንም ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በተቀመጠው የትብብር ማዕቀፍ ውስጥ ለመተባበር ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ ገልጿል።

ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን በሰሜኑ ኢትዮጵያ ያለውን ጉዳይ በጥንቃቄ ሊያይና ሊመረምር እንደሚገባው በማሳሰብ፤ ሁሉንም ተጎጂ የሕብረተሰብ ክፍሎችና ክልሎች ፍትህዊ ሆኖ ሳያዳላ ሊመለከት እንደሚገባው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ምክረ ሃሳብ ሰጥቷል።

## ኮሚሽኑ ይፋ ያደረገው የሐሰት ድርሰት...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ተቃራኒ የቆመ ነው።

እርሳቸው እንደተናገሩት፤ ይህን "የምርመራ ሪፖርት" ነው ብለው ባወጡት የሐሰት ድርሰት አማካይነት ኢትዮጵያ ላይ ያደረሱትን ስህተት ማረሳሳት አይችሉም። "ሪፖርቱ" ሆን ብሎ ስህተትና ሰበብ ፈልጎ ያንን በግፍ የተጨማለቀ የሕወሓት ቡድን ህልውና ለማስጠበቅ የታቀደ ነው። የአሸባሪውን ቡድን የተበላሸና የጎደፈ አሰራሩን ለመደበቅም የተዘጋጀ ነው። ምክንያቱም ሕወሓት እንደ አሸባሪ የሚሰራውን ስራ ኢትዮጵያውያን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አጋልጠውታል። ይህ ማለት ደግሞ እነርሱም ራሳቸው ለአሸባሪው ቡድን አቅጣጫ በመስጠት እንዲሁም የፋይናንስ አቅርቦት በማድረስ አብረውት ሲጓዙ የቆዩበት ነው። ስለዚህም ይህንን የእነርሱን የግፍና የበደል ሸክም ወደሌላው መውሰድና ማላከክ ይፈልጋሉ። ይህንን ደግሞ ኢትዮጵያውያኑም ሆኑ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብም በፍጹም የሚቀበሉት አይሆንም።

በአሁኑ ሰዓት ሪፖርቱን ይፋ የማድረጋቸውም ሁኔታ እርዳታ እስከጉድጓድ የወሰዱለትን፣ መሳሪያ እስከ ምሽግ ያደረሱለትን ቡድን እንዲወቀስባቸው ስለማይፈልጉ ነው ያሉት አቶ እንዳለ፣ ይሁንና ከጀርባቸው በተለያየ አሰራር ቢኖሩም ቡድኑን ማዳን አይችሉም ብለዋል።

ይፋ ባደረጉት "ሪፖርት" አሸባሪውን ቡድን መደገፋቸው እጅግ ከሞራል የወረደ ስራ ነው። ኮሚሽኑ ሰብዓዊ መብትን ለተራ ስራና ለፖለቲካ መጠቀሙ አሳፋሪም ጭምር ነው ብለዋል። "ሪፖርቱ"ን እንደሪፖርት በራሱ ጽፈው ማውጣታቸው ምንም አይነት ሞራል እንደሌላቸው የሚያሳይ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ሕጋዊ የሆነና ዓለም አቀፋዊ የሆነ ድርጅት ያጠናውን ሪፖርት ትተው ሶስት ግለሰቦች ወደስፍራው ሳይመጡ በስማ በለው ድርሰት እንዲጽፉ ተፈቅዶላቸው ይፋ መደረጉ ከተዓማኒነት የራቀ በመሆኑ አሸባሪውን በዚህ አካሄዳቸው ሊያድኑበት አይችሉም። በዚህ ጉዳይ ዓለም ባለፈው ታዝቧቸዋል፤ አሁንም እየታዘባቸው ነው። ይህ አካሄዳቸው ነገሮችን በፈለጉት መጠን የሚቀይርላቸው ሳይሆን ኢትዮጵያውያኑን የበለጠ አንድ የሚያደርግ ነው። በተጨማሪም አፍሪካውያን ራሳቸውን እንዲያዩ የሚያደርግ ነው። በተለይ ደግሞ የምዕራቡ ዓለም አካሄዱ የበለጠ አግጥጦ እየታየ መሆኑን የሚያሳብቅ ነው።

ከዚህ የበለጠ ሪፖርት ሊያወጡ ቢችሉም ምንም መደናገር እንደማያስፈልግ የተናገሩት አቶ እንዳለ፣ ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ ሆነው የቅይጥ ጦርነት አካል የሆነውን ይህን የምዕራቡን የተሳሳተ አጀንዳ መረዳት መቻል አለባቸው ብለዋል። ሪፖርቱን ያወጣው አካል ራሱ ሕገ ወጥ ቡድን ነው። ሪፖርቱ የወጣውም በሕገ ወጥ መንገድ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ለተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ እጅ መስጠት የለባቸውም።

የበለጠ አንድነታችንን በማጠናከር እንዲህ አይነቱን ተራ ትርክት መከላከል መቻል አለብን ሲሉም ጠቅሰው፤ በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በኢትዮጵያ አገራችን ላይ የመጨረሻ የረከሰ ነገር እየተካሄደ ነው ሊሉና ይህን ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ማሳወቅ እንደሚጠበቅባቸው አመልክተዋል። በአሁኑ ወቅት ስለአማራው፣ ስለአፋሩ ጉዳት ማስረዳት ብሎም ከጫፍ እስከ ጫፍ ያለውን የኢትዮጵያውያን ጉዳት ማስታወቅ እንደሚገባ ተናግረዋል። ከዚህ ቀደም በወረረን ጣሊያንና በእኛ ላይ እኩል ማዕቀብ የጣሉብን አካል ነው ዛሬም አሸባሪውን ሕወሓት እና ኢትዮጵያን እኩል ለማየት የሚፈልገውና እዚህ ላይ ንቁዎች ልንሆን ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ ላይ አካሂጀዋለሁ ያለው "የምርምራ ሪፖርት" የተሟላ እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ትናንት ባወጣው መግለጫ ማሳወቁ ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## «ሪፖርቱ» የአሸባሪው ትህነግን ተደጋጋሚ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ ግፍና ወንጀሎችን እንዳሳየ ለማየት የሞከረና ኢፍትሃዊ ነው!

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከፍ ባለ ሕዝባዊነትና ዲሲፕሊን የተገራ ሰራዊት ነው።ይህንን ሠራዊት በሕዝባዊነቱም ሆነ በዲስፕሊኑ ለመክሰስ መሞከር አንድም ሠራዊቱን በሚገባ አለማወቅ ፤ አለበለዚያም ለእኩይ ዓላማ አቅም መግዣ አድርጎ ከመጠቀም መሻት የሚመነጭ ነው።

ሠራዊቱ ለሁለት አስርት ዓመታት በትግራይ በነበረው ቆይታ በቀበሮ ጉድጓድ እየኖረ የሕዝቡን ደሕንነት ከመጠበቅ ባለፈ ፤ ካለችው እያዋጣ ለትግራይ ሕዝብ ጤና ጣቢያዎችንና ትምህርት ቤቶችን ሲገነባ የነበረ ነው።

በየወቅቱም የደረሱ ሰብሎችን ከመሰብሰብ ጀምሮ ጸረ-ሰብል ተባዮች ሲፈጠሩም በመከላከል ስራዎች ውስጥ ከሕዝቡ ጎን በመሆን ሕዝባዊ አጋርነቱን በተጨባጭ ያሳየ ነው። በትግራይ በነበረውም ቆይታም ከትግራይ እህቶቻችን ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ በደም የተሳሰረ ሠራዊት ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በተሰማራባቸው የሰላም ማስከበር ዘመቻዎች ከደቡብ ኮሪያ እስከ ደቡብ ሱዳን የሚታወቀው ከፍ ባለ ሕዝባዊነቱ፣ ዲሲፕሊኑ እና የግዳጅ አፈጻጸሙ ነው። በዚህም የተለያዩ የእውቅና ሰርተፍኬቶችና፣ ሜዳሊያዎችንና ዋንጫዎችን ማግኘት የቻለ ፤ በሰላም ወዳዱ ዓለምአቀፍ ሕብረተሰብ ከፍ ያለ እውቅና የተለገሰውና ዛሬም በዚሁ የሚታወቅ ሠራዊት ነው።

በሕዝባዊ እምቢታ ከሥልጣን የተወገደው አሸባሪው ትህነግ በኃይል ወደ ሥልጣን እመለሳለሁ በሚል ቀቢጸ ተስፋ በሰሜን እዝ ላይ ያደረሰውን ጥቃት ተከትሎም ሠራዊቱ በቡድኑ ለመናገር የሚከብድ ግፍ ቢፈጸምበትም ፤ጥቃቱን ተከትሎ የሚያካሂዳቸው ወታደራዊ ዘመቻዎችም የትግራይን ሕዝብ ደህንነት አደጋ ውስጥ እንዳይከቱ በከፍተኛ ጥንቃቄና መስዋዕትነት ሲያከናውን ቆይቷል።

ይህ ከከአስተሳሰብ መሰረቱ የሚመነጨው የሠራዊቱ ሕዝባዊነት በአሸባሪው ትህነግ ትንኮሳዎች በብዙ ቢፈተንም ሠራዊቱ ፤አብሮት ለኖረው ሕዝብ ያለውን ከበሬታ ዋጋ እስከ መክፈል በሚደርስ ሕዝባዊነት በተግባር አሳይቷል። ለዚህም ከተራ ወታደር እስከ ከፍተኛ አመራር ድረስ መስዋእት ለመክፈል የተገደዱ ጥቂቶች አይደሉም።

የሰው ማዕበልን ታሳቢ ያደረገ ዘመን ያለፈበት ወታደራዊ ስትራቴጂ የሚከተለው አሸባሪው ትህነግ ስትራቴጂው ሊያስከትል የሚችለውን መጠነ ሰፊ እልቂት ታሳቢ በማድረግ ሠራዊቱና የሠራዊቱ አመራሮች የከፈሉት መስዋዕትነት፤ ለትግራይ ሕዝብ በተለይም ለከንቱ ዓላማው ለሚማግዳቸው የትግራይ ሕጻናት፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች እልቂት ለመቀነስ የነበረው አስተዋጽኦ ምን ያህል እንደሆነ ታሪክ የሚዘክረው ትልቁ የሕዝባዊነቱ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

ይህ የሠራዊቱ ማንነት አደባባይ በሞላበት እውነታ ውስጥ አሻባሪው ትህነግ እና የሚጋልቡት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የሠራዊቱን ስም የማጠልሸት ዘመቻ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ሠራዊቱ ጥቃት በተሰነዘረበት ማግስት የታሰበው ሳይሆን ሲቀር ጥቃት ጀምሯል ከሚለው ጀምሮ በዜጎች ላይ ዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽመዋል የሚሉ ጩኸቶች ሲያሰሙ ተስተውለዋል።

የሽብር ቡድኑ አመራሮች "በመብረቃዊ ጥቃት" ጦርነቱን እንደጀመሩ በእብሪት በአደባባይ እየለፈፉ ባለበት ሁኔታ ፤ የጉዳዩ ባለቤት በመሆን ጦርነቱን መከላከያ የጀመረው ለማስመሰል ከፍ ባለ ድምጽ ሲጮሁ ተሰምተዋል ፣ ይህም እኩይ ዓላማችንን ያሳክልናል በሚል ረጅም ርቀት ተጉዘዋል።

ተከሰተ የተባለውን ችግር ለማጣራት የተሰየመው የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በጋራ ባደረጉት ማጣራት የተገኘው ውጤት ግን ችግሩ የተባለለትን ያህል እንዳልሆነ ፤ክሱ የተጋነነና ሠራዊቱን የማይገልጸው መሆኑን፤ የዘር ማጥፋት የሚባል ወንጀል እንዳልተፈጸመም አረጋግጧል።

መንግሥትም የጥናቱን ግኝት በከፊል በመቀበል ማስተካከያ በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ማስተካከያዎችን በማድረግ የወሰዳቸውን እርምጃዎች በግልፅ አስታውቋል፤ በቀጣይም ተመሳሳይ ጥፋቶች እንዳከሰቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለመስራትና ችግሮችን ለማረም ያለውን ቁርጠኝነት በተግባር አሳይቷል።

በዚህም ቡድኑ በሚያካሂዳቸው ትንኮሳዎችም ሆነ በተከታታይ በካሄዳቸው ተጨማሪ ሁለት ጦርነቶች ሠራዊቱ ፍጹም ሕዝባዊነቱን በሚመጥንና ከፍ ባለ ዲሲፕሊን ዘመቻዎችን አከናውኗል። ራሱን ግጭት ከሚያባብሱ ተግባራት ከማቀብ አንስቶ አሸባሪው ቡድን ለፖለቲካ ቁማር የሚፈጥራቸውን አደጋዎች በኃላፊነት በመወጣት ለትግይ ሕዝብ ያለውን የጸና አጋርነት ዳግም አረጋግጧል ።

አሸባሪው ትህነግ ግን የጥናቱን ግኝት ሙሉ በሙሉ አለመቀበሉን በማሳወቅ በተከታታይ በአማራና በአፋር ክልሎች ባደረጋቸው ወረራዎች በተመሳሳይ የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን በማካሄድ ፤ለዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት መርሆዎች ያለውን ንቀት በተጨባጭ አሳይቷል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ሰሞኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የባለሙያዎች ቡድን በሰብአዊ መብት ስም ያወጣው አድሎአዊና ፖለቲካዊ ዓላማን ያነገበ "ሪፖርት" ይህንን የሠራዊቱን ሕዝባዊነት እና ለዲሲፕሊን ያለውን ተገዥነት ከግምት ያላስገባ ፤ የአሻባሪውን ትህነግን ተደጋጋሚ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችንና የዘር ማጥፋት ወንጀሎች እንዳላየ ለማየት የሞከረ ተራ የፖለቲካ ተልእኮ ያነገበ ፤ ሠራዊቱን ለማጠልሸት እየተካሄደ ያለ ሴራ አንድ አካል ነው።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እንኳን በዜጎቹ ላይ ጥፋት ሊፈጽም ቀርቶ ፤በዘር ማጥፋት ወንጀል በማስፈጸም የሚፈለጉ የአሸባሪው ትህነግ ከፍተኛ አመራሮችን ከየተደበቁባቸው ዋሻዎች ውስጥ ከፍ ባለ ሰብአዊነት አውጥቶ እግር እያጠበ ወደ ሕግ ማቅረብ የቻለ ፤ ለሰለጠነበት ወታደራዊ ዲሲፕሊንና ላነገበው የጸና ሕዝባዊነት ያለውን ተገዥነት በተጨባጭ ያሳየ ነው! ስለሆነም በውሸት ሪፖርት እውነትን መደበቅም ሆነ የኢትጵያን መከላከያ ሠራዊት ሥም ፈጽሞ ማጠልሸት እንደማይቻል ሊታወቅ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የሰብዓዊ መብት የባለሙያዎች ኮሚሽን «ሪፖርት»

## - የፖለቲካ ፍላጎት ማስፈጸሚያ

በየኔነው ስሻው

የአሸባሪው ትህነግ በቅጥፈት የታጀበ የሴራ ጉዞ ከጫካ እስከ ከተማ የዘለቀ ብቻ ሳይሆን፤ ለሴራው ማሳለጫ የሚሆን የሃሰት ጩኸቱን የሚያግዙትና የሚያስተጋቡለት አያሌ አጋሮች በአገር ውስጥም በውጪ አገራትም ያሉት የጥፋት ኃይል ነው። ቡድኑ በትግራይ ሕዝብ ስም ነጻ አውጪ ብሎ ራሱን በመሾም የአንዳንድ ምዕራባውያን አገራትና ታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶችን ተልዕኮ ተሸክሞ ጫካ ሲገባ፤ የተልዕኮው ዳር ማድረሻ አቅም የሚሆነውን ሁሉ የሚያገኘው በህዝቡ ላይ በሚሰራቸው እኩይ ሴራዎች ላይ በመመስረት ከጋላቢዎቹ በሚዘረጋለት ዳረጎት ነበር።

ለምሳሌ፣ የ77ቱ ድርቅ ይህ ደግሞ በአንድ በኩል ትህነግ ቀጠናውን የጦር አውድ በማድረጉ ዜጎች ተረጋግተው ሰብዓዊ ድጋፍ እንዳያገኙ በማድረጉ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ከወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት ወደ አካባቢው የሚላከው ሰብዓዊ ድጋፍ ለትግራይ ሕዝብ እንዳይደርስ እክል በመፍጠር የትግራይን ህዝብ ለከፋ ረሃብ ዳርጎት ነበር። ይሄ ብቻም ሳይሆን ትህነግ የትግራይ ሕዝብ ባለበት ቆይቶ ድጋፍ የሚያገኝ ከሆነ ያቀደው ሴራ እንደማይሰምርለት በማወቁ፤ ከራያ አካባቢ ጀምሮ ህዝቡ ወደ ሱዳን እንዲሰደድ በማስገደድ "የማዕከላዊው መንግስት ለትግራይ ህዝብን ሰብዓዊ ድጋፍ እያደረሰ ባለመሆኑ ህዝቡ ለከፋ ረሃብና ስደት ተዳርጓል" በሚል ማደናገሪያ ወሬና "መንግስት በትግራይ ሕዝብ ላይ ረሃብን እንደ ጦር መሳሪያ እየተጠቀመ ነው" የሚል ቅጥፈትን አሰራጭቷል።

ከውጭ ሆነው የሚጋልቡትና የሚደግፉት ኃይሎችም ምንም እንኳን እውነቱን የሚያውቁት ቢሆንም፤ ዓላማቸው ኢትዮጵያን ማንኳሰስና የኢትዮጵያ መንግስትን ማስወገድ በመሆኑ ይሄንኑ የትህነግ ቅጥፈት በስፋት አስተጋብተዋል። አስተጋብተውም ዝም አላሉም፤ ከፍ ያለ የሰብዓዊ ድጋፍና ገንዘብ እንዲገባለት አድርገዋል። ቡድኑም ይሄን ገንዘብና ሰብዓዊ ድጋፍ ለህዝቡ ሳይሆን ለቡድኑ አቅም ማጠናከሪያና የጦር መሳሪያ መግዣ አውሎታል። አጋሮቹም ለምን ብለው ሳይጠይቁ የቀደመውን ረሃብን የጦር መሳሪያ ትርክት እንደ ገደል ማሚቶ ማስተጋባቱን፤ ድጋፉን በአናት በአናቱ በህዝቡ ስም ማቀበሉን በመቀጠል ተጋግዘው ለስልጣን አብቅተውታል።

ይህ የቀደመ ታሪክና ተግባራቸው በተለይ አሸባሪው ትህነግ ከማዕከላዊው መንግስት ተገፍቶ ወደ ትግራይ ክልል ገብቶ በመከላከያ ሰራዊት የሰሜን ዕዝ ላይ በፈጸመው ጥቃት በአገር ላይ ያለውን ጥልቅ ክህደት ካረጋገጠበት እለት ጀምሮ፤ የረሃብ ፖለቲካውን በትኩረት እየሰሩበት ይገኛል። በዚህ ረገድ መንግስት ለትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ የሚያደርገውን ጥረት ለማስተጓጎል ቢሳናቸው እንኳ፤ ወደ ክልሉ የገባው ድጋፍ ለህዝቡ እንዳይደርስ እና ሽብር ቡድኑ ዓላማ ማስፈጸሚያ እንዲውል በማድረጉ ሂደት ተናብበው እየሰሩ ይገኛሉ።

በዚህም የትግራይ ሕዝብ የሚላክለት ሰብዓዊ ድጋፍ ሳይደርሰው በረሃብ እንዲቀጣና ለከፋ ስቃይ እንዲዳረግ የፈረዱበት ሲሆን፤ በአንጻሩ መንግስት የትግራይ ህዝብ እንዲራብ በማድረግ "ረሃብን እንደ ጦር መሳሪያ እየተጠቀመ ነው" የሚል የጅራፉን አይነት ጩኸት ሲያስተጋቡ ይደመጣሉ።

ለአብነት፣ መንግስት በተለያየ ጊዜና መንገድ ወደክልሉ የሚያስገባቸውን ሰብዓዊ ድጋፎች በነዳጅ እጥረት ምክንያት ለህዝቡ ማድረስ አልቻልንምና ነዳጅ ይግባልን በሚል ሰበብ በመጋዘን አከማችተው ሕዝቡን ሲያሰቃዩ ታይቷል። መንግስትምቀደምሲል በክልሉ በመጠባበቂያነት ካስቀመጠው ነዳጅ በተጨማሪ ነዳጅ እንዲደርስ እየሰራ ባለበት ወቅት፤ ያለ ጦርነት መኖር የማይችለው አሸባሪው ትህነግ ለጦር ጉዞው ማሳለጫ እንዲሆን ከተከማቸው ነዳጅ ከ570ሺ ሊትር በላይ አንስቶ ሲወስድ የተከዱ የመሰላቸው ተባባሪዎች ትህነግ ነዳጅ ዘረፈ ሲሉ ባወጡት መግለጫ ቀድሞውንም ሰብዓዊ ድጋፉ ያልደረሰው በነዳጅ እጥረት ሳይሆን በአሸባሪው ትህነግና ተባባሪዎቹ የሴራ ትስስር ምክንያት የትግራይን ሕዝብና የፌዴራሉን መንግስት ለማቃቃር ባላቸው ጽኑ መሻት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር አደረጉት።

ይሄ መንገዳቸው የከሸፈባቸው አሸባሪው ትህነግ እና ተባባሪዎቹ ታዲያ ከሰሞኑ ሌላ አጀንዳ በተጠባባቂነት ካስቀመጡበት ይዘው የሰብዓዊ መብት የባለሙያዎች ኮሚሽን "ጥናት ሪፖርት" በሚል ብቅ ብለዋል። "ሪፖርቱ" እንደ ቀደሙቱ ሁሉ የፖለቲካ ፍላጎት ማስፈጸሚያ ሆኖ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነው። ይሄን የኮሚሽኑ "ሪፖርት" የኮሚሽኑን ወገንተኝነት እና የተሰጠውን ፖለቲካዊ ተልዕኮ ለማሳካት በሚያስችለው መልኩ ስለመዘጋጀቱ ከሚያረጋግጡ ነጥቦች መካከል፤ የመጀመሪያው፣ "ሪፖርቱን" ያዘጋጀው ኮሚቴ የተቋቋመው ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸውን አገራት እና ተቋማት ጥቅም ለማስጠበቅ መሆኑ ሲሆን፤ ይሄም ሉዓላዊት በሆነች አገር እና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት የተፈረጀን የሽብር ቡድን "የትግራይ ኃይሎች" "የትግራይ ሰራዊት" በሚል የክብር ስም መጥራቱ ነው።

ሁለተኛው ነጥብ፣ ኮሚቴው ይህን "ሪፖርት" ሲያዘጋጅ ጥናቱ ከሚከናወንባት አገር ኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ አከናወንኩ ማለቱ ነው። ይህ ደግሞ ሽብርተኛ ቡድኖች በሚፈነጩባቸው አገራት ሳይቀር በቦታው እየተሄደ የሚሰራን ጥናት በኢትዮጵያ ሲሆን በርቀት እንዲከናወን ማድረጉ፣ ያውም ሊጠቀስ የሚችል የመረጃ ምንጭ ሳይዝ መፈጸሙ፤ በድምዳሜውም የአሸባሪውን ትህነግ ዘርፈ ብዙ ሰብዓዊ ጥቃቶች በወታደራዊ ስነ-ምግባሩ፣ በግዳጅ አፈጻጸም ብቃቱ፣ በህዝባዊነቱ እና በተላበሰው የወገናዊነት ባህሪው ተደጋጋሚ ዓለም አቀፍ ምስጋና እና እውቅና ሲቸረው ለቆየው ለኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት መስጠቱ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው ሶስተኛው ነጥብ፤ የሽብር ቡድኑን ሀሰተኛ መረጃዎች ስታስተጋባ የቆየችው የባለሙያዎች ምርመራ ቡድን አባሏ ካሪ ሙሩንጊን በኮሚሽነርነት መመደቧ ሲሆን፤ ሴትየዋ ቀደም ባሉት ጊዜያት በሽብር ቡድኑ ሲሰራጩ የነበሩ ሀሰተኛ መረጃዎችን በማሰራጨት አጋርነቷን ስትገለጽ መቆየቷን ከግል የቲውተር አካውንቶቿ የተገኙት መረጃዎች መጠቆማቸው ነው። ከዚህም በላይ ቀደም ሲል በተመድ የሰብዓዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽን እና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በጋራ የተጠናውን የጥናት ውጤት እና ምክረ-ሃሳብ ለመጠቀም ፈቃደኛ አለመሆኑ የተልዕኮ ተሸካሚነቱን የሚያረጋግጥ ነው።

በተመሳሳይ መንግስት በጋራ ኮሚሽኖቹ የጥናት ምክረ-ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ያቋቋመው የሚኒስትሮች ግብረ ሃይል የምርመራ እና የክስ ኮሚቴ በአማራና በአፋር ክልሎች ያከናወነውን ጥናት እና ያገኘውን ውጤት እንዲሁም ያስቀመጠውን ምክረ-ሃሳብ በግብዓትነት ለመጠቀም ፈቃደኛ ስላለመሆኑም መረጃዎች ያሳያሉ። በአንጻሩ፣ በትግራይ ክልል ተፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲያረጋግጡለት በመረጃ ምንጭነት የተጠቀማቸው ሰዎችም የሽብር ቡድኑ አባላት፣ ታጣቂዎች፣ ፖለቲካዊ አመራሮች፣ ችግሩ ከመፈጠሩ አስቀድሞ ጭምር የፌዴራል መንግስትን ሉዓላዊ አገራዊ ስልጣንና ኃላፊነት በማጣጣልና በማዛባት ጭምር ለሽብር ቡድኑ ድጋፍ እና ከለላ ሲሰጡ የነበሩ ካድሬ የህክምና ባለሙያዎች፣ በክልል በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራሮች እና ስመ መምህራን ናቸው።

ለምርመራውም ትክክለኛ የመረጃ ምንጮችን ሳይጠቅስ ከታማኝ ምንጮቼ ባሰባሰብኩት አስተማማኝ መረጃ በሚል የተለመደ የማወናበጃ ስልት መጠቀሙ የኮሚሽኑን ገለልተኝነትና ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ የከተተ "ሪፖርት" ስለመሆኑ ያመላከቱ ሃቆች ናቸው።

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የእሾህ ብዕረኞች

**ለደጋጎች ግብረ መልስ፤**

"የዓለም ሥልጣኔ መሠረት የተቀረጸው በብዕር ቀለም ነው። የዓለማችን የጥፋትና የጦርነት ታሪኮች የተበጠበጡትም በብዕር ቀለም አማካይነት ነው።" ዘመን ያሸበተው ይህ ዝነኛ "አረጋይ" ብሂል የተሸከመውን የገዘፈ እውነት በተመለከተ በብዙ አቅጣጫ መፈተሽ ይቻላል። መልካም ጥበባትን፣ ምርምራቸውን፣ እውቀታቸውንና ግለ ታሪኮቻቸውን በአግባቡ ሰንደው እና ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ተርጉመው በጽሑፍ ላቆዩልን ባለ ወርቃማ አእምሮዎች (Beautiful Minds እንዲሉ) ታሪክ ባለመታከት ሲያመሰግናቸው እንዲኖር አደራችንን እናስተላልፋለን።

ምሥጋናችንን ለማቅረብ ግድ ያለን የኖሩበትን ዕድሜ አስልተው ብቻም ሳይሆን ከፊታቸው ላለው ትውልድና ዘመን ጭምር ግድ ብሏቸው እውቀታቸውን ያለስስት፣ ጥበባቸውን ያለንፍገት ላስተላለፉልን ደጋጎች ብቻም አይደለም። ዛሬም በእኛይቱ ጀንበር መሰል የጽሑፍ ቅርሶችንና ሰነዶችን በማቆየቱ ሕያው ተግባር አድካሚ ኃላፊነታቸውን በትጋት እየተወጡ ያሉ በርካታ "የአፍቃሬ በጎነት" ባለ ብእሮች በዓለማችን ላይ እንደ ከዋክብት እያበሩ ስላሉ "በእጅ የያዙት ወርቅ ከምንትስ ይቆጠራልን" ብሂል እንዳያስተርትብን እነርሱንም "አሹ!" ብሎ ማበረታታቱ ግድ ይላል። ብዕራቸው ይለምልምልን፤ አክብሮታችንም ይድረሳቸው።

**በእሾህ ብዕር ደም ጠቃሾች፤**

ብዕራቸውን ለእውነት፣ ቀለማቸውንም ለውበት ያዋሉ ጸሐፍት የመብዛታቸውን ያህል፤ በአንጻሩም በተቃርኖ የቆሙ የእሾህ ብዕረኞችንም ዓለማችን "አምጣ ወልዳለች።" ምድራችን ሰላም አግኝታ እፎይ እንዳትል በጽሑፋቸው አማካይነት እየደነቋቆሉ እንደምን እያስነከሷት እንዳሉም እለት በእለት የምናስተውለው ሐቅ ነው። እውነትን አዛብተው፣ ታሪክን አፋልሰው፣ አምባገነንነትን ሰብከውና ሁከትን ቀስቅሰው በሰው ልጆች እልቂት ደስ በመሰኘት "በዋንጫቸው ውስጥ ደም እየሞሉ ቺርስ!" በመባባል በፌሽታ የተሳከሩ የዓለማችን ፀሮች ቁጥራቸውም ሆነ ሥራዎቻቸው ተዘርዝሮ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ "ትዝብታችንን በማውረስ" ጊዜ ይግለጠው ብሎ ማለፉ ይቀላል።

ሰፊውን ምልከታችንን ሰብሰብ አድርገን በአገራዊ መሰል ችግሮቻችን ዙሪያ ትኩረት መስጠቱ ይበጅ ስለመሰለን ስለኛዎቹ "የቤት ውላጅ የእሾህ ብዕረኞች" ጥቂት ሃሳቦችን እንፈነጣጥቅ። ሕወሓት የአገሪቱን ሀብት አጋብሶ ለማዳከም በኋላም ለአካባቢ መሬቶች ቅርምትና ለጦርነት ዝግጅት ዳር ዳር ከማለቱ ቀደም ብሎ በትጋት ሲሰራ የኖረው በእሾህ ብዕረኞቹ አማካይነት የክፋት ሴራውን በማስረጽ ውጊያ መክፈት ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ስትራቴጂው በሚገባ ግቡን እንደመታለት በውጤቱ ማረጋገጥ ይቻላል።

ሕወሓት ከውልደት እስከ እድገቱ፣ ከልጅነት እስከ ጉልምስናው የኖረውና ምናልባትም አብሮት ሊቀበር የሚችለው "ከእኔ ወዲያና ከእኛ ወዲያ ላሳር" የሚለው ትዕቢቱና ትምክህቱ በዋነኛነት የሚጠቀስለት "ሌጋሲው" እንደሆነ ለማመን አይከብድም። ይህንን የክፋት አስተሳሰቡን ሲዘራና ሲበትን የኖረው የእሾህ ብዕር አስጨብጦ ባሰለፋቸው "ሠራዊቱ" አማካይነት ነበር። ዛሬ ዛሬ ደግሞ የዕሾህ ብዕረኞቹን ፈለግ የሚከተሉ የማሕበራዊ አሜከላዎችን በዓለም ዙሪያ በትኖ ይህንኑ አገርንና ሕዝብን የማተራመስ፣ የማድማትና በታሪክ እውነታዎች ላይ የመዘባበት ተልዕኮውን አጠናክሮ ገፍቶበታል። ከጦር ሜዳው ባልተናነሰ ፍልሚያ ጎን ለጎን

> ሕወሓትና ብዕረኞቹ በዚህ ጉዳይ ብርቱ መሆናቸውን ባንመሰክር ከእውነት እንጋጫለን፡፡ ሀሰተኞች ገንነው ሲወጡ እውነትን የያዙት ለምን ዓይናፋር ሆነው "ከራስ በላይ ነፋስ" በሚል ፍልስፍና ሕይወታቸውን ለመምራት እንደወሰኑ ምክንያቱን ለመግለጽ "እነርሱን መሆን" ግድ ይላል

የተከፈተብን ጦርነት ቀደም ሲል በብዕር ዛሬ ደግሞ በማሕበራዊው ሚዲያ መሆኑን አንባቢው ልብ ይበል።

"ብዕራቸውን ለከፋፋይነት" በመጠቀም የመጻሕፍት ገጾቻቸውን ኢትዮጵያን ለማሳነስ ቢቻልም ለማዳከም በትጋት ሲሰሩ የኖሩት ጥቂት የማይባሉት የዘመናችን አፍቃሬ ሕወሓት ጦማሪዎች "የደረሷቸው" በርካታ ጥራዞች የተለወሱት በዘመን ተሻጋሪ ከፋፋይ መርዞች ቀለማቸው እየተበጠበጠ ነበር። ለማሳያነት እንዲረዳም ሁሉንም መሰል መጻሕፍት ሊወክል የሚችለውን አንድ መጽሐፍ ብቻ ለማሳያነት እንጥቀስ።

የመጻሐፉ የተሳከረ ርዕስ "ዘረኛው ማነው? ኢትዮጵያዊያን ፍረዱ! ሁለት ሺሕ ዓ.ም ሚሊኒዬም - ኢትዮጵያ " የሚል ሲሆን ደራሲው በተለያዩ ርዕሶች የጻፏቸው ሌሎች ጠቃሚ መጻሕፍትም መኖራቸውን ሳናስታውስ አናልፍም። ይኼኛው መጽሐፍ ግን በመልካም አዝመራ ውስጥ የበቀለ እንክርዳድ መሆኑን የምንተቸው መልካሞቹን በመዘንጋት ያለመሆኑ ይታወቅ።

መጽሐፉ በወቅቱ "አንቱታን ባተረፉ" የግዜው ሹመኞች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶትና አድናቆት ተችሮት በተመረቀበት ዕለት በቦታው በመገኘት የዓይን እማኝ ለመሆን እድል አግኝተን ነበር። በመጽሐፉ ላይ የተሰጡትን ግምገማዎችም ልብ ተቀልብ ሆነን ተከታትለናል። ይዘቱንም ከዳር እስከ ዳር ለማንበብ አልሰነፍንም። በዚሁ የመጽሐፍ ምረቃ ላይ የተገኘው ሌላው የሙያ ባልደረባችን የመጽሐፉን ገጾች ገለጥ እያደረገ ይዘቶቹን በመቃኘት ላይ እያለ፡- "ይድረስ ለትምክህተኛ ሁሉ፤ እንደ መግቢያ" የሚለውን መንደርደሪያ እንዳየና "ዘረኝነት ሲባል ምን ማለት ነው?" የሚለውን የምዕራፍ 3 ክፍል ፈጠን ብሎ ካነበበ በኋላ በድፍረት የተገለጹት ክፉ ሃሳቦች እጅግ አስቆጥተውት "በእምባ ቀረሽ" ቁጭት እየተብሰከሰከ ፈጣሪን ለፍርድ የተማጸነው እዚያው አጠገቤ እንደተቀመጠ ነበር።

የዚህ መጽሐፍ አስኳል ሃሳብ የሚከተለው ነው። "ሕወሓት - ኢሕአዴግ ዘረኛ የተባለው የክልል መንግስታትን ቋንቋን መሠረት አድርጎ በመስራቱ ነው? ወይንስ ሌላ ተጨማሪ ያልተለመደ ባሕሪ ጨምሮበታል? ለምንስ አስፈለገ? በድሮው እንደነበር ቢቀጥል አይሻልም ነበር ወይ? ይህ አካሄድ ዘረኝነትን ያስፋፋል፣ ያጋጫል፣ ያራርቀናል፣ ያጣላናል፣ አገሪቷ ወደማትወጣው አዘቅት ሊከታት ይችላል፤ የሚሉ ወገኖች አሉ። ዕውነት ግን ያጣላል፣ ያራርቃል፣ ወይንስ ያቀራርባል፣ ያፋቅራል?" በማለት መደላድሉ ከተመቻቸ በኋላ ጸሐፊው የአገሪቱን በርካታ ብሔረሰቦች ስም በጥላቻ እየጠቀሱና በተለይም በአንደኛው የትግራይ ተጎራባች ክልል ላይ ጫን በማለት "የጭቃ ጅራፋቸውን" እንዴት እንደሚያጮኹ ገጾቹን ገልጾ ማንበብ ይቻላል፤ (ከገጽ 85 ጀምሮ)።

መጽሐፉ ገና ከመግቢያው ጀምሮ የአገሪቱን ቀደምት መሪዎች፣ የታሪክ ባለሙያዎች፣ የታላላቅ ሰዎች ንግግሮችንና ቀደምትና የወቅቱን ደራስያን በስምና ሥራዎቻቸውን እየጠቀሱ ደራስያኑን እያንቋሸሹ የሚሰድቡበትን ቋንቋና ገለጻ ደግሞ ማስታወሱ "ከሰደበኝ መልሶ የነገረ ገደለኝ" መርህን መጣስ ስለሚሆን ወደ ጥልቅ ይዘቱ በመግባት መሄሱ እጅግም ረብ አይኖረውም።

መቼም የሕወሓት ግልጽና ድብቅ ተልዕኮ አገሪቱን እንዴት አሽመድምዶ ዛሬ ለደረስንበት መከራ እንደዳረገን በብዙ ማስረጃዎች እያመላከትን ባለመሰልቸት ስንጽፍ መክረማችን ይታወሳል። በተለይም የዘመን ተሻጋሪነት ባህርይ ባለው የጽሑፍ ጥበብ ታሪክን እያዛቡና እውነታን እያጣመሙ የሕዝቦችን የአብሮ መኖር ተፈጥሯዊ ባህርይ በእሾሃማ ብዕር በማጠር ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ወንጀልን መፈጸም ይቅር የማያሰኝ ተግባር መሆኑ ለማንም ይጠፋል ተብሎ አይታመንም።

ሕወሓት ይሉት "የሞት መላዕክ" በአገሪቱ ታሪክ፣ በነባራዊ እውነታዎችና በሕዝቦች ሥነ ልቡና ላይ ሲፈጽም የኖረው የከፋ በደል ከመላው ሕዝብና በተለይም ከአብዛኛው የትግራይ ሕዝብ አዕምሮ ውስጥ ተጠርጎ እስኪወጣ ድረስ ምን ያህል ጥረትና ዓመታት እንደሚያስፈልግ ለግምት እንኳን አዳጋች እንደሆነ መገመት አይከብድም።

በተደጋጋሚ በዕብሪት በወረራቸው አካባቢዎች ቀብሯቸው የሄደው አውዳሚና ተቀጣጣይ ፈንጂዎችን በተመለከተ፤ ክብር ለመከላከያ ሠራዊታችን የመሃንዲስ ባለሙያዎች ይሁንና ጥንቃቄ በታከለበት ወታደራዊ ግዳጅ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከተቀበሩበት ቦታ እየተለቀሙ መጽዳታቸውና መክሸፋቸው የማይቀር ነው። ነገር ግን በአጠቃላይ በአገሪቱ ዜጎች በተለይም በትግራይ ሕዝብ አእምሮ ውስጥ በተበከለ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት የታጨቀው ክፉ አስተሳሰብ በምን ያህል ዘመናት ታጥቦ እንደሚጸዳ ለመገመትም ሆነ ለማሰብ በእጅጉ ይፈትናል።

የፈተናው ክብደትና ውስብስብነት የሚናቅ ባይሆንም የአገሪቱ የታሪክ ባለሙያዎችና ደራስያን እስከ ዛሬ በህትመት ዘዴ ተሰራጭተው በሕዝብ አእምሮ ውስጥ የተነሰነሱትን መርዛማ የሕወሓት ታሪኮችና ትርክቶች በእውነታና በማስረጃ ለመሞገት ቁርጥ ውሳኔ በማድረግ ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል። ለዚህ ተልእኮ ተፈጻሚነትም መንግሥትና ያገባናል የሚሉ ተቋማት የታሪክ ተመራማሪ ምሁራኑንና ደራስያንን በቅርበት ሊያግዟቸውና ሊያደፋፍሯቸው ይገባ ይመስለናል።

በፈራ ተባ እየታለፈ ያለው የታሪክ ውይይትና ክርክር ጉዳይም ከምንም በፊት ትኩረት ተሰጥቶበት ወደ ተግባራዊ ዘመቻ መግባት እስካልተቻለ ድረስ ጓያ እንደሰበረው ምስኪን ሰው "በቆይ ብቻ" እየፎከሩ ጊዜ ማባከን በዚህ ጸሐፊ እምነት ድክመት ብቻ ተብሎ የሚታለፍ ሳይሆን ታሪክንና እውነትን ከመበደል ተለይቶ ሊታይ አይገባውም።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በርካቶቹ ዩኒቨርሲቲዎቻችን የታሪክ ክፍላቸውን በመዝጋት የመምህራኑን ልብና መንፈስ ሲሰብሩና ተማሪዎች የታሪክ ትምህርትን ልክ እንደ አንድ አስፈሪ መንፈስ እንዲሸሹት ባደረጉበት ወቅት በዚሁ ጋዜጣ ላይ የመረረ ጩኸታችንን ማስተጋባታችን አይዘነጋም። ያ ቸልተኝነት የሚያስከትለው ውጤት በቅርብ የሚገለጽ ሳይሆን ከዓመታት በኋላ ፍሬ አፍርቶ መመልከታችን አይቀርም።

አሁንም ቢሆን ጊዜው አልመሸም፤ "የኢትዮጵያ ታሪክ ስንል የቱን ማለታችን ነው?" የሚለው ጉንጭ አልፋ መከራከሪያ ጥርት ብሎ ወደ እውነቱ መቃረብ ይኖርበታል። በቃል ሙግት ብቻ የሺህ ዓመት ዕድሜ አለው የምንለውን ታሪካችንን "በአሉ ተባባሉ" እያጎላን ጮክ ብለን በመናገር፤ በጽሐፋችን ግን አይናፋርነታችን ጠንክሮ "እነ አከሌ ምን ይሉናል?" የምንል ከሆነ ጠቡ ከታሪክና ከእውነታ ጋር ብቻም ሳይሆን ህሊናንም ይጨምራል። እትትት እያሰኘ ድፍረታችንን ቆፈን ካስያዘው ፖለቲካ ተላቀን ነፃ እስካልወጣን ድረስ ቸል ያልነው የታሪክ እውነታ እንደሚፈርድብንም ማሰቡ አይከፋም። ለዩኒቨርሲቲዎቻችንና የትምህርት ሥርዓቱን ለሚመሩ ሹመኞች ቀደም ሲል የሰጠነውን ማሳሰቢያ ደግመን ማስታወሱ አግባብ ይመስለናል።

ሕወሓት የራሱን ትርክት በራሱ የእሾህ ብዕረኞች እያጣደፈ ይጽፍና ያጽፍ የነበረው በፌዴራል ከፍተኛ የትምህርት ሥርዓቱ ላይ ይህንን መሰል መሰሪ ስልት ለመተግበር እንደነበር ዛሬ በሚገባ እውነቱ እየተገለጠ መጥቷል።

ብዙ የታሪክ ምሁራንና ደራስያን ያፈጠጠውን የሕወሓት ተንኮልና ሴራ እያስተዋሉ "ምንትስን ምን አገባው ከእርሻ" በሚል ፈሊጥ ራሳቸውን ሸሽገውና ሰውረው "ክፉን ቀን እንደ ቅዝምዝም ዝቅ ብለው ለማሳለፍ" መሞከራቸው ፀሐይ የሞቀው እውነታ ነው። ቀላሉ ማሳያ በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ታሪክ ላይ ደፈር ብለው በየሚዲያው የምናስተውላቸውን ጥቂት ተመሳሳይ ሰዎች ብቻ በማየት እውነቱን ማረጋገጥ ይቻላል።

ሕወሓትና ብዕረኞቹ በዚህ ጉዳይ ብርቱ መሆናቸውን ባንመሰክር ከእውነት እንጋጫለን። ሀሰተኞች ገንነው ሲወጡ እውነትን የያዙት ለምን ዓይናፋር ሆነው "ከራስ በላይ ነፋስ" በሚል ፍልስፍና ሕይወታቸውን ለመምራት እንደወሰኑ ምክንያቱን ለመግለጽ "እነርሱን መሆን" ግድ ይላል።

በመጨረሻም፡- "እሾህን በእሾህ" እንዲሉ በውሸት ሲተረክ የኖረውን የሕወሓት ትርክት ለማርከስ ጊዜውም ሆነ አመቺው ወቅት አሁን ስለሆነ የዘርፉ ምሁራንና የአገራችን ደራስያን ያሸለበውን ብዕራቸውን ቀስቅሰው እውነቱን እየገላለጡ በውሸት የተበከለውን የሕዝባችንን አዕምሮ በተለይም የትግራይ ወገኖቻችንን ሥነ ልቡና ሊፈውሱ ውዴታ ብቻ ሳይሆን የዜግነት ግዴታ ጭምር ነው። ሰላም ይሁን!

# ወቅታዊ

# «ሪፖርቱ የአሸባሪውን ቡድን የተበላሸና የጎደፈ አሰራሩን ለመደበቅ የተዘጋጀ ነው»

**አቶ እንዳለ ንጉሴ**
**የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር**

አስቴር ኤልያስ

**በሰብዓዊ መብት ጥሰት ስም ኢትዮጵያ ላይ የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማስፈጸም በመሯሯጥ ላይ የሚገኙ አንዳንድ የምዕራባውያን አገራት በዓለም አቀፉ ሰብዓዊ መብቶች ኤክስፐርቶች ኮሚሽን መርማሪ ቡድን ያስጠኑትን ሪፖርት ሰሞኑን ይፋ ማድረጋቸው ይታወቃል። ይህ በሰብዓዊ መብት ጥሰት ስም ይፋ የሆነው የሐሰት ድርሰት የአሸባሪውን ቡድን ህልውና ለማራዘም የታለመ ስለመሆኑም የአደባባይ ምስጢር ነው። ይሁንና በመርማሪ ቡድን ይፋ የተደረገው የጥናት ውጤት በሐሰት የታጨቀ ከመሆኑም በተጨማሪ ጥናቱ መከተል የተገባውን ሳይንሳዊ መንገድ ያልተከተለ በመሆኑ በኢትዮጵያ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘ ነው።በተለይ ደግሞ ለአሸባሪው ቡድን አይን ያወጣ ውግንናን ያሳየ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን እጅ ለመጠምዘዝ ሆነ ተብሎ ታቅዶ የተሰራበት መሆኑ ተዓማኒነቱን የሚጎድለው ሆኖ ተገኝቷል።የኢትዮጵያ መንግስት ረሃብን እንደጦር መሳሪያ ተጠቅሟል በሚል በሪፖርቱ ሳይ በማስፈር ውንጀላ ለማቅረብ መፈለጉ ኡኡታውን በማሰማት ሳይ ያለውን አሻባሪ ቡድን ለመታደግ ታስቦ የተቀናበረ መሆኑን አመላካች ነው። ይህን መሰረተ ቢስ ውንጀላ የታጨቀበትን ሪፖርት ምክንያት በማድረግ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ከሆኑት ከአቶ እንዳለ ንጉሴ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል።**



**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈጽሟል በሚል ሰሞኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ይፋ ያደረገውን ሪፖርት እንዴት አገኙት?**

**አቶ እንዳለ፡-** በመጀመሪያ ይህ ኮሚቴ ለምን ተቋቋመ የሚለውን ብናነሳ ጥሩ ይመስለኛል።ምክንያቱም ኮሚቴው የተቋቋመበትን መንፈስ ካላየነው አሁን ያለውን ሪፖርት መረዳት አንችልም።በኢትዮጵያ እንደሚታወቀው የሰሜኑ የአገሪቷ ክፍል አንድ አሸባሪ ቡድን ማለት ኢትዮጵያውያኑን በዘር፣ በኃይማኖት ከፋፍሎ ላለፉት 30 እና 40 ዓመታት አገር ወደማፍረስ ደረጃ የደረሰ ቡድን ነው።በዚህም ብዙ ኢትዮጵያውያን ተጎድተዋል።ሌላው ቀርቶ የአካባቢው አገሮችም ጭምር ተጎድተዋል።አሸባሪው ቡድን በዚህች አገር ላይ ያልሰራው ግፍ የለም ማለት ይቻላል።አገራችንን ከመዝረፍ ጀምሮ፣ ባህሏን ከማንኳሰስ ብሎም ሉዓላዊነቷን ከማጠልሸት ጀምሮ ሲሰራ የቆየ ቡድን ነው።እንዲህ በመሆኑም ይህን አሸባሪ ቡድን ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ ወደ ጥግ አስይዘውታል።

ስለዚህ አሸባሪው ቡድን ከመጀመሪያም ጀምሮ የነጻነት ጥግ የሆነችውን አገር ለማፍረስ ያቋቋሙት ቡድን ስለሆነ እነዚህ ያቋቋሙት አካላት ቡድኑን በቀላሉ አያዩትም።ስለዚህም ነው በ15 ቀን ውስጥ ከተሸነፈበት ጉድጓድ አንስተው እንደገና በእርዳታ እና በሰብዓዊነት ስም ይህንን ቡድን ለማምጣት የሚጥሩት።እሱ ደግሞ ከመጀመሪያውም ጀምሮ ሚዛናዊም አልነበረም።ለዚህ አሸባሪ ቡድን በእርዳታ ላይ እርዳታ በጥቅም ላይ ጥቅም ከማንጋጋት በስተቀር ያንን ሁሉ ግፍ ሲፈጽም እና ኢትዮጵያውያኑን እንደዚያ ሲያዋርድ እና ሲበጠብጥ አንድም ጊዜ ቢሆን እረፍ ሊሉት አልወደዱም፤ ማለትም አይፈልጉም።ቡድኑ ሲቋቋም ጀምሮ ተጽዕኖ እንዲያደርስ የተደገፈው በእርዳታ ስም ነው።አሁንም ይህንን ቡድን ያመጡት በእርዳታና በሰብዓዊ መብት ስም ሲሆን፣ እያቆዩት ያለው በዚሁ ነው እንጂ ቡድኑ ከመጀመሪያው ጀምሮ የዘር ማጥፋት እየፈጸመ የመጣ ነው።ለዚህ ደግሞ ቡድኑ የተቋቋመበትን መርሃግብር ማንበብ ብቻ በቂ ነው።

ኅብረተሰብን ጠላት አድርጎ የፈረጀ ቡድን በመሆኑ የዘር ማጥፋት የሚጀምረው በራሱ ከዚህ ነው።ኢትዮጵያን አፈርሳለሁ ብሎ ሲጀምር ኢትዮጵያን ሲያፈርስ ሕዝብን እንደማፍረስ የሚቆጠር ነውና የዘር ማጥፋት ማለት ይህ ነው።

ይህንን ቡድን ‹ይሁን እስኪ› በሚል ኢትዮጵያውያን ከለውጥ ወዲህ ሰላምንና እርቅን እናድርግ ብለው ለመኑት።ነገር ግን ያቋቋሙት ቡድን ግን የተላከበትን ተልዕኮ ስላልፈጸመላቸው ለእርቁ ፈቃደኛ አልነበሩም።ከዚህም የተነሳ የመጀመሪያው ዙር አላዋጣውም፤ ሁለተኛውም እንዲሁ አልሆነለትም፤ አሁን ደግሞ እንዲሁ ወደሶስተኛው መጥቷል።ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሕግንና ሉዓላዊነታቸውን ለማስከበር ብሎም አንድነታቸውን ለማስጠበቅ መልስ እየሰጡ ይገኛሉ።ይህ ቡድን ደግሞ ከኢትዮጵያውያኑ በተቃራኒው በመቆም ኢትዮጵያን ለማፍረስ፣ ለማዋረድ ብሎም በባህል የሌለ እና ጭካኔ የተሞላበትን ድርጊት በመፈጸም አሁን ያለበት ደረጃ ላይ የደረሰ ቡድን ነው።

ስለዚህ የተፈጸሙት ጉዳዮች ራሱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ (ዩ ኤን ኦቻ) ለማጣራት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጋር ሆኖ በትክክለኛ ዘዴ፣ ሳይንሱን በተከተለ መንገድ፣ መካተት የሚገባቸውን በማካተት በመጀመሪያም እነርሱን ጭምር ደስ ያላሰኘ ሪፖርተሩን ይፋ አድርጎ ነበር።በመሆኑም የእነርሱ ወኪል የሆነውን አሸባሪ ቡድን የወቀሰ ሆነ።የሚፈልጉትን ኢትዮጵያ ላይ ያሰቡትን ነገር አላገኙም።ብሎም የኢትዮጵያን መንግስት ማፍረስ አልቻሉም።በዚህ ደግሞ እነርሱ ደስተኛ አልነበሩም።ስለዚህ እንደለመዱት ሌላ ድርሰት መፈብረክ ነበረባቸው።ስለዚህ ሌላ ጉዳያቸውን የሚያስፈጽምላቸው የሚመለከተውን አካልና ባለድርሻውን ሁሉ ባካተተ መንገድ የተሰራውንና በተወሰነ መልኩም ቢሆን ተቀባይነትን ያገኘውን ሪፖርት ትተው ትልቅ ድርጅት የሆነው ዩ ኤን ኦቻ ያጠናውን እንዲሁም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ያጠናውን በሶስት ሰው ብቻ በተጠና ሪፖርት ተኩት።

ይህ ማለት ደግሞ ሕገ ወጥ የሆነ አካሄድ እንጂ ማንም መብቱን ሰጥቷቸው እንዳልሆነ ነው።ቡድኑ ሲቋቋም ራሱ ሕገ ወጥ የሆነ ቡድን ነው።በመሆኑም አካሄዱ ሕገ ወጥ በመሆኑ እውቅና የሚሰጠው አይደለም።ኢትዮጵያ እውቅና ባትሰጠውም ለሰላም ካላት ፍላጎት የተወሰነ ለማለሳለስ ሙከራ አድርጋ ነበር።ኢትዮጵያ በባሕሪዋ ለዲፕሎማሲ ቅድሚያ የምትሰጥ አገርም ስለሆነች ነው።

ነገር ግን ቡድኑ የጭካኔ በትሩን ከመምዘዝ ወደኋላ አላለም።ልክ እንደ አሸባሪው ሕወሓት ይህ የተቋቋመው ኮሚቴ ስራው ያው ነው።ይህ የተቋቋመው ኮሚቴና አሸባሪው ሕወሓት የሚሰሩት ስራ አንድ አይነት ነው ማለት ይቻላል።በተለይ ደግሞ ዋና ስራቸው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እና አንድነት ማናጋት ነው።

ስለዚህ ሪፖርት ገና ሲጀምር እንኳ አስተውለሽ ከሆነ ሕወሓትን ያስቀመጠበት መንገድ በጥንቃቄ ነው።ለምሳሌ ሪፖርቱ ላይ የኢትዮጵያ መንግስትና አጋሮቹ ይላል።በተጨማሪም በአሸባሪነት የተፈረጀውን ሕወሓትን የትግራይ መንግስት ይላል።ሕወሓት ደግሞ አሸባሪ ቡድን እንጂ የትግራይ ክልል መንግስት አይደለም።የትግራይ መንግስት ሕወሓት በተቋቋመበት ጊዜ እንኳ የፈረሰ ቡድን ነው።ስለዚህም ኢትዮጵያ ያቋቋመችው የክልሉ መንግስት ሌላ ነው።ሕወሓት በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሸባሪ ቡድን ነው ተብሎ የተፈረጀ በመሆኑ ሪፖርቱ ማስቀመጥ ያለበት አሸባሪ ብሎ ነው።ስለሆነም ማስቀመጥ ያለበት መንግስት ባስቀመጠው አግባብ ነው።እሱ የሕወሓትን ስም መቀየር አይችልም።ሕጉ አይፈቅድለትም።በዚህ ሪፖርት ሊያስተካክሉ የፈለጉት የአሸባሪውን ቡድን ስም ጭምር ነው ማለት ይቻላል።

በመጀመሪያ ራሱ አንድ ኢትዮጵያውያን ፈቅደው ያቋቋሙትን መንግስትና አንድ አሸባሪ ቡድንን እኩል ማየቱ በራሱ አግባብነት የሌለው ነው።ይህን ማድረግ ያስቻላቸውስ የትኛው ሚዛን ነው ብሎ መጠየቁም ተገቢነት ያለው ነው።ሰሞኑን እየተደረገ ያለው ነገር የሚያሳየው በግድ እኩል ለማድረግ ያለውን ጥረት ነው።ይህ ደግሞ በጣም የጭካኔ መንገድ ነው።ምክንያቱም አሸባሪው ያንን ሁሉ ያጠፋውን በደልና ግፍ እያዩና ያሰቃየውን የኅብረተሰብ ክፍል እየተመለከቱ ለዚህ ጨካኝ ቡድን እውቅና እንደመስጠት የሚያስቆጥር ነው።

ይህን ሪፖርት ያዘጋጀው የጥናት ቡድን ከመጀመሪያው ጀምሮ በራሱ ሕገ ወጥ ነው።ተጠባቂ ስራዎቹም ሕገ ወጥ ናቸው።እንዲያው በአጋጣሚ እንኳን ጥሩ ነገር አድርገው ቢሆን (በእርግጥ እነርሱ ጥሩ ነገር ያደርጋሉ ብዬ አልልም) ተቀባይነት ያለው አይሆንም።በአሁኑ ሰዓት በራሱ ኢትዮጵያ ከሌላው አካል ጋር ሆኖ እያስጠናችው ያለው ጥናት አለ።ተዋክበው ይህንን ሪፖርታቸውን ይፋ ያደረጉት ያንን ሪፖርት ለመቅደም በመፈለጋቸው ነው።በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ከተከሰተው ግጭት ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ ወንጀሎችን አስመልክቶ ሲካሄድ የነበረው የምርመራ ሒደት ይፋ ከመደረጉ በፊት ለመቅደም ነው የሐሰት ድርሰታቸውን ተሽቀዳድመው ያወጡት ማለት ይቻላል።ስለዚህ አካሄዳቸው በራሱ በዚህ ልክ የተደራጀ ከመሆኑም በተጨማሪ እየተሰራ ያለውም በባለሙያዎች ሆን ተብሎ እንደሆነ ያመላክታል።እነርሱ በቤታቸው የኢትዮጵያ ከመውጣቱ በፊት መሽቀዳደማቸው ነው። አሳዛኙ ነገር አንደኛው ሙያዊ አካሄድን የተከተለ አለመሆኑ ነው።ግዴታውንም ያልተወጣ ነው።ይህ ጥናት ዩኤን ኦቻ የሚባለው የተባበሩት መንግስታት ራሱ ምን ያህል የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዞች ሰለባ እንደሆነ ያሳየበት ስራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሪፖርቱ የተካሄደው እርስዎም እንዳሉት ትክክለኛውን የጥናት መስፈርት ተከትሎ አሊያም ሳይንሳዊ የሆነ መንገድ ተከትሎ አይደለም፤ አጥኚዎች ነን ያሉት አካላት ዩጋንዳ ተቀምጠው በስማ በለው ያገኙትን መረጃ ሰብስበው ነው አጠናን ያሉትና ይህ አካሄዳቸው በራሱ ጥያቄ ውስጥ አይጥላቸውም?**

**አቶ እንዳለ፡-** በኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ ያለው ነገር ቅይጥ ጦርነት ነው።ከዛ በፊት ግን ኢትዮጵያውያንን የሚከፋፍል እና የሚነጣጥል ስራ በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያውያኑን በኢኮኖሚውና በሌላም ሌላ የሚያዳክም ስራ ከተሰራ በኋላ የመጨረሻው ዱላ ሊመጣ ይችል ነበር።ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ንቁ ስለሆኑ ነው ከመጀመሪያ ይህንን የተከላከሉት።ስለዚህ ይህ ሪፖርት ለእኔ የቅይጥ ጦርነቱ አካል ነው።ለምሳሌ ይህን ሪፖርት የምቆጥረው ሮይተርስ ወይም ደግሞ ቢቢሲ አሊያም ሲኤን ኤን እንዳወጣው ነው።እነዚህ በሙሉ ደግሞ ከዛ ቡድን ጋር ለ40 ዓመታት ሲዘርፉ የቆዩ ናቸው።ኢትዮጵያ የነጻነት ቀንዲል መሆኗ የማይመቻቸው፣ የኢትዮጵያ ነጻነት ሌሊትና ቀን የሚያባንናቸው ቡድኖች ናቸው።

ስለዚህ ይህ ይፋ የተደረገው ሪፖርት እንደሪፖርት ሊቆጠር አይችልም።ምክንያቱም አንደኛ ሳይንሳዊ ዘዴን አልተከተለም፤ ሁለተኛ ደግሞ መሳተፍ የሚገባቸውን

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



> **ይ**ህ አሸባሪው ቡድን ሲዘርፍ አይናቸው ያያል፡፡ ነዳጁን፣ ዘይቱን፣ ስንዴውን ከነመኪናው ጭምር ሲዘርፍ አንዱ ላይ እንኳን ስለዘራፊነቱ አላነሱም፡፡ እንዲያውም ከምስረታው ጀምሮ እርዳታን፣ ረሃብን እንደጦርነት የተጠቀመው ቡድን ቢኖር ሕወሓት ነው፡፡ አሁንም ራሱ ሕወሓት በእርዳታ ስም የተቋቋመና በእርዳታ ስም ጦርነት እያካሄደ ያለ ቡድን ነው

ባለድርሻ አካላት አልተሳተፉበትም።በሶስት ሰው የተሰራ ሪፖርት የ120 ሚሊዮን ሕዝብ አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ አይመጥንም፤ በአፍሪካ ትልቋን ኢትዮጵያ፣ በአጠቃላይ ነገሯ ስትወሰድ ደግሞ በአፍሪካ ቀዳሚ የሆነችውን አገር እንዲሁም ጂኦፖለቲካዊው ድርሻዋ ከፍ ያለችውን አገር እንዴት በእነዚህ ሶስት ሰዎች ልትወከል ትችላለች የሚያሰኝ ነው።ይህ በምንም ተዓምር ሊሆን የማይችል ነገር ነው።ይህ ይፋ የተደረገው ሪፖርት የትኛውንም ሪፖርት እንኳን እንደግብዓት መጠቀም ያልፈለገ ነው።የትኛውም ሪፖርት ያላለፈውን ነገር እንደመነሻ የሚወሰድበት ሁኔታ አለ፤ ይህ ይፋ የተደረገው ሪፖርት ግን ይህንን ማድረግ አልፈቀደም።ይህ ማለት ቀደም ሲል ራሱ ያጠናውንም ሪፖርት እንደመነሻ መጠቀም አልፈለገም።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ ይህ ፍላጎቱ ምንን ለማሳየት ነው ይላሉ?**

**አቶ እንዳለ፡-** በአጠቃላይ ሆነ ብሎ ስህተትና ሰበብ ፈልጎ ያንን የተጨማለቀ ቡድን ለመደገፍ የታቀደ ነው።ሪፖርቱ የዚያን የአሸባሪውን ቡድን የተበላሸና የጎደፈ አሰራሩን ለመደበቅ የተዘጋጀ ነው።ምክንያቱም ሕወሓት እንደ አሸባሪ የሚሰራውን ስራ ኢትዮጵያውያንን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አጋልጠውታል።ይህ ማለት በተዘዋዋሪ እነርሱም አሉበት ማለት ነው።ያሉበት መንገድ ደግሞ አቅጣጫ በመስጠት ይመሩት ነበር።የፋይናንስ አቅርቦት ያደርጉ ነበር።ይህ በመሆኑም እነርሱም የተቀመጡት በመሸማቀቅ ነው።ስለዚህ ይህንን ሸክም ወደሌላው መውሰድና ማላከክ ይፈልጋሉ።ይህንን ደግሞ ኢትዮጵያውያኑ በፍጹም የሚቀበሉት አይሆንም።የዓለም አቀፍ ማህበረሰብም ይህንን አይቀበልም።ጉዳዩ ከሳይንስም ከሞራልም ውጪ ነውና።በአጠቃላይ ይህ ሪፖርት ዩኤን ኦቻ የሚባል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በፍጹም ሊወክል የሚችል ነገር አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- ሪፖርቱ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስብሰባ ቀድሞ እንዲወጣ የተደረገበት ዋናው ዓላማ ምን ይሆን?**

**አቶ እንዳለ፡-** ለእኔ ሪፖርቱን በየትኛውም ሰዓት ቢያወጡት የተለየ አይደለም።በእርግጥ አንቺ እንዳልሽው የተመድ ስብሰባ አለ።ከዛ ጋር ተያይዞ የተወሰነ ጫና እናድርግ በሚል ነው። እሱ ግን ያለቀለት ጉዳይ ነው።ኢትዮጵያውያኑ ቀድመው ጉዳዩን ጨርሰውታል።በአሁኑ ሰዓት የሚመለስ ነገር የለም።የእነርሱ ተስፋ አለመቁረጥ ነው እንጂ ይህን ሪፖርት በማውጣት የሕወሓት ቡድንን ማዳን አይችሉም።እነርሱ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሱትን ስህተት ማረሳሳት አይችሉም።በአሁኑ ሰዓት እየሸሹ ያሉት ከራሳቸው ነው።እንደዚያ ካልተባለ ያንን እርዳታ እስከ ጉድጓድ የወሰዱለትን መሳሪያ እስከ ጉድጓድ ያደረሱለትን ቡድን እንዲወቅስባቸው አይፈልጉም፤ ይሁንና ከጀርባቸው ያሉት እነርሱ ናቸው፤ ነገር ግን በዚህ አይነት አካሄድ እነርሱን ማዳን አይችሉም።አሁን በተወሰነ መልኩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሚሰበሰብበት ጊዜ የተወሰነ ወገንተኝነት እናደርግለታን የሚል ቢሆንም ይህ ግን አይሰራም።ይህን ስውር አካሄዳቸውን ኢትዮጵያ በቀላሉ የምትመልሰው ይሆናል።ይህን ቡድን ከሰራው ግፍ አንጻር እንደ ኢትዮጵያ የቻለው ያለ አይመስለኝም።ለምሳሌ አንድ አካል ተነስቶ አሜሪካንን ለማፍረስ እሄዳለሁ ቢል አሜሪካ አጥንቱን ጭምር ነው ልታቃጥል የምትችለው።ስለዚህ እነርሱ አሸባሪውን ቡድን መደገፋቸው እጅግ ከሞራል የወረደ ስራ ነው።ሰብዓዊነትን ለዚህ ጸያፍ ድርጊት መጠቀም ማለት እጅግ የረከሰ ስራ ነው ማለት ይቻላል።ሰብዓዊ መብትን ለተራ ስራና ለፖለቲካ መጠቀሙ አሳፋሪም ጭምር ነው።ሪፖርቱን እንደሪፖርት በራሱ ጽፈው ማውጣታቸው ምንም አይነት ሞራል እንደሌላቸው የሚያሳይ ነው፡ ለትምህርትም፣ ለእውቀትም ለአጠቃላይ ለዓለም ራሱ ነውር ራሱ አሰዳቢ የሆነ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሪፖርቱ የኢትዮጵያን መንግስት ረሃብን እንደጦርነት ተጠቅሟል፤ የዘር ማጥፋት ተካሂዷል… የሚሉ ክሶችን አካቷል። ይሄን እንዴት አዩት?**

**አቶ እንዳለ፡-** ረሃብን እንደጦርነት የሚጠቀሙት እኮ ራሳቸው ብር የሰጡት አካላት ናቸው።ለምሳሌ የአሜሪካ የእርዳታ ድርጅት (ዩኤስአይዲ) እርዳታን ለመላው ኢትዮጵያ በተለይ በሌሎች አካባቢዎች በተፈናቀሉና ጉዳት ባለባቸው አካባቢዎች ጭምር ከመስጠት ይልቅ ለዚህ ቡድን ነው እየመረጠ የሚሰጠው።ይህ ማለት ጥፋት ለሚፈጽም ቡድን መስጠት ማለት ነው።ለስንት ዓመታት የሚመጣለትን እርዳታ እየሸጠ መሳሪያ ሲገዛበት የነበረው በዚህ ቡድን አመቻችነት ነው።በአጋሮቹ ጭምር ማለት ነው።ይህ አሸባሪው ቡድን ሲዘርፍ አይናቸው ያያል።ነዳጁን፣ ዘይቱን፣ ስንዴውን ከነመኪናው ጭምር ሲዘርፍ አንዱ ላይ እንኳን ስለዘራፊነቱ አላነሱም።እንዲያውም ከምስረታው ጀምሮ እርዳታን፣ ረሃብን እንደጦርነት የተጠቀመው ቡድን ቢኖር ሕወሓት ነው።አሁንም ራሱ ሕወሓት በእርዳታ ስም የተቋቋመና በእርዳታ ስም ጦርነት እያካሄደ ያለ ቡድን ነው።

ታዲያ ይህንን ቡድን ለማዳን ነው ያልተገባ ሪፖርት ይፋ ያደረጉት።ይህ ግን ኢትዮጵያን ጨርሶ አይገልጽም።ይህ የሚገልጽ ከሆነ በትክክል ሕወሓትን እና የራሱን አጋሮች ነው።ስንትና ስንት መኪና እዛ ሄዶ የቀረው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።ይህ ማለት ደግሞ በእርዳታ ስም እነዚህን መኪናዎች እሰጥሃለሁ፤ አንተ ተዋጋቸው በሚል ነው።ሚሊሻዎችህን አንቀሳቅስባቸው ማለት ነው።ሌላ ትርጉም የለውም።ስለዚህም ሪፖርቱ የሚገልጸው እነርሱን ስለሆነ ገልብጦ ለራሳቸው መንገር ነው።እነርሱ እየነገሩን ያለው የተገለበጠውን የራሳቸውን ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እነርሱ ባወጡት ሪፖርት የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና በመፍጠርና የመከላከያ ሰራዊቱን በማጠልሸት ሕወሓትን ማጉላት ይችላል? ተዓማኒነትስ ይኖረዋል?**

**አቶ እንዳለ፡-** እንዴት ይቻላል! ይህ ማለት ምን ያህል ጥርሳቸውን አግጥጠው ለጥፋት እንደተነሱ የሚያሳይ ነው።በተለይ አካባቢውን በመበጥበጥ ኢትዮጵያውያኑን ለማሰቃየት በግልጽ የተነሱበት ነው።ሕጋዊ የሆነና ዓለም አቀፋዊ የሆነ ድርጅት ያጠናውን ሪፖርት ትተው ሶስት ግለሰቦች ድርሰት እንዲጽፉ ተፈቅዶላቸው ይፋ መደረጉ ከተዓማኒነት የራቀ ጉዳይ ነው።በዚህ ጉዳይ ዓለም ባለፈው ታዝቧቸዋል፤ አሁንም ይታዘባቸዋል።የባይደን አስተዳደር ምን ነካው እየተባለም ጭምር ነው።ይህ በራሱ ኢትዮጵያውያንን በቅጡ ካለማወቅ የመነጨ ነው።አሊያም ደግሞ በመሃላቸው የሆነ የግንዛቤ ችግር ተፈጥሯል ማለት ነው።ይህ አካሄዳቸው ነገሮችን በፈለጉት መጠን የሚቀይርላቸው ሳይሆን ኢትዮጵያውያኑን የበለጠ አንድ የሚያደርግ ነው።በተጨማሪም አፍሪካውያን ራሳቸውን እንዲያዩ የሚያደርግ ነው።በተለይ ደግሞ የምዕራቡ ዓለም አካሄዱ የበለጠ አግጥጦ እየታየ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የጥናት ቡድኑ አይኑን ያፈጠጠ አድልዎ ያለበት ድርጊት ከመፈጸሙ ጎን ለጎን የመቀሌውን ጉዳይ ድጋሚ ማጥናቱስ የሕግ ጥሰት አይሆንበትም?**

**አቶ እንዳለ፡-** መደበኛ በሆነው ጥናት እንኳ ምርጠታዊ (selective) ሆኖ ማጥናት አይቻልም።ጥናት ሲባል ጠንካራውንም ደካማውንም ጎን የሚመለከተው ሚዛናዊ በማድረግ ነው።እነርሱ ያደረጉት ግን ኢ-ሳይንሳዊ የሆነ ነገር ነው።ነገር ግን የሰሩት መጥፎ ስራ ስላለ እሱ ደስ አላሰኛቸውም።ስለዚህ በመጀመሪያ የተጠናውን ሪፖርት እንደገና ማንቋሸሽ አለባቸው።የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር ግን ሶስት ሰው ብቻ ያጠናው ሪፖርት ሊቀርብ ባለመቻሉ ነው።ምክንያቱም ሲቋቋም ጀምሮ ይህ ቡድን በራሱ ሕገ ወጥ ስለሆነ ነው።ኢትዮጵያ እውቅና ያልሰጠችው ነው።ምክንያቱም እውቅና ሊያሰጥ የሚያስችለውን መስፈርት ሁሉ ያላሟላ ነው።ቡድኑ ያወጣው ሪፖርት እንዲህ ቢሆን ወይም እንዲህስ ቢሆንስ ለማለት ካልሆነ በስተቀር ለውሳኔ የሚሆን አይደለም።ወደ ውሳኔ ለመቀየር ግን ሊሰራ የሚችለው በመጀመሪያው የተጠናው ሪፖርት ነው።ይህኛው ግን በሕገ ወጥ አካሄድ ሕገ ወጥ ቡድን የሰራው ስራ በመሆኑ ይህንኑ ለእነርሱ መንገር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሪፖርቱ ስለመሰረተ ልማት አለማግኘታቸው ተጠቅሷል፤ ይህ ጉዳይ አሸባሪው ባለበት ሁኔታ መሰረተ ልማት መገንባት የሚያስችል ሆኖ ነው? አሸባሪው በየደረሰበት ሁሉ ቀድሞ የተገነቡትን መሰረተ ልማት ማውደሙ እየታወቀ ይህ መባሉ ምንን የሚያመላክት ነው?**

**አቶ እንዳለ፡-** ለዚህም እኮ ነው በአጠቃላይ ሪፖርቱ ልክ አይደለም የምለው።በመጀመሪያ ደረጃ ስለመሰረተ ልማት ከኢትዮጵያውያን በላይ እነርሱ ምን አግብቷቸው ነው።እነርሱ መሰረተ ልማት እንዲወድም መኪና እየሰጡ ነው።ጎን ለጎን ደግሞ መሳሪያ እያቀረቡ ነው።ሕወሓት ደግሞ ከትግራይ ክልል አልፎ የሌላው ክልል መሰረተ ልማት እያወደመ ነው።በመላ ኢትዮጵያ ያለውንም ጭምር እያወደመ ነው።ስለዚህ ስለመሰረተ ልማት ለማውራትም በራሱ ሞራልም የላቸውም።ሕወሓትን ሲያቋቁሙት ጀምሮ ባንክ እንዲዘርፍ፣ ድልድይ እንዲሰብር አድርገው ነው።ስለሆነም ይህ ቡድን እንኳን ኢትዮጵያን ሊጠይቅ ቀርቶ ከተቻለው በረፈደ ሰዓትም ቢሆን መጠየቅ ያለበት ይቅርታን ነው።እነርሱ ያዋቀሩት ቡድን የሰጡትን ተልዕኮ ሳይጨርስ እየሞተባቸው ስለሆነ ስለምን ቀድሞ ይሞትብናል በሚል ተነሳሽነት ነው እያደረጉ ያሉት ስራ።

**አዲስ ዘመን፡- ሪፖርቱ ትኩረቱን ያደረገው ኢትዮጵያ ላይ ጫና ለመፍጠር ይመስላልና በዚህ ጉዳይ መፍትሔው ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ እንዳለ፡-** መፍትሔው ቀላል ነው፤ አንደኛ ምንም መደናገር አያስፈልግም።ከዚህ የበለጠ ሪፖርት ሊያወጡ ይችላሉ።ስለዚህ ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ ሆነው ከፍተኛውን ቅይጥ ጦርነት የሚባለውን የምዕራቡን የተሳሳተ አጀንዳ መረዳት መቻል አለባቸው።ስለዚህ ይህ ሪፖርት ቢወጣ የሚገርም አይደለም።ራሱ አውጪው አካል ሕገ ወጥ ቡድን ነውና።የወጣውም በሕገ ወጥ መንገድ ነው።ስለዚህ አሁን ኢትዮጵያውያን ችግራቸውን ወደማጠናቀቁ ገደማ ቀርበዋል።ለተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ እጅ መስጠት የለባቸውም።እያንዳንዳቸው ግን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ‹ይህ በጣም የረከሰ ሪፖርት ነው› ሊሉ ይገባል።ስለዚህም ለእንዲህ አይነቱ ውዥንብር ቦታ መስጠት አያስፈልግም።የበለጠ አንድነታችንን በማጠናከር እንዲህ አይነቱን ተራ ትርክት መከላከል መቻል አለብን።በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በኢትዮጵያ አገራችን ላይ የመጨረሻ የረከሰ ነገር እየተካሄደ ነው ሊሉና ይህን ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።በአሁኑ ወቅት ስለ አማራው፣ ስለ አፋሩ ጉዳት ማስረዳት ይጠበቅብናል።ከጫፍ እስከ ጫፍ ያለውን የኢትዮጵያውያን ጉዳት ማስረዳትም አለብን።ከዚህ ቀደም በወረረን ጣሊያንና በእኛ ላይ እኩል ማዕቀብ የጣለብን አካል ነው ዛሬም አሸባሪውን ሕወሓት እና ኢትዮጵያን እኩል ለማየት የሚፈልገውና እዚህ ላይ ንቁዎች ልንሆን ይገባል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ እንዳለ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ነፃ የንግድ ቀጠናው ለድሬዳዋ ኢንቨስትመንት ያመጣው መልካም አጋጣሚ

አንተነህ ቸሬ

የኢትዮጵያን የወጪና ገቢ ንግድ በማቀላጠፍና የኢንቨስትመንት ፍሰቱን በመጨመር ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተስፋ የተጣለበት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና (Dire Dawa Free Trade Zone)፣ ነሐሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ስራ እንደጀመረ ይታወሳል።በድሬዳዋ የሚገኘውን የኢንዱስትሪ ፓርክና ደረቅ ወደብን ከዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት፣ ከባቡርና ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በማቀናጀት እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የባንክና የጉምሩክ አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ ወደ አገልግሎት እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችሉት ተግባራት ሲከናወኑ ከቆዩ በኋላ ስራ እንዲጀምር የተደረገው ነፃ የንግድ ቀጠናው፤ ለበርካታ ዓመታት ከነፃ የንግድ ቀጠና አሰራር ርቆ ለኖረው የኢትዮጵያ ንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት ትልቅ አበርክቶ እንደሚኖረው ተገልጿል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ነፃ የንግድ ቀጠናውን መርቀው ስራ ባስጀመሩበት ወቅት «ነፃ የንግድ ቀጠና ጥቅል አገራዊ ምርትን፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትንና የወጪ ንግድን ለማሳደግ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው።የበለፀጉት አገራት በንግድና ኢንቨስትመንት ስራቸው ትልቅ ለውጥ ያስመዘገቡት እንደነፃ የንግድ ቀጠና ያሉ አሰራሮችን በመዘርጋታቸው ነው።በድሬዳዋ የተቋቋመው ነፃ የንግድ ቀጠና የራሱ ሕግና አሰራር ያለው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረ ሌላ ትንሽ ኢትዮጵያ ነው።ነፃ የንግድ ቀጠናው እንዲቋቋም የተፈለገበት ምክንያት የተቀላጠፈ የሎጂስቲክስና የንግድ ስርዓት ለመዘርጋት ነው።ቀጠናውን በአግባቡ በመጠቀም በጥቅል አገራዊ ምርት፣ በወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ፍሰት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ ይገባል» ሲሉ አብራርተው ነበር።


ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ኢትዮጵያ 40 እና 50 ሚሊዮን ሕዝብ እያላት በነበረው አሰራር ልትቀጥል እንደማትችልና ቀልጣፋ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችን ማወቅና መተግበር እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ በተለይ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ነፃ የንግድ ቀጠናው የፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በገቢና ወጪ ንግድ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ላይ እመርታ እንዲመጣና ውጤት እንዲመዘገብ ከመንግሥት ጋር በመተባበር መስራት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል።

የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና የወጪና ገቢ ንግድን በማቀላጠፍ፣ የኢንቨስትመንት ፍሰትን በማሳደግና የስራ እድል በመፍጠር ለድሬዳዋ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት እድገት እንዲያስመዘግብ አወንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል። የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ካሚል ኢብራሂም ነፃ የንግድ ቀጠናው በይፋ ከተመረቀ በኋላ ብዙ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በነፃ ንግድ ቀጠናው ውስጥ ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩ እንደሆነ ይናገራሉ።

እንደ አቶ ካሚል ገለፃ፣ ነፃ የንግድ ቀጠናው በሌሎች አገራት ከሚገኙ ብዙ ነፃ የንግድ ቀጠናዎች ያላነሰ የመሰረተ ልማት አቅርቦት አለው። በዚህም ምክንያት በቀጠናው ውስጥ ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ቁጥር ጨምሯል።

እስካሁን ድረስ 48 ባለሀብቶች በነፃ የንግድ ቀጠናው ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተው ተመዝግበዋል። ከዚህ በተጨማሪም በርካታ ባለሀብቶች ስለነፃ ንግድ ቀጠናው ገለፃ ስለተደረገላቸው፤ በቀጣይ ጊዜያት በነፃ የንግድ ቀጠናው ለመሰማራት ፍላጎት የሚያሳዩና የሚመዘገቡ ባለሀብቶች ቁጥር ከዚህም በእጅጉ የበለጠ እንደሚሆን ይጠበቃል።ምዝገባው በአዲስ አበባም እየተካሄደ ይገኛል።

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፣ ወደ ነፃ የንግድ ቀጠናው ገብተው ለመሰማራት ፍላጎት ካሳዩት ባለሀብቶች መካከል በአምራች ዘርፎች የተሰማሩ ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪም በአገልግሎትና በሎጂስቲክስ ዘርፎች የተሰማሩ ባለሀብቶችም ወደ ነፃ የንግድ ቀጠናው እየገቡ ነው።



እስካሁን ድረስ 48 ባለሀብቶች በነፃ የንግድ ቀጠናው ለመሰማራት ፍላጎት አሳይተው ተመዝግበዋል

ቀልጣፋና ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ በመፍጠር በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስተናገድ ዘርፈ ብዙ ዝግጅቶች እንደሚያስፈልጉ አይካድም። በዚህ ረገድ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ የነፃ ንግድ ቀጠናው ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ከማል ይገልፃሉ።እርሳቸው እንደሚሉት፤ የነፃ ንግድ ቀጠናውን መቋቋም ተከትሎ እየጨመረ የመጣውን የባለሀብቶች ፍሰት በብቃት በማስተናገድ ነፃ የንግድ ቀጠናውን ውጤታማ ለማድረግና አገራዊ ተጠቃሚነት እውን እንዲሆን የባለሀብቱን ፍሰት የሚመጥን አገልግሎት ለማቅረብ እየተሰራ ነው።

«ነፃ የንግድ ቀጠናውን መቋቋም ተከትሎ የባለሀብቶች ፍሰት እየጨመረ በመምጣቱ እኛም ብዙ ዝግጅቶችን እያደረግን ነው።የሥራ መመሪያዎችንና ደንቦችን አዘጋጅተን ጨርሰናል።በነፃ የንግድ ቀጠናው ውስጥ የማምረቻ፣ የሎጂስቲክስና የመጋዘን (Warehouse) አገልግሎቶች ይሰጣሉ።የንግድ ቀጠናውን የአገልግሎት አቅም፣ እየጨመረ ከመጣው የባለሀብቶች ፍሰት ጋር ለማጣጣም መሬትን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ነው» ይላሉ።

በሌላ በኩል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣሉ ተብለው የሚጠበቁ ተቋማት ነፃ የንግድ ቀጠናው ስራውን እያከናወነ ባለበት ፍጥነት ስራቸውን የማከናወናቸው ጉዳይ እንደስጋት ሊነሳ እንደሚችል አቶ ካሚል ይጠቅሳሉ። «ለባለሀብቶች አገልግሎት የሚሰጡ የመንግሥት የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የኢምግሬሽን፣ የጥራትና ደረጃ፣ የሎጂስቲክስና ሌሎች ተቋማት ነፃ የንግድ ቀጠናው እየሄደበት ባለው ፍጥነት ልክ ላይሄዱ ይችላሉ የሚል ስጋት አለን» ይላሉ። ይህን ስጋት ለማስወገድ በቅንጅት መስራት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

«ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ የነፃ የንግድ ቀጠና አሰራርን ተግባራዊ ባለማድረጓ ብዙ ጥቅሞችን አጥታለች» የሚሉት አቶ ካሚል፣ ነፃ የንግድ ቀጠናው ንግድና ኢንቨስትመንትን በማነቃቃት ለድሬዳዋ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያ ትልቅ ተስፋ ያለው በመሆኑ ለውጤታማነቱ መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተጨባጭ ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ።

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ባለሀብቶችን በሚገባ ለማስተናገድ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ እንዳለበትና በባለሀብቶች ፍሰት የአካባቢው ማኅበረሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ስለሚሆን ኅብረተሰቡ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ለማቅረብ ተጠቃሚነቱን ማሳደግ እንደሚገባውም ይመክራሉ።

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የኢንቨስትመንት ዳይሬክተር አቶ መሐመድ ሐሰንም ነፃ የንግድ ቀጠናው መቋቋም ለከተማዋ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማደግ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ይናገራሉ።ከነፃ ንግድ ቀጠናው መቋቋም በኋላ ባለሀብቶች ከአገር ውስጥ ከውጭ አገራት በመምጣት የንግድ ቀጠናውንና ከተማዋን እየጎበኙ ብዙዎቹም በኢንቨስትመንት ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩ እንደሆነም ይገልፃሉ።

በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ የፀጥታ ችግሮች የከተማዋ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እንዲዳከም አድርገውት እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ መሐመድ፣ በአሁኑ ወቅት የከተማዋ ሰላም የተረጋጋና አስተማማኝ በመሆኑ የኢንቨስትመንት ፍሰቱም እየተነቃቃ እንደሚገኝ ይገልፃሉ። «የከተማዋ ሰላም የተረጋጋ በመሆኑ ስራ ያቆሙት እየተከፈቱ ነው፤ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችም ወደ ስራ እየገቡ ይገኛሉ። የኢንዱስትሪውም ሆነ የአገልግሎት ዘርፉ ከፍተኛ መነቃቃት እያሳዩ ነው» በማለት የከተማዋ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ስላለበት ወቅታዊ ሁኔታ ያስረዳሉ።

እንደርሳቸው ገለፃ፣ የከተማዋ አስተዳደር ባለሀብቶችን ለመቀበልና ቀልጣፋ የኢንቨስትመንት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ አሰራሮችን አዘጋጅቷል። አስተዳደሩ አዋጭ የሆኑ 31 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመለየት ባለሀብቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተለያዩ ቋንቋዎች መረጃዎችን አደራጅቷል።ድሬዳዋ ከወደብ በቅርብ ርቀት ላይ የምትገኝ የኢንዱስትሪ ከተማ በመሆኗ የከተማዋ ኢንቨስትመንት ለስራ እድል ፈጠራ ከሚኖረው አስተዋጽኦ አንፃር ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ዘርፎች እንዲሰማሩ አስተዳደሩ እንደሚያበረታታም ይናገራሉ።

አቶ መሐመድ እንደሚሉት፣ በአሁኑ ወቅት በድሬዳዋ ከአንድ ሺ 200 በላይ ፕሮጀክቶች በግንባታ ላይ ይገኛሉ።ከእነዚህ መካከል 80ዎቹ ግዙፍ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሲሆኑ አንዳንዶቹም በመጠናቀቅ ላይ ናቸው። ቀደም ሲል ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ለመሰማራት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል አንዱ የነበረውን የመሬት ችግር ለመፍታት በተሰሩ ስራዎች፤ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ/ነፃ የንግድ ቀጠና መግባት ያለባቸውን ወደ ቀጠናው እንዲገቡ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ከተማ አስተዳደሩ ወዳዘጋጃቸው ስፍራዎች ገብተው እንዲሰሩ የሚያስችል የክላስተር አደረጃጀት ተግባራዊ ተደርጓል። ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ማሟላት የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች አሟልተው በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ ለማድረግ ለልማት የሚውሉ ቦታዎችን ቀድሞ በመለየትና የካሳ ክፍያዎችን በመፈፀም ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር እየተሰራ ነው።

በ2015 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ ለ490 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ለመስጠት፣ 10 ትልልቅ ሆቴሎችን ለመገንባት፣ ለ17ሺ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር እቅድ የተያዘ ሲሆን፤ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በማሳደግና የስራ እድል ፈጠራ አቅማቸውን በመጨመር ወደ ከፍተኛ የአምራችነት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ማድረግ የዓመቱ ትኩረት እንደሚሆን አቶ መሐመድ ገልፀዋል።

«የኢንቨስትመንት ዘርፍ ችግሮችን በመፍታት የከተማዋን የኢንቨስትመንት ፍሰት ለመጨመር ዘርፉ በቦርድ እንዲመራ የተደረገ ሲሆን ሰብሳቢም የከተማዋ ከንቲባ ናቸው።ሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፍ ጉዳዮች በቦርዱ እየታዩ የዘርፉ ችግሮችም ሆኑ የባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ፈጣንና የተደራጀ ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋል» ይላሉ።

«ነፃ የንግድ ቀጠናው ይፈጥራል ተብሎ የሚታሰበው የሥራ እድል ከድሬዳዋ አልፎ ለምስራቁና ለሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች ጭምር የሚተርፍ ነው» የሚሉት አቶ መሐመድ፤ ድሬዳዋ ከተማ ነፃ የንግድ ቀጠናው የፈጠረውን እድል በመጠቀም ጭምር በኢንዱስትሪ መናኸሪያነት የሚታወቀውን ስሟን (Industrial Brand) ለመመለስ ጥረት እያደረገች እንደምትገኝም ተናግረዋል።

የምጣኔ ሀብት ጥናት ምሁራን እንደሚያስረዱት፤ ነፃ የንግድ ቀጠናው የምጣኔ ሀብት ትስስርን ለማጎልበት ይረዳል።ኢንቨስትመንትን በማሳደግና ተጨማሪ የስራ እድሎችን በመፍጠር የሥራ አጥ ቁጥር እንዲቀንስ ያግዛል።የገበያ አማራጮች እንዲጨምሩ በማድረግ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲያድግም አስተዋፅኦ ያበረክታል።ይህም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ ተጨማሪ አቅምና አማራጭ ይፈጥራል።አገር በቀል ባለሀብቶች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን እንዲለምዱ እድል ይፈጥርላቸዋል።ከዚህ በተጨማሪም የወጪና ገቢ ንግድን በማቀላጠፍ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ ያበረታታቸዋል።የንግዱ መፋጠን ደግሞ የምርት ፍላጎትን ለመጨመርና ደንበኞችን ለማፍራት ያስችላል።ይህም ነፃ የንግድ ቀጠና ከንግድ ልውውጥ በተጨማሪ የአገር ውስጥና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን የማሳደግም ድርብ አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው ያመለክታል፡፡

የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና፤ በንግድ ልውውጥና በኢንቨስትመንት ፍሰት ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማቃለል ከተተገበሩ የመፍትሄ አማራጮች መካከል አንዱ ተደርጎ ሊጠቀስ የሚችል ነው።ነፃ የንግድ ቀጠናው አዳዲስና ሰፊ የሆኑ የሥራ እድሎችን ለመፍጠር፣ ተኪ ምርቶችን ለማምረት፣ የእውቀት ሽግግርን ለማሳደግ እንዲሁም ለአገር ውስጥ የቀረቡ ምርቶችን ለማከማቸትና የሎጀስቲክስ ወጪን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።ይህም አገራዊ የሎጂስቲክስ ተወዳዳሪነትን ትርጉም ባለው መልኩ ሊለውጥ የሚችል በመሆኑ የአገሪቱን የገቢና ወጪ ንግድ ስርዓት ለማቀላጠፍ ያግዛል።አሰራሩ የሚያስገኛቸው ጥቅሞችና የሚፈጥራቸው እድሎች የምርት ወጪን በመቀነስ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋትም ትልቅ ሚና ይኖረዋል።እነዚህ ሁሉ ጥቅሞች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለጥቅል አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ዓይነተኛ ፋይዳ አላቸው።

በነፃ የንግድ ቀጠናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ህጋዊ አሰራሮች ቀለል ያሉና ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን የሚቀንሱ በመሆናቸው ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚያደርጉትን ጥረት በአንፃራዊነት ቀላል ያደርጉላቸዋል።በነፃ የንግድ ቀጠናው ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ባለሀብቶች፣ አስመጪና ላኪዎችም ሆኑ ድርጅቶች የልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ።ይህ ደግሞ የአገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ከሚሰጠው ከነፃ የንግድ ቀጠና ስርዓት ርቃ መቆየቷ ብዙ ጥቅሞችን እንዳሳጣት እየተገለጸ ነው።የእነዚህ ጥቅሞችና እድሎች መታጣት ደግሞ በአጠቃላይ እድገቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረባት አይካድም።ድሬዳዋም ቀድሞ ትታወቅበት ከነበረው የኢንዱስትሪና የንግድ መናኸሪያነቷ ርቃ መቆየቷ ይታወቃል። በድሬዳዋ የተቋቋመውን ነፃ የንግድ ቀጠና ይህን ሁኔታ ለመቀየር ጥሩ እድል ይዞ መጥቷል።ስለሆነም በድሬዳዋ የተቋቋመውን ነፃ የንግድ ቀጠና በሚገባ በመጠቀም የድሬዳዋን የኢንቨስትመንት ፍሰት ማሳደግ ይገባል፤ ከድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመርና በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎችም ተጨማሪ ነፃ የንግድ ቀጠናዎችን በማቋቋም አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገቱ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያስመዘግብ ማድረግ ይገባል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# ስምድ ስባሹ ሪፖርት

**ምሕረት ሞገስ**

ሰሞኑን ከመጠጥ ቤቱ ጠፍቶ የሰነበተው ተሰማ መንግስቴ ዛሬ ከብስጭቱ ጋር ብቅ ብሏል። ጠፍቶ ቢከርምም ብስጭቱን ሊያስታግስ መጠጣት አሰኝቶታል። እንቅፋት ከተሰናቸው ቤት ጎራ አለ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዘወትር ደንበኛ የሆኑት ዘውዴ መታፈሪያ እና ገብረየስ ገብረአምላክ ብርጭቋቸውን ከፊታቸው አስልፈው የሞቀ ጨዋታ ይዘዋል። ተቀላቀላቸው።

ተሰማ እንደበፊቱ ቢራ አላለም፤ ዛሬ ጠንከር ያለ አልኮል ነገር አስፈልጎታል። ጂን አዘዘ፤ ዘውዴ እና ገብረየስ ተያዩ፤ ትንሽ ግራ የገባቸው ይመስላሉ። ተሰማን የሚያውቁት በእርጋታው ሁሉንም ነገር ቀለል አድርጎ የሚያይ ሆኖ ነበር። ዘውዴ « ምን ሆነኻል?» የሚል ጥያቄ አቀረበለት። ተሰማ በበኩሉ « ሁልጊዜም የሚያስገርመኝ የኢትዮጵያ ጠላት ብዛት ነው። የሚገርመው ደግሞ ብዙ ኢትዮጵያውያን ይህንን አለማወቃቸው እና ለጉዳዩም ትኩረት አለመስጠታቸው ነው። ሃሳቡ ጥልቅ ነገሩ ጥብቅ የሆነ ቡድን ሊመራ ቢመጣም የሚያምን፤ የሚስማማ እና የሚያግዝ ማግኘት አዳጋች ነው። ሁሉም ነገሮችን በጥልቀት ከሚመለከት በሳል ሰው ጋር በመተባበር ለአገር ከመረባረብ ይልቅ የጠላት መጠቀሚያ ይሆናል።...» እያለ መራር ንግግሩን ቀጠለ።

«ነገር የሚከረው ጎንጓኙን ሲያገኝ ነው፤ ዛሬስ እኔን ተከተሃል፤ ነገርን ችላ ብሎ ወይም በትዕግስት መያዝ እንጂ ሆን ብለው ከጎነጎኑት መከረሩ አይቀርም፤ ይሔ ደግሞ የሚጎዳው አንዱን ወይም አጥፊ እና ተናጋሪውን ብቻ አይደለም። አንተንም ነው። ስለዚህ በንዴት መስከር በማግስቱ ጉዳት እና ራስ ምታት በመሆኑ መታገስ፤ በብልሃት ማለፍ እና መጠንቀቅ ይሻልሃል።» አለ ዘውዴ የንዴት ይሁን የሌላ ጥርሱን ከከንፈሩ እያላቀቀ።

ተሰማ በዘውዴ ንግግር ትን እስኪለው ሳቀ። «በፊት ይህንን ምክር የምመክርህ እኔ ነበርኩ። ለካ ምክር ለሰጪው ቀላል ነው የሚባለው እውነት ነው።» ብሎ ከት... ከት... ብሎ ሳቀና ያበሳጨውን ጉዳይ ቀለል ለማድረግ ሞከረ። በፊላ ወተት ላይ ውሀ እንደመቸለስ። «ነገሮችን በጥንቃቄ ማየት ስህተት ላይ ላለመውደቅ ያግዛል። ነገር ግን በጥንቃቄም ለማየት ያልፈለገ የፈለገ አይኑ ቢፈጥም ልቡ ካላየ ጉዳዩ አይገለጥለትም፤ ምክንያቱም መጀመሪያውኑ መደምደሚያ ላይ ደርሷል። ነገሩ ሃሜተኛም ያፍራል ሃሰተኛም ይረታልና እውነቱ መውጣቱ አይቀርም።» አለ በድጋሚ የተቀዳለትን ጂን በአንድ ትንፋሽ ጨልጦ እያስቀመጠ።

ገብረየስ ግራ ገባው ተሰማ እና ዘውዴ የሚነጋገሩትን ከማዳመጥ ውጪ ምንም ዓይነት ቃል አልተነፈሰም። ቀደም ሲል አልኮል እየጨለጠ የሚናገረው ዘውዴ ነበር ። ዛሬ ግን በዘውዴ እግር ተሰማ ተተክቷል። ገብረየስ ፈዞ ተሰማን ሲያይ ዘውዴ ለተሰማ ጥያቄ አቀረበ። «ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ ምን ዓይነት ስብሰባ ላይ ብትውል ነው እንዲህ የተበሳጨኸው? ለመሆኑ ያበሳጨህ ምንድን ነው?» ሲል አከታትሎ ጥያቄዎችን አቀረበ። ተሰማ በበኩሉ «በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል ይህንኑም አጣራለሁ በሚል የተሰየመው ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሰየመው ቡድን ነበር። በጣም በሚገርምህ መልኩ ቀድሞም ቢሆን ከመነሻው ዓላማው የኢትዮጵያን መከላከያ ለማጠልሸትና በአገሪቱ ላይ ተጨማሪ ጫና ለማሳደር ነው። መድረሻውም ፖለቲካዊ መሆኑ ይታወቃል። ምክንያቱም እነሱ ሁልጊዜም ቢሆን እንዲህ አይነት ጉዳይ ውስጥ አለሁ የሚሉት ከጀርባቸው ዓላማ ሲኖራቸው ነው። በምን ምክንያት የኢትዮጵያን መንግስት እጅ እንጠምዝዝ ብለው ሲያስቡ ተላላኪ መንግስት ሲያሻቸው ሰብአዊመብት ጥሰትን ሽፋን አድርገው ይነሳሉ።

**ቡድኑ ችግሩ ወደተከሰተበት ስፍራ ሳይሄድ ሥራውን ከውጭ ሆኖ በስልክ ሲሠራ መቆየቱ በጥናት ተብየው ሪፖርት ላይ ተመላክቷል፡፡ በዚህ መልኩ የሚደረግ ጥናት ተዓማኒነትና ተቀባይነት የለውም። ሳይንሳዊም አይደለም**

በዛ ላይ ቡድኑ ራሱ ለተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ካውንስል ባቀረበው ሪፖርት፣ በግብዓት ዕጥረትና መሰል ምክንያቶች የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንደሚያዳግተው እና ጥልቅ ምርመራ ማካሄድ እንደማይችል አስታውቆ ነበር። ኮሚሽኑ የተጠቀመው የጥናት ዘዴ፣ ከጥናቱ ወሰንና ከዳሰሳው ስፋት፣ ከመረጃ አሰባሰብም ሆነ ከአተናተኑ ሂደት አንጻር ሳይንሳዊ መንገድን ያልተከተለና ከዓለምአቀፍ ድንጋጌዎች ጋር የተቃረነ እና የተሳሳተ ነበር።» ሲል በተሰማ አነጋገር ዘውዴ ተገርሞ፤ «ፖለቲካውን በጥንቃቄ እየተከታተልክ መሆኑን አረጋግጫለሁ» ብሎ ሳቀ። ተሰማ በፈገግታ «ይሔ እኮ የእንጀራ ወይም የፖለቲካ ጉዳይ ሳይሆን የአገር ጉዳይ ነው። የተበሳጨኹትም ለዚሁ ነው።» አለ። «አዛኝ መሳይ» ብሎ ረጅም ትንፋሽ አስወጣ።

ዘውዴ በበኩሉ «የገረመኝ ደግሞ ጥናቱ ሳይንሳዊ አለመሆኑን መግለጽህ ነው። እስኪ ሳይንሳዊ አይደለም ያሰኘህ ምንድን ነው? » ሲል ዘውዴ ተሰማን ለማፋጠጥ ሞከረ። ዛሬ ተሰማ የሚበገር አልሆነም። «ኮሚሽኑ ጥቂት ግለሰቦችን ከኢንቴቤ ኡጋንዳ ለአንድ አመት ያህል ቆይቶ በስልክ አነጋገርኩ በማለትና በመሰል ተጨባጭነት በሌላቸው አሉባልታዎች ላይ በመመስረት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። እንደውም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሥራውን ሳያከናውኑ ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ቀድሞም ቢሆን ፖለቲካዊ አላማ አንግበው መስራታቸውን ያመለክታል።» ሲል አስረዳ። ዘውዴ በተሰማ መልስ ተደስቷል። «ለምድ የለበሰ ሪፖርት አወጡ በለኛ» ብሎ ጣራ ጣራውን ማየት ጀመረ።

ተሰማ ቀጠለ፤ «በመንግስት በኩል ቡድኑ ምንም አዲስ ነገር ለመሥራት የሚያስችል አቅም የሌለውና እውነተኛ ሥራ ለመሥራት ፍላጎት ያልነበረው ስለመሆኑም ከሂደቱ ማረጋገጥ ችሏል። የቡድኑ አባላት ገና ሲመጡ ጀምሮ ወደስፍራው ሄደው የተከሰተውን ችግር ለማየት የሚያስችል ዝግጅት የሌላቸው በመሆናቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በጋራ ያካሄዱትን ጥናት ጥሬ መረጃ በመውሰድ ዳግም ለመተንተን ጥያቄ አቅርበዋል።

ይሔ የሚያሳየው አገሪቱ ላይ ዲፕሎማሲያዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጫና ለማሳደር የታለመ ኢ-ፍትሃዊና ህቅ ላይ ያልተመሰረተ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ሆን ተብሎ የተሠራ ሴራ መኖሩን የሚያሳይ ነው።ደግሞም እኮ በቅርቡ የተባበሩት መንግስታት ለሚያካሄዱት ስብሰባ እንደመረጃና ማስረጃ ለማቅረብ ነው፤ ይሄ የተቀናጀ ስለመሆኑ ብዙ ሳይንሳዊ ትንታኔ አያስፈልገውም። ትንሽ ፖለቲካውን ቀረብ ብሎ ለተከታተለ እውነቱ ቁልጭ ብሎ ይታያል። ቀድሞም ቢሆን የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን በመረዳት ኮሚሽኑ ከሰው ኃይል ጀምሮ በአካባቢው የተፈፀመውን ችግር ለማጣራት በቂ አቅምና ዝግጁነት ያልነበረው እንደሆነ በማረጋገጡ ከመነሻው ቅሬታውን ቢያቀርብም ቡድኑ ሁለት ባለሙያዎችና ሦስት ኮሚሽነሮችን በመያዝ ብቻ ወደ ሥራ ገብቷል።» ሲል በዝርዝር ጉዳዩን እንደሚያውቀው ለዘውዴም ሆነ ለገብረየስ በደንብ አብራራላቸው።

ቡድኑ ችግሩ ወደተከሰተበት ሥፍራ ሳይሄድ ሥራውን ከውጭ ሆኖ በስልክ ሲሠራ መቆየቱ በጥናት ተብየው ሪፖርት ላይ ተመላክቷል። በዚህ መልኩ የሚደረግ ጥናት ተዓማኒነትና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ማንኛውም አካል የሚያውቀው ነው። ቡድኑ ያተኮረው ተከስተውባቸዋል ከተባሉ ሥፍራዎች ውስጥ በመቀሌ፣ በቆቦና ጭና እንዲሁም በደደቢት ላይ ብቻ መሆኑ ጥናቱን ጎዶሎ ያደርገዋል። በተጨማሪ ቡድኑ የሄደበት የጥናት አካሄድም ሙሉ ለሙሉ የጥናት መስፈርቶችን ያላሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

በቀላሉ የፖለቲካ ዓላማ ያለው መሆኑን ለማወቅ ሌላው ቀርቶ ቡድኑ ለአንድ ወገን የሚያዳላና የፖለቲካ ይዘት ያለው ሪፖርት ማቅረቡን በማየት ብቻ ማረጋገጥ የሚያዳግት አይደለም። ለአብነት ገና ከመነሻው ጦርነቱን ማን ጀመረው? በሚለው ላይ እውነታውን ክዶ የሚነሳ መሆኑ በራሱ ማሳያ ነው። ከዚህ አንጻር መላው የዓለም ሕዝብ ጦርነቱን አሸባሪው ትህነግ እንደጀመረው እየታወቀና ራሱ የሽብር ቡድኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ‹መብረቃዊ ጥቃት ፈጸምን› ብሎ ምስክርነቱን ሰጥቶ እያለ "የፌዴራል መንግስት እና የትግራይ ክልል አንዱ በሌላው ላይ በማሳበብ" በሚል የጦርነቱ አስነሺ ማን እንደሆነ ለመሸፈን ያደረገው ጥረት የቡድኑን አይን ያወጣ ወገንተኝነት ያሳያል።» ሲል ስለቡድኑ ወገንተኝነት በሰፊው ለማስረዳት ሞከረ።

«በሌላ በኩል የመቀሌው የሰብአዊ መብት ጥሰትን በተመለከተ ቀደም ሲል የተባበሩት መንግስታት እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት የጋራ ኮሚቴ ማጣራት አድርጎ እያለ ድጋሚ ለማጥናት መነሳቱ ጥናት በተካሄደበት ስፍራ በድጋሚ ጥናት መካሄድ የለበትም የሚለውን የጋራ ስምምነት የጣሰ ነው።»

የጥናቱ ግኝት ተብሎ የተገለፀው ሪፖርትም ሆነ የጥናቱ ዘዴን በተመለከተ በርካታ እርስ በርስ የሚጣረሱ መረጃዎች የታጨቁበት እና ወደ እውነታው ለመንደርደር የማያስችሉ፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱም ወደ እውነታ ለመድረስ የማያስችሉ ሰነዱም የውሸት ለመሆኑ ምስክሮች ናቸው። በማለት የተናገረው ተሰማ፤ ለአብነት መግደል፤ መድፈር፣ መጨፍጨፍ፤ ወዘተ የሚሉ ቃላትን በሪፖርቱ ውስጥ ቢያካትትም ነገር ግን ቡድኑ መረጃዎችን ያጣራው በስልክ ከመሆኑ አንጻር ይህንን ለማወቅ የሚከብደው መሆኑን ከራሳቸው ከተገለፀ የጥናት መንገድ ራሱ ማወቅ ይቻላል። ለምሳሌ በመቀሌ ሴቶች መደፈራቸውን ከጠቀሰ በኋላ ማስረጃ ያደረገው አንድ ሃኪም ምስክር መሆኑ ምንም ዓይነት የጥናት መልክ የሌለው ሰነድ እንደሆነ የሚያመላክት ነው። ሲል ለጓደኞቹ አብራራ።

ቡድኑ በመቀሌ ማረሚያ ቤት ዘረፋ እንደተፈፀመ ይገልጻል። ነገር ግን የአሸባሪው ትህነግ ኃይሎች በመከላከያ ኃይል ተመትተው ሲወጡ፤ አስር ሺህ የሚሆኑ ታራሚዎችን ፈትተው በመሄዳቸው እነዚህ ሰዎች ማስረጃ እንዳይገኝባቸው ዘርፈው እንደሄዱ ይታወቃል። ይህ እየታወቀ እንዲህ ዓይነት ያፈጠጡ እውነቶችን በመካድ ችግሩን የፈፀመው የመንግስት ኃይል እንደሆነ ለማሳየት መሞከሩ የሰነዱን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል።

በጭና እና ቆቦ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ በተመለከተ የገለፀው፤ ቡድኑ ገና ከመነሻው ለአሸባሪው ቡድን ጥፋተኝነትን ለመከላከል የሄደበት መንገድ ትዝብት ላይ የሚጥለው ነው። በጭና ጭፍጨፋ የተፈፀመው መንግስት በወቅቱ ኅብረተሰቡ ታጥቆ የአሸባሪው ትህነግን ታጣቂ ኃይሎች እንዲዋጋ በማዘዙ የሽብር ቡድኑ አባላት ሲቪልና ተዋጊ የሆኑትን መለየት ባለመቻላቸው የተፈጠረ እንደሆነ አድርጎ አቅርቧል። እንዲህ ዓይነት ሪፖርት የፖለቲካ ሰነድ ከመባል ውጪ ሌላ ሰም ሊሰጠው የማይችል ነው። መንግስት ሰብአዊ እርዳታን እንደ ጦር መሳሪያ ተጠቅሟልም ብሏል፤ ነገር ግን በራሳቸው ሰዎች በመጋዘን ውስጥ በቂ እህል መኖሩን አረጋግጠናል ብለው አልነበረ እንዴ አሁን ታዲያ ያ የተናገሩት የት ገባ ?። ብቻ በአጠቃላይ የቡድኑ የመጨረሻ ግብ የመንግስትን ስም ማጠልሸት እና የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ላይ የሀሰት ክስ ለመጫን ሲል መሆኑ ግልፅ ነው።» ሲል ዘውዴ ለተሰማ ብድግ ብሎ አጨበጨበ። «በደንብ ሪፖርታቸውን አይተኸዋል። ታዲያ ምን አበሳጨህ?» ሲል ዘውዴ አንዳንድ ምዕራባውያንና አውሮፓውያን አንድ ነገር ማድረግ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት ዘዴ መሆኑን ለመግለጽ ሞከረ።

ተሰማ በበኩሉ «በሞኝ ክምር ዝንጀሮ ልጇን ትድር እንደሚባለው በሞኞች ገንዘብ ብልጣብልጦች ይጠቀማሉ። ነጮቹ ብልጣብልጦቹ በየሰበባ ሰበቡ እኛን እያባሉ እነርሱ እኛን ለመዝረፍ፤ ወይም የኢትዮጵያ መሆን ያለበትን ሃብት ለማሳጣት ሲጥሩ የሽብር ቡድኑ ትህነግን እና ሸኔን የመሳሰሉ የእናት ጡት ነካሾች ሲተባበሩ እና ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሲጥሩ መስማት እጅግ ያሳምማል።» አለ።

ዘውዴ በበኩሉ « በግልፅም ባይሆን በድብቅ ጦርነት እያወጁ ቢያሰቃዩንም። ‹ነፋስ በተነሳበት ጊዜ እሳት አይጫርም፤› እያልን ዝም ብንልም፤ አንተ እንዳልከው የውጪ ጠላቶቻችን የሚያካሂዱትን ዘመቻ መረዳታችን አይቀርም። ለወደፊት ግን ሴራቸውን ከመረዳት አልፈን ለመከላከል የምንችልበት ደረጃ ላይ የምንደርስበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ አለኝ። ዋናው ጉዳይ እርስ በእርስ ለመስማማት ጥረት ማድረግ እና የውጪ ጠላቶችን ሴራ ላልገባው ማስረዳት እንጂ መበሳጨት ትርፍ የለውም። እነርሱ ቢደክሙም የኢትዮጵያ ትንሳኤ ሩቅ አይሆንም።» ሲል፤ ተሰማ በረጅሙ ተነፈሰ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# መስከረም እና ኪነ ጥበብ

**ዋስልኝ አየለ**

እነሆ እንቁጣጣሽን አሳልፈን መስከረም አጋማሽ ላይ እየደረስን ነው።አሁንም ግን የበዓሉ ድባብ እንዳለ ነው።የሬዲዮና ቴሌቭዥን ማስታወቂያዎች አሁንም በበዓል ማጀቢያዎች የደመቁ ናቸው፤ በአደይ አበባ ዘፈኖች የታጀቡ ናቸው።ምክንያቱም በየመስኩ ያለው አደይ አበባ ገና እንደፈካ ነው።የመስከረም ወር እንዲህ ነው!

የመስከረም ወር ስሙ የሚጠራበት አጋጣሚ ብዙ ነው።ከሌሎች ወሮች የሚለየው ይሄው ስመ ገናናነቱ ነው።ስመ ጥር የሆነው ደግሞ በተፈጥሯዊ ባህሪው ነው።የክረምት ወራት አልቆ ፀሐይ የሚወጣበት፣ አበቦች በየመስኩ የሚፈኩበት ስለሆነ ነው።መስከረም ከክረምቱም ከበጋውም ወቅት የተለየ ነው።በክረምት ‹‹እኘኘኘ...›› ያለ ዝናብ እና ብርድ ነው።መሬቱም ጭቃ ነው።በበጋ ወቅት ደግሞ የነደደ ፀሐይና ሙቀት ነው።መሬቱም አቧራ ነው።መስከረም ግን ከሁለቱም ነፃ የሆነ ነው።የከፋ ጭቃ የለም፤ የከፋ አቧራ የለም።የከፋ ብርድ የለም፤ የከፋ ሙቀት የለም።በእነዚህ ባህሪያቱ ነው ስመ ጥር የሆነው።ከወራት ሁሉ ተለይቶ ለሰው ስም እንኳን ይውላል።በተለይም ለሴት ስም በስፋት ይውላል።ከመስከረም ወር በስተቀር የሰው ስም የሚጠራበት ወር አላውቅም።በገጠር አካባቢ በጣም አልፎ አልፎ በታኅሳስ ስም የሚሰየሙ ሰምቻለሁ (ትሳሱ)፡፡

መስከረምን የሰኔ ወር ትንሽ ሳይፎካከረው አይቀርም።ምናልባት ሁለቱን ስመ ጥር እንዲሆኑ ያደረጋቸው የክረምት ወር መግቢያና መውጫ ስለሆኑ ይሆን? በሌላ በኩል ደግሞ ለተማሪ ሁለቱም ወሮች ልዩ ስሜት አላቸው።የሰኔ ወር ተማሪ የሚለያይበት፤ የመስከረም ወር ደግሞ ተማሪ የሚገናኝበት ነው። በገበሬውም ካየነው እንደዚሁ ነው።በሰኔ ለእርሻ በጣም የሚታትርበት ነው፤ በመስከረም ደግሞ የዘራውን እሸት የሚቀምስበት ነው።በተማሪና በገበሬም አይወሰንም።በመንግስት ሰራተኛውም ሰኔ እና መስከረም የተለዩ ናቸው።ሰኔ የአዲስ በጀት መጀመሪያ ነው፤ መስከረም ብዙ አዳዲስ ሥራዎች የሚጀመሩበት ነው።

ወደ ዋናው ርዕሳችን ስንገባ የመስከረም ወርን እንዲህ ስመ ጥር ያደረገው ተፈጥሯዊ ባህሪውን ምክንያት በማድረግ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ናቸው።መስከረም በራሱ ጥበብ የሆነ ወር ነው።ለዚህም ነው በኪነ ጥበብ ሥራዎች ውስጥ ስሙ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው።ምንም እንኳን ዘፋኞች ውስጥ ቢበዛም፣ በገጣሚዎች፣ በተዋናዮች፣ በደራሲዎች... ከወራት ሁሉ በበለጠ የተጠቀሰ ነው።የጥበብ ሰዎች አበባ ሲያዩ ሀሳብ ይመጣላቸዋል ማለት ነው።ወደ ግጥሞችና ዘፈኖች ከመሄዳችን በፊት ግን የኪነ ጥበብ መጀመሪያ የሆኑትን የስነ ቃል ውጤቶችን እንመልከት።

በምሳሌያዊ ንግግሮች ውስጥ መስከረም ተደጋግሞ ይጠራል። የወሩን ተፈጥሯዊ ባህሪ ከሚገልጸው ምሳሌያዊ ንግግር እንጀምር።‹‹የመስከረም ዝናብ ከላም ቀንድ ይለያል›› ይባላል።የምሳሌያዊ ንግግሩ ትርጉም የመስከረም ዝናብ ሁሉንም ያማከለ አይደለም ለማለት ነው።የላም ቀንድ በጣም የተጠጋጋ ነው።አንዱ ጋ ዝናብ ዘንቦ አንዱ ጋ ላይዘንብ ይችላል ማለት ነው።ምሳሌያዊ ንግግሩ በጣም የተጋነነ ቢሆንም የመስከረም ዝናብ ግን እንዲህ ነው።አራት ኪሎ ዘንቦ ፒያሳ ላይዘንብ ይችላል።

‹‹መስከረም በአበባው ሰርግ በጭብጨባው›› የሚባል ምሳሌያዊ ንግግርም አለ።ጭብጨባ የሰርግ መለያ እንደሆነ ሁሉ የመስከረም መለያውም አበባ ነው።አንድ መንገደኛ እየሄደ የሆነ መንደር ውስጥ ጭብጨባ ከሰማ ‹‹እዚህ ግቢ ሰርግ አለ ማለት ነው›› ብሎ ይገምታል።እርግጥ ነው ነገሩ ሰርግ ብቻም ላይሆን ይችላል፤ በሌላ የድግስ ፕሮግራምም ይጨፈራል።ዋናው ግን ለሰርግ ነው።የመስከረም ወርም እንደዚሁ ነው።ስለመስከረም በተለያየ መረጃ የሚያውቅ አንድ የውጭ አገር ሰው ኢትዮጵያ መጣ እንበል።ኢትዮጵያ ሲገባ ጋራ ሸንተረሩ በአበባ ተንቆጥቁጦ ካየ ‹‹የመስከረም ወር ነው ማለት ነው›› ይላል።

ሌላው ገናና ምሳሌያዊ አነጋገር ደግሞ ‹‹ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም›› የሚባለው ነው።መስከረም አዲስ ዓመት ስለሆነ ባለፈው የተከናወኑ አስገራሚ ነገሮች ይታወሳሉ።በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ ባሉ ሳምንታት የሚወጡ ጋዜጦችና መጽሔቶችን ልብ ብላችሁ ከሆነ ያለፈውን ዓመት ክስተቶች ያስታውሳሉ።ለምሳሌ 2015 ሊገባ ሲል የ2014 ዓ.ም አስገራሚ ክስተቶች ይታወሳሉ ማለት ነው።‹‹ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም›› የሚባለው ለዚህ ነው።በዓመቱ ውስጥ የሆነ አስገራሚ ነገር አይጠፋም።

‹‹ለሞኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ›› የሚባል ምሳሌያዊ ንግግርም አለ።አሁንም ሰኔ እና መስከረምን ልናነፃፅር ነው።የሰኔ ወር የክረምት መግቢያ ሲሆን መስከረም ደግሞ የክረምት መውጫ ነው።ሞኝ ወይም ሰነፍ የሆነ ሰው በሰኔ ገበሬው ሁሉ ሲሯሯጥ እሱ ዝም ይላል።መስከረም ላይ ተፍ ተፍ ቢል ከየት ይመጣል! ‹‹ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ›› እንደሚባለው ማለት ነው።

ሌሎች ምሳሌያዊ ንግግሮች ደግሞ በቃል ግጥም የሚባሉ ናቸው።የቃል ግጥም ሆነው እንደ ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያገለግሉ አሉ።ያ ማለት ለዘፈንና እንጉርጉሮ ሳይሆን በጨዋታ (በወሬ) መካከል ሀሳቡን ለማዳበርና ግልጽ ለማድረግ ይጠቀሙታል ማለት ነው።

**መስከረም ሲጠባ**
**አደይ ሲፈነዳ**
**እንኳን ሰው ዘመዱን**
**ይጠይቃል ባዳ**

ይሄን የቃል ግጥም በብዙ የባህልና የበዓል ዘፈኖች ውስጥ ስለምንሰማው የዘፈን ግጥም ይመስለን ይሆናል።ዳሩ ግን የንግግር ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።በወግ መካከል የሚያወሩት ነው።ምናልባትም ዜማ ላይኖረውም ይችላል፤ መድረክ ላይ በሚነበብ ግጥም አይነት በወሬ መሃል ያስገቡታል።የመስከረምን ጸዳልነት ለመግለጽ ነው። በተለይም ገበሬዎች በክረምት ከፍተኛ የሥራ ውጥረት ውስጥ ስለሚሆኑ ዘመድ ከዘመድ እንኳን አይገናኙም።በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው የገጠራቱ የአገሪቱ ክፍል (በተለይም ቀደም ባሉት ዘመናት) ድልድይና የመኪና መንገድ ስለሌለ የሚገናኙት የወንዝ ውሃ ሲጎድል ነው።ወንዞች ከመስከረም በኋላ ስለሚጎድሉ ዘመድ ከዘመድ ይገናኛል።እንኳን ዘመድ ባዕዳም ይጠየቃል ያሉት ለዚህ ነው።

**ያረሰማ ጎበዝ**
**እርፍ የነቀነቀ**
**ወፍጮው እያጓራ**
**መስከረም ዘለቀ**

አዝማሪዎች በሰርግና በሌሎች ዝግጅቶች ላይ ገበሬውን ለማወደስ ይጠቀሙታል።ከአዝማሪዎች በፊት ግን የህዝብ ግጥም ነው።እንደማንኛውም ምሳሌያዊ ንግግር በወግ መካከል ይጠቀሙታል።በነገራችን ላይ ይሄ ምሳሌያዊ ንግግር (የቃል ግጥም ልንለውም እንችላለን) ከመስከረም ወር ይልቅ በሰኔና በሐምሌ ይደጋገማል።ምክንያቱም ሰነፍና ታታሪ ገበሬን ለማነጻጸር የሚያገለግል ነው።ሰነፍ ገበሬ በሰኔ እርሻ ላይ ተፍ ተፍ አይልም፤ ጎበዝ ገበሬ ደግሞ ተፍ ተፍ ይላል።ሰነፉ ገበሬ ጠንክሮ ባለመሥራቱ በሐምሌና ነሐሴ ይቸገራል (የሚመገበው ያጣል)።ጎበዝ ገበሬ ግን በክረምት ጠንክሮ ያረሰው ዓመቱን ሙሉ ስለማያልቅ ከመስከረም መስከረም ወፍጮው እያጓራ ይዘልቃል ማለት ነው።

ከቃል ግጥሞችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንወጣ ደግሞ ደራሲዎችን፣ ገጣሚዎችንና ዘፋኞችን እናገኛለን።ስለመስከረም ብዙ ተዘፍኗል።ምናልባት ግን በዘፈኖች ውስጥ የግጥሞች መደጋገም ይኖር ይሆናል፤ በብዙ የባህል ዘፈኖች ውስጥ የህዝብ ቃል ግጥም ስለሚበዛ መደጋገሙ ያጋጥማል።በሁሉም ውስጥ አበባ ይኖራል፣ ጋራ ሸንተረሩ በአደይ አበባ መድመቁ ይገለጻል።

ወደ ገጣሚዎች ስንሄድ በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው እንግዲህ የመንግስቱ ለማ ነው።የመስከረም ወርን ባህሪ የሚገልጽ ነው፡፡

የመስቀል ወፍና
የአደይ አበባ
ቀጠሮ እንዳላቸው
መስከረም ሲጠባ
ማን ያውቃል?

የመስቀል ወፍ እና የአደይ አበባ አንዳች አስማት ያላቸው ነው የሚመስል።የሚታዩት በመስከረም ወር ብቻ ነው።የመስቀል ወፍ ላይ ግን አንድ ሳይንሳዊ መላ ምት አለ።ወፏ ከየትም የመጣች ወይም አዲስ የተፈጠረች ሳትሆን የነበረች ናት ይባላል።የክረምት ወር አልፎ መስከረም ሲጠባ በሚወጣው ፀሐይ ቀለሟ ይቀየራል የሚል መላ ምት ይጠቀሳል።

የአደይ አበባ ነገር ግን አሁንም ምሥጢሩ አልተገለጸም።መለኮታዊ ምሥጢር ያለው ይመስላል።ቃልኪዳኑን ጠብቆ መስከረም ላይ ነው የሚያብብ።ሌሎች የሳር እና የተክል አይነቶች ዝናብና ውሃ ካገኙ ይበቅላሉ።በበጋ ወቅት በመስኖ ዳርቻ ይታያሉ።አደይ አበባ ግን ዓመቱን ሙሉ ዝናብ ቢሆን በበጋ ወቅት አይበቅልም፤ በየትኛውም የመስኖ ዳርቻ አደይ አበባ አይታይም።

በመስከረም ላይ የተሰሩ በርካታ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ናቸው ያሉት።ዘፈኖችንም ግጥሞችንም እንዘርዝር ቢባል ሙሉ ጋዜጣው አይበቃም።‹‹ደስ ይላል መስከረም›› በሚለው ደስ የሚል የባለቅኔ ሙሉጌታ ተስፋዬ ግጥም እንሰነባበት።ደስ የሚል መስከረም ይሁንላችሁ!

ደስ ይላል መስከረም
በግርሻ ጣይ ሰርዶ ነቅሎ በሚያዝያ ንሸ ተርበጥብጦ
በግንቦት ሐሩር ተቀቅሎ በፀሐይ አብስሎ በዝናብ አብቅሎ
ከወዳጅ ከዘመድ ተቀላቅሎ
ባዝራን ከአህያ አዳቅሎ
በባለ በርሸት ሽልም በቅሎ
ተፈናጦ አብሮ ገስግሶ
ጅራፍ ግርፊያ ሆያ ሆዬ ቡሄ በሉ ተጫውቶ
ኪዳነ ምሕረትን አንግሶ ደግሞ በወሩ ለአስተሮዬው
ግሼን ማሪያም እማአርያም ደጀሰላም ደርሶ ለመሳለም

**«እዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ**
**ዐደይ ስምስም ስኔ እንዳንቺ የለም...»**
**እያሉ ንጥቂያ**
**ከጀንበር መፍለቂያ እስከ ጀንበር መጥለቂያ**
**አሰሳ ነቅሉ ባሕር እንጉዳይ**
**ጀግና ሰው ገዳይ**
**አካል እንጉዳይ**
**እያሉ ሲያንጎራጉሩ!**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**ቡቃያው ጣል ከንበል ሲል**
**ሸሩባዋ ወርዶ እንዲያ ሲዘናፈል**
**ልቤ እንደበቀሉ ያድራል ሲፈለፈል**
**በቀጭን ተሰርታ ስትል ዘንከት ዘንከት**
**ጻሉ ሲል ሲያነጋ አገር በመለከት**
**ስመስቀል ጠንስሶ በማድጋ ገንቦ ለእንግዳ ቀንሶ**
**በሞቴ አፈር ስሆን እያስ ሲያጋፍር**
**ጥርስ እንጎቻ አስፍቶ አሞጭ በመሰሰው እርጎ ፍርፍር**

እንኳን ሳቅ ጨዋታው ድብድቡ ልፊያው
ድገሙኝ ያሰኛል ሰፊፍ የለሽ ሞገድ መደዶ ዘር
**ዜማ ሲቆረቆር ክትፊያው**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**የሸንብራ እሸት እየጠረጠሩ**
**የልጅነት ሚዜ €€ሽረ አይዋ ክንዴ« እያሉ እየጠሩ**
**አብሮ ወፍ ጥበቃ ማማ ሳይ ተሰቅሉ**
**ካፊያውን በገሳ በአንድ ተጠልሉ**
**እሳት አቀጣጥሉ በቆሉ ጠባብሶ**
**አየሁ አላየሁም... ሰማሁ አልሰማሁም**
**በሳልቶ አፍ አብሶ**
**ስስሶ አስፈትሉ የእናት ኩታ ለብሶ**
**ሳዋዊ ተልኮ ለልጅ ተጎናብሶ**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**እንደቢራ ቢሮ አበባ ለአበባ ዐደይ እንቡር እንቡር**
**በፍቅር ስመክረም**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**ወፉ ከነ ጎጆው እስከ መናጆው**
**ንቡ ከነ ቀፎው መረባ ከነ እርፎው**
**በዐደይ ስምስም ክብር ስመስከረም ክብር**
**ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ!**
**የዓመት አሥራት ሲያፈስ**
**ሲያስገባስት ግብር**
**በዝማሬ ሲያብር**
**አንጄት ሲበረብር**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**ተዋዶ ወዶ ተወሕዶ ያንጀት ተፈቃቅዶ**
**ባንድ አብሮ ስመክረም**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**ስቅኔ ዘረፋው ጠፈፍ ሲል ፈፋው**
**የቆሉ ተማሪ ያ ተመራማሪ**
**የወሳዲት አምላክ የድንግል አዝማሪ**
**ያ ደበሉ ለባሽ!**
**በእግዚትነ ማሪያም! እባካችሁ እባሽ እባካችሁ ቁራሽ**
**እያስ ሲለምን**
**ከጥንቅሹ ቅንጥሽ ማሩቴ ባይሰጠው**
**አይቀር መደንገጡ አራሽ አባ ወራሽ ማብላት ያሰስጠው**
**የማይስወጠው**
**በዓይኑ እየመዘነ በልቡ እማይመርጠው**
**ገሩ ባሳገሩ**
**ያ ባስሞፈሩ ያ ባስዘገሩ**
**በሞቴ ነው ቋንቋው ስሞት ነው ነገሩ**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**ወዶ ተወሕዶ ያንጀት ተፈቃቅዶ**
**አንድ ልብ አቅዶ**
**አንድ ሳይ ስመክረም**
**ደስ ይሳል መስከረም!**
**ጥቅምትና ኅዳር ቢያዋውል ምንጭ ዳር**
**ታኅሳስና ጥር ዐውድማ አስስቅልቆ ጥሪት እሚያስቋጥር**
**የካቲት መጋቢት መኸር አስከትቶ ቢያበስል እንደ ዐቃቢት**
**ሚያዚያና ግንቦቱ ተርቲበኛው ቀርቦ ወርዶ ረከቦቱ**
**የሳም ልጅ በዋንጫ ቢቀርብ ስልባቦቱ**
**ሰኔ ሐምሌ ነሐሴ እንደ ቄስ ምናሴ**
**እያረበረበ ደግሞ እየወረበ**
**ሰማይ በበረቀ ታርሶ ርሶ ሲስረቀረቅ**
**ከራሱ እስኪታረቅ**
**ሁሉም እንደ ግብሩ**
**ሁሉም እንደ ሙያው!**
**አሥራ ሁስቱም ወር**
**እዮሃ አበባዬ መስከረም ሲጠባ**
**ያኔ ነው ገቢያ**
**ያኔ ነው መታያው**
**ያኔ ነው ማባያው**
**ደስ ይሳል መስከረም!**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ሕይወት በማርያም ወንዝ ዳርቻ

**ሰላማዊት ውቤ**

ማርያም ወንዝ የተሰኘው ሥፍራ እንኳንስ የሰው ልጅ ሌላ ፍጡር ይኖርበታል ተብሎ አያታሰብም። የፅዳቱ መጓደል ቆሼን ጭምር ያስንቃል።በቆሻሻ የተዋጠውና የተበከለው ይሄ ወንዝ መነሻው ቁስቋም ማርያም ሽሮ ሜዳ አካባቢ በላይ ሲሆን ቀጨኔ መድኃኒዓለምን መዳረሻው አድርጎ ወደታች ይወርዳል።ቦታው የሚጠቃለለውና የሚጠራው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 23 ውስጥ ነው።

የወንዙ ውሃ በቆሻሻ ከመበከሉ የተነሳ የተቃጠለ የፍሬን ዘይት በመምሰል ወደ ጥቀርሻነት ተለውጧል።ሆኖም በዚህ አካባቢ የወንዙን መጥፎ ሽታ ተቋቁመው የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ።መኖራቸውን እንኳን ማንም በቅጡ የማያውቀው የህብረተሰብ ክፍሎች የአዲስ አበባ አንዱ ገመና ሆነው ዘመናትን ተሻግረዋል።

እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ኑሯቸውን የሚገፉት በልመና ነው።ኑሮዬ ብለው በወንዙ ዳር ዳር ሰፍረው ለሚኖሩትና በልመና ለሚተዳደሩት የኔ ቢጤዎች የማርያም ወንዝ ሁሉም ነገራቸው ነው።ጎህ ሳይቀድ በድቅድቅ ጨለማ ለልመና ከቤታቸው ሲወጡ የመጀመሪያ ስራቸው በወንዙ ውሃ ፊታቸውን ማበስ ነው።መጠኑ ከፍ በሚል ጊዜ በእጃቸው እየጨለፉ ፤ሲቀንስ ደግሞ በዙሪያው ባገኙት ነገር እየጠለቁ ዓይናቸውን አበስ አበስ ያደርጉበታል።በተለይ ዕጣ ፈንታቸው ነገር ዓለሙን ያስረሳቸው አንዳንድ አዋቂዎችና ህፃናት ሙሉ በሙሉ ፊታቸውንና እግራቸውን ይታጠቡበታል። አንዳንዶቹ እንደሚናገሩትም ቤት በሚውሉበት ጊዜ ለምግብ መሥሪያ ይጠቀሙበታል።

በወንዙ ዳርቻ የተደረደሩት ቤቶች በአሮጌና ቁርጥራጭ ላስቲክና ቆርቆሮዎች ተለጣጥፈው የተሰሩ ናቸው።አብዛኞቹ ቤቶች ከ10 እስከ 30 በመሆን የኔቢጤዎች በሕብረት ተጨናንቀው የሚኖሩባቸው ናቸው።ለቤቶቹም በወር ከ200 እስከ 500 ብር ይከፍላሉ። የኔ ቢጤዎቹ ሌሊት ወጥተው በልመና ከሚያገኙትን ገንዘብ ለዕለት ጉርሳቸውና ለቤት ኪራይ ያውሉታል።

የማርያም ወንዝ የኔ ቢጤዎች ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ከመኝታቸው ይነሳሉ።አንዱ ሌላውን የመቀስቀስ ኃላፊነትም አለበት።በዚህ ጊዜ በአካባቢው ጫጫታና ሁካታ ይበረታል ።ህጻናትና ታዳጊዎችም በብዛት አይነስውራንን ስለሚመሩ የሌሊቱ ትዕይንት አካል ናቸው።

በተለይ ሴቶች ደካማ እናቶችን፣ አካል ጉዳተኞችንና በክራንች ወይም በዱላ የሚሄዱትን ይደግፋሉ። ቤት የሚቀር የለም። እጅ እግር የሌላቸው ሁሉም ዓይነት የአካል ጉዳት ያለባቸው ቢቻል በሸክምና በእዝል ባይቻል በኪራይ ዊልቼር ለልመና ይወጣሉ። ጉዳተኞቹን መሸከምና ማዘሉም ለመንደራቸው ነዋሪዎች ሌላ በድርድር ዋጋ የሚቆረጥለት የገቢ ምንጭ ነው።

በተለይ ጉልበት ያላቸው ጎረምሶች ከልመናው ባሻገር እጅ እግር የሌላቸውን ጨምሮ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውን በማጓጓዝ ነው የቤት ኪራይ የሚከፍሉትና የዕለት ጉርሳቸውን የሚሸፍኑት።ከአምስት እስከ ሰላሳ የሚደርሱ የቤተሰብ አባላት እርስ በእርስ እየተዛዘሉ፣ እየተመራሩና እየተደጋገፉ ጨለማው ሳይገልጥ መንደራቸውን ለቅቀው ይወጣሉ።

‹‹እናት›› እያሉ በቁልምጫ የሚጠሯት 31 ቁጥር አውቶቡስን ጨምሮ የሽሮ ሜዳ መስመር አውቶቡስ ሹፌሮች ጨለማው ሳይገልጥ እያሳፈሯቸው ይከንፋሉ። በአራቱም የአዲስ አበባ ማዕዘናት ይሰማራሉ።ቦሌ ወደ ጉምሩክ፣ ካራማራ ሆቴል፣ ሩዋንዳ ማዞርያ፣ ሳሪስ አቦ ፣ መገናኛ፣ 22 ቹቹኒያ አካባቢ፣ መስቀል አደባባይ፣ መርካቶ የልመና መዳረሻ ሥፍራዎቻቸው ናቸው።

አቶ መርጋ ዲሳሳ በእንዲህ ዓይነቱ የልመና ሥራ ተሰማርተው ከሚገኙ የማሪያም ወንዝ መንደር ነዋሪዎች አንዱ ናቸው።አውቀውት ባይነግሩንም ዕድሜያቸው በግምት ወደ 75 ዓመት የሚጠጋ ይመስላል። ሁለት እጅ የላቸውም፤ እንደነገሩን እግር ቢኖራቸውም አይታዘዝላቸውም።

በብዛት ቦሌ አካባቢ ነው የሚለምኑት። መገናኛም ይቀመጣሉ። አልፎ አልፎ መርካቶ የሚወጡበት ጊዜም አለ። የንግስ በዓላት ቀንም በየአድባራቱ በመገኘት ምጽዋት ይጠይቃሉ። በእነዚህ አካባቢዎች በብዛት የሰው እንቅስቃሴ በመኖሩ ዳጎስ ያለ ገቢ ያገኛሉ፤ መጠኑን ባይገልፁትም ለሚሸከማቸው ሰው ከፍተኛ ገንዘብ ከፍለው፤ፈጣሪያቸውንም አመስግነው ወደ ማደርያቸው ማርያም ወንዝ ይመለሳሉ።‹‹እናት›› የሚሏት አውቶቡስ እንደወሰደቻቸው ወደ ማደርያቸው ትመልሳቸዋለች።

ሌላው የ67 ዓመቱ አዛውንትና ምስካየ ህዙናን መድኃኒዓለም አካባቢ ሲለምኑ ያገኘናቸው አቶ አዳነ ቢልልኝም የዚሁ መንደር ነዋሪ ናቸው። በሕክምና ሰበብ ከክፍለ ሀገር መጥተው ነው አዲስ አበባ ሰምጠው የቀሩት። ዘበኝነት ተቀጥረው በቅጡ 30 ዓመት ያልሞላት ልጃገረድ አግብተው የራሳቸው ጎጆ በመቀለስ ሁለት ልጆች ወልደው ይኖሩ ነበር።

ሆኖም ምስካየ ህዙናን መድኃኒዓለም አካባቢ አስፋልት



አቶ አዳነ ቢልልኝ



ወይዘሮ የሺሀረግ ወርቁ

መንገድ ሲያቋርጡ መኪና ገጫቸው። በአደጋው ታፋቸውና ትከሻቸው ክፉኛ ተጎዳ። ባለመኪናው የካቲት 12 ሆስፒታል ወስዶ ጥሏቸው ጠፋ።በቂ ህክምና ባለማግኘታቸውም መንቀሳቀስ ተሳናቸው፤ ለብዙ ጊዜም የአልጋ ቁራኛ ሆኑ። የዘበኝነቱን ሥራም በዚህ ምክንያት ተዉት። ልመናም መተዳደርያቸው ሆነ።

ልጆቻቸው ሴቷ 20 ዓመት ወንዱ ደግሞ ስምንት ዓመቱ ነው። በብዙ ትግል ዘንድሮ ትንሹን ልጃቸውን ቅድመ መደበኛ ትምህርት አስገብተውታል። ትልቋ ስምንተኛ ክፍል ከደረሰች በኋላ አቋርጣለች። ሰው ቤት ልብስ እያጠበችም ሆነ ጉሊት ቢጤ እየሰራች እራሷንና እነሱን ታስተዳድር ነበር። ሆኖም አሁን አእምሮዋ በመታወኩ ሥራውን ካቆመች ዓመታት አልፏታል። በዚህም ምክንያት ቤተሰቡ የሚተዳደረው አቶ አዳነ ለምነው በሚያመጡት ገንዘብ ነው። ከዚሁም ላይ ሌሊት ወጥተው ማታ ለሚገቡባት የላስቲክ ጎጆ 300 ብር ይከፍላሉ።


ሌላዋ የማርያም ወንዝ ነዋሪ ወይዘሮ የሺሀረግ ወርቁ ናቸው።ወይዘሮ የሺሀረግ እንዳወጉን ከደራ ተፈናቅለው ከመጡና በአካባቢው መኖር ከጀመሩ ዘንድሮ ሁለተኛ ዓመታቸውን ይዘዋል። ሦስት ልጆች የነበሯቸው ቢሆንም የየራሳቸውን እንጀራ ፍለጋ በየአቅጣጫው በመበተናቸው ብቻቸውን ነው የሚኖሩት። ሆኖም ብቻቸውን እንደሚኖሩ ይግለፁ እንጂ በጠባቧና በደካማዋ የላስቲክ ቤት ወለል ላይ የሚያድሩት አምስትና ስድስት ሆነው በሕብረት ነው። በግላቸው በወር የሚደርስባቸው ኪራይም 500 ብር ነው።

በዕለቱ ምስካየ ህዙናን መድኃኒዓለም ደጃፍ እናግኛቸው እንጂ ይሄን ለመክፈልና የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ይለምናሉ። ምክንያታቸው ደግሞ ሀገራቸው ሳሉ ወድቀው እጃቸው ስለተሰበረ የራሳቸውን ልብስ ማጠብ እንኳን አለመቻላቸው ነው።

በአጠቃላይ የማርያም መንደር ነዋሪዎቹም ሆኑ ከዚያ እየተነሱ በአዲስ አበባ በሁሉም አቅጣጫ ለልመና የሚሰማሩ ዜጎች የመንግስትንም ሆነ የሌሎች ግብረሰናይ ድርጅቶችን ትኩረት ይሻሉ።

በሴቶችና ህፃናት ማህበራዊ ቢሮ የማህበራዊ ጥበቃ ማስተባበሪያና መከታተያ ዳይሬክተር አቶ መሀመድ ከማል እንደሚሉትም ችግሩን ለመፍታት በጀት ተመድቦለት የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት የሚል ፕሮጀክት ተቀርጿል። ከመጪው ጥቅምት ጀምሮም በይፋ ስራ ይጀምራል። ሆኖም በአካባቢውም ሆነ በከተማዋ ባለሀብቶች ከክፍለ ሀገር እያመጡ የሚለምኑባቸውና ሌሎችም ልመናን ባህል ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች መኖራቸው ስለተረጋገጠ እነዚህ ተለይተውና የሕግ ማዕቀፍ ወጥቶ እንደሚተገበር ነግረውናል።

# ዓለም አቀፍ



## ኢራን የኒውክሌር ስምምነት ላይ ለመድረስ የኤጀንሲውን መተማመኛ እንደምትፈልግ አስታወቀች

ኢራን የኒውክሌር ስምምነት ላይ ለመድረስ ከዓለም አቀፉ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ መተማመኛ እንደምትፈልግ አስታወቀች።የኢራን ፕሬዝዳንት ኢብራሂም ራይሲ እና የፈረንሳይ አቻቸው ኢማኑኤል ማክሮን በኒውዮርክ እየተካሄደ ከሚገኘው የመንግስታቱ ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ጎን ለጎን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መክረዋል።

ፕሬዝዳንት ኢብራሂም ራይሲ÷ ኢራን ተዓማኒ፣ አካታች እና ዘላቂ የኒውክሌር ስምምነት ላይ ለመድረስ ቁርጠኛ አቋም እንዳላት አብራርተዋል።ይሁን እንጂ ዓለም አቀፉ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ዘላቂ የኒውክሌር ስምምነት ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑን መግለጻቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

የኢራን ፕሬዝዳንት ኢብራሂም ራይሲ የኒውክሌር ስምምነት ላይ ለመድረስ አሜሪካ የጣለቻቸውን ማዕቀቦች ማንሳት እንዳለባት ማስታወቃቸው ይታወሳል።ፕሬዝዳንቱ ኢራን የኒውክሌር ጦር መሳሪያ መርሐ ግብሯን በዘላቂነት ለማስወገድ ከአሜሪካ በኩል አስተማማኝ ዋስትና ልታገኝ ይገባል ብለዋል።

ከአሜሪካ ጋር ፊት ለፊት ለመነጋገር ጊዜው ገና እንዳልሆነ ጠቅሰው ከቴህራን ጋር ስምምነት ላይ ለመድረስ በፈለገችው ዋሺንግተን ቅንነት ላይ ጥርጣሬ እንዳለቸውም ከዚህ በፊት አስታውቀዋል።

ማዕቀቦችን ማንሳት የመፍትሄ አካል መሆን አለበት ያሉት ፕሬዝዳንቱ÷ ጉዳዩን በጥንቃቄ ለመቋጨትም በኢራን ላይ የሚነሱ ፖለቲካዊ እና መሠረተ ቢስ ውንጀላዎች ሊቆሙ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።ዋስትናዎችን በተመለከተ የተጣሉ ማዕቀቦችን በዘላቂነት ማንሳት እንጂ ጊዜያዊ እርምጃ እንደማይፈልጉ ጠቅሰዋል።

ለጉዳዩ አስተማማኝና ዘላቂ መፍትሄ ከተገኘ በእርግጠኝነት ስምምነት ላይ መድረስ ይቻላል ማለታቸውን አልጀዚራ መዘገቡ ይታወሳል።



## ፕሬዝዳንት ፑቲን በሩሲያ«ከፊል ወታደራዊ ጥሪ» እንዲደረግ አዘዙ

ሩሲያ “ከፊል ወታደራዊ ጥሪ ” እንድታደርግ ማዘዛቸውን ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን አስታወቁ።ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን ትናንት እንዳስታወቁት፤ ወታደራዊ ጥሪው ወታደራዊ ልምድ ያላቸው እና በተጠባባቂነት የሚገኙ ሃይሎች የሩሲያን ጦር እንዲቀላቀሉ የሚያደርግ ነው።

ወታደራዊ ጥሪው የሀገሪቱ መከላከያ ሚኒስቴር ሩዚያ ከዩክሬን ጋር ላለባት የተራዘመ ጦርነት ተጠባባቂ ሀይሎችን በሰራዊቱ ዕዝ ውስጥ ለማስገባት መወሰኑን ተከትሎ የመጣ መሆኑን ገልፀዋል።ከሁኔታዎች አንፃር ወሳኔው ትክክል ነው ያሉት ፕሬዝዳንቱ ወታደራዊ ቅስቀሳው በፍጥነት እንዲጀመር ትዕዛዝ መስጠታቸውንም አብራርተዋል።

የመከላከያ ሚኒስትሩ ሰርጌ ሾይጉ እንዳስታወቁትም ለዩክሬን ጦርነት 300 ሺህ የተጠባባቂ ሀይሎች ጥሪ የማድረግ ፍላጎት መኖሩን ተናግረዋል።

ጥሪ የሚደረግላቸው ዜጎችም ተጨማሪ ስልጠናዎችን እንደሚወስዱና በወታደራዊ ግዳጅ ላይ ያለው ሰራዊት የሚያገኘውን ጥቅማ ጥቅም እንደሚያገኙም ጠቁመዋል።

ጥሪው በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንደማይተገበር እና የውትድርና ልምድ ያላቸው ሩሲያውያን ብቻ ጥሪ እንደሚደረግላቸው መናገራቸውን አር ቲ ዘግቧል።

በሩሲያና በዩክሬን መካከል ያለው ግጭት አሁንም እንደቀጠለ ሲሆን ሩሲያ ይህን ጥሪ የምታደርገው ጦሯን ይበልጥ ለማጠናከር መሆኑን ወታደራዊ ባሉሙያዎች ይናገራሉ።ሩሲያ ከስምንት ዓመት በፊት ቁጥጥር ስር የገባችው ክራይሚያ እንዲሁም ፑቲን እያካሄዱት ያለው ወታደራዊ ዘመቻ የዶምባስ ክልልን “ነጻ ማውጣት” መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልጹ ቆይተዋል። የሉሀንስክ እና የዶምባስ አካባቢዎች በሩሲያ በሚደገፉ ኃይሎች ቁጥጥር ስር ይገኛሉ።በዚህ ምክንያትም በሁለቱ አገራት መካከል ያለው ግጭት እንደቀጠለ ነው።

# ስፖርት



## የፕሪሚየር ሊጉ አክሲዮን ማህበር አዲስ ደንብ እያዘጋጀ ነው

**ቦጋለ አበበ**

የ2014 ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ በተለያዩ ከተሞች ሲካሄድ እስከ መጨረሻ ያስተናገደው ጠንካራ ፉክክር በበጎ ጎን የሚነሳ ነው። ይሁን እንጂ በውድድሩ ቻምፒዮን የሚሆነውንና ከሊጉ የሚወርደውን ክለብ ለመለየት በነበሩ የመጨረሻ ሳምንት ጨዋታዎች ክለቦች እጅግ ተቀራራቢ ነጥብ መያዛቸውን ተከትሎ ውዝግቦች መፈጠራቸው አልቀረም። ከጨዋታ መላቀቅ ጋር በተያያዘ ውዝግቦች እንዳይፈጠሩ የመጨረሻ ሳምንት ጨዋታዎች በተመሳሳይ ሰአት እንዲካሄዱ ቢደረግም ችግሮች መፈጠራቸው ይታወሳል። በዚህም በደል ተፈጽሞብናል ያሉ ክለቦች አቤቱታቸውን ቢያቀርቡም ያገኙት መፍትሄ የለም። በቀጣይ ግን ተመሳሳይ ችግሮች ሲገጥሙ በህጋዊ አግባብ ለመፍታትና ለመቆጣጠር እንዲቻል የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማህበር አዲስ የውድድር ደንብ አዘጋጅቶ እየተወያየበት እንደሚገኝ ጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክሲዮን ማኅበር 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ባለፈው ሰኞ በሀያት ሪጀንሲ ሆቴል ባደረገበት ወቅት እንደተገለጸው አዲስ እየተዘጋጀ የሚገኘው የውድድር ደንብ ውይይት ተደርጎበት በቅርቡ ይጸድቃል።

የቤትኪንግ ኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዮሐንስ ጥላሁን በክብር እንግድነት በታደሙበት በዚህ መድረክ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክሲዮን ማኅበር የቦርድ ሰብሳቢ መቶ አለቃ ፍቃደ ማሞ በ2015 ሊሰሩ ስለታሰቡ ጉዳዮች ዙርያ ማብራሪያ ሰጥተዋል።



**የኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ አክሲዮን ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ መቶ አለቃ ፍቃደ ማሞ፣**

በ2014 የውድድር ዘመን በአነስተኛና በከፍተኛ ሁኔታ ችግሮች አጋጥመው እንደነበር ያስታወሱት መቶ አለቃ ፍቃደ፣ ከነዚህም መካከል በዳኝነት በኩል የሚፈጠሩ ስህተቶች ቅፅበታዊ እና ከዳኛው ችሎታ ጋር የሚገናኝ በመሆኑ በቅን ልቦና የተፈፀሙ ስህተቶች ይሆናሉ ተብሎ እንደታመነባቸው አንስተዋል። እንደ መቶ አለቃ ፍቃደ አገላለጽ፣ አንዳንድ ስህተቶች በፍፁም ሆን ተብሎ የተፈፀሙ ናቸው። አክሲዮን ማህበሩ እነዚህ ነገሮች ዘንድሮ እንዳይደገሙ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በትኩረት ከሚነጋገርባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። “ሌላው የገጠመን ፈተና የውድድሩን አሸናፊ አንገት ለአንገት የተናነቁበት እና ወራጆቹም እስከ መጨረሻው ድረስ ያልታወቁበት የውድድር ዘመን ነበር። የመጨረሻ ሳምንት ጨዋታዎችን በተለያዩ ሜዳዎች በእኩል ሰዓት እንዲካሄዱ ተደርጓል። ያም ቢሆን አንዱ ለቆብኛል፣ ተንኮል ተሰርቶብኛል እና ያለ አግባብ ድርጊት ተፈፅሞብኛል የሚል ክስ ቀርቦልናል። ያደረግነው የጨዋታው ኮሚሽነር እና ዳኞች ጠርተን አነጋግረናል። በቀረበው ክስ መሠረት ተፈፀመ የተባለውን ነገር የሚያሳይ ማስረጃ ባናገኝም ለወደፊቱ እንዲህ ያሉ ነገሮች ሲያጋጥሙን በውድድር ደንባችን ይህንን መቆጣጠር የሚያስችል አዲስ ደንብ ተዘጋጅቷል ተወያይተንበት የሚፀድቅ ይሆናል” ሲሉ መቶ አለቃ ፍቃደ ተናግረዋል።

የቦርድ ሰብሳቢው በጠቅላላ ጉባኤው ሌሎች ጉዳዮችን በማንሳትም ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን፣ የተጫዋች ኤጀንቶች (ደላሎች) ትኩረታቸው የአገራችን ተጫዋቾች ላይ ማድረጋቸውን ጠቁመዋል። ለደቡብ አፍሪካው ትልቅ ክለብ ማሚሎዲ ሰንዳውንስ እየተጫወተ የሚገኘው አበቡበከር ናስር የዚህ ውጤት መሆኑን እና በቀጣይም በርከት ያሉ ተጫዋቾች ይህን እድል እንደሚያገኙም አብራርተዋል። የአክሲዮን ማህበሩም በዚህ ሀሳብ መሠረት በንብረት ረገድ ሀሴት እያፈራ መምጣቱንና የራሱ ንብረቶችን እያገኘ እንደሚገኝ ተጠቁሟል።

“የሊጉ አክሲዮን ራሳችንን ከሱፐር ስፖርት ጋር ሰፊ ገምግመናል፣ በግምገማችን ከኮቪድ ወረርሽኝ በኋላ ተመልካቾች ወደ ሜዳ እንዲገቡ ቢፈቅድም ውድድሮቹ የሚካካሄዱበት መንገድ በሜዳ እና ከሜዳ ውጭ በሚለው ከማድረግ ይልቅ በተመረጡ አምስት ከተሞች ማድረጉን መልካም መሆኑን ተስማምተናል። በዚህም መሠረት ዘንድሮ በአምስት በተመረጡ ከተሞች ውድድሮቻችንን እናካሂዳለን” ያሉት የቦርዱ ሰብሳቢ በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭቱ ወቅት የሚታየው ሎጎ (አንድ ሰው ኳስ ሲመታ የሚያሳየው) እና የመግቢያ ሙዚቃው እንዲቀየር ሰፊ ክርክር እና ውይይት በማድረግ እንዲቀየር መወሰኑን አስረድተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን ለአሰልጣኞች፣ ለዳኞች፣ ሚዲያ አካላት እና ለክለብ አመራሮች እንደተሰጡ ተገልጿል። በዚህም ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ተደርጓል። ሆኖም ግን በክለብ አመራሮች ስልጠና የሚላኩ ሰዎች ከሌላ የስራ ዘርፍ የሚመጡ መሆናቸው ለስልጠናው የማይመጥኑ በመሆናቸው በቀጣይ ትክክለኛ ተወካይ የማይመጣ ከሆነ ተቀባይነት እንደማይኖረው ታውቋል።

የዘንድሮ ውድድር በባህር ዳር፣ ድሬዳዋ፣ አዳማ እና በመጨረሻም አዲስ አበባ እንደሚደረግ የተጠቆመ ሲሆን፣ ሀዋሳን በተመለከተም ዓመቱን ሙሉ ሜዳውን እንዲያስተካክሉ በተደጋጋሚ እንደተነገራቸውና ኮሚቴም ሄዶ እንደተነጋገረ ተገልጿል። እነርሱም ሜዳውን እንደሚያስተካክሉ የገለጹ ሲሆን፣ ሜዳው ከተሰራና ካለቀ በኋላ አክሲዮን ማህበሩ ወደ ሐዋሳ ሊሄድ እንደሚችል ማብራሪያ ተሰጥቷል። ሆኖም የዚህ ዓመት ውድድር መዝጊያ አዲስ አበባ እንደሚሆን ታውቋል። ከዚህ ቀደም አንድ ሜዳን ለመምረጥ መመዘኛው ሆቴል፣ ጥሩ መጫወቻ ሜዳ እና ፀጥታ ነበር። አሁን ግን ተመልካች በአግባቡ መገኘት ስለሚገባው አንዱ መለኪያ የተመልካች ብዛት ሆኗል። ስለዚህ ውድድሩ የሚካሄድባቸው ከተሞች ተመልካች ወደ ስታዲየም እንዲመጣ ከፍተኛ ቅስቀሳ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተነግሯል። ውድድሩ እየተካሄደ ተመልካች የሌለው ከሆነ ውድድሩን አቋርጦ ተመልካች ወደሚገኝባቸው ከተሞች ሊኬድ እንደሚችልም መቶ አለቃ ፍቃደ አሳስበዋል።

አክሲዮን ማህበሩ በ2015 ለመስራት ካሰባቸው ተግባራት ውስጥ 160 ጨዋታዎችን በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ማስተላለፍ አንዱ ነው። ሆኖም ብዙ ክርክር አስነስቷል። በቀጣይ ብዙ ውይይት የሚያስፈልገው በመሆኑ ከውድድሩ ጅማሮ አስቀድሞ የቀጥታ ስርጭት ሽፋን የሚያገኙ የጨዋታ ብዛቶች ወደ ፊት የሚታወቁ ይሆናል። ሌላው ገቢ ለማግኘት በስታዲየሞቹ ማስታወቂያ ለመስራት ዲጅታል የማስታወቂያ ሰሌዳ ወደ አገራችን ለማምጣት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ የተጠቀሰ ሲሆን ይሄም ይሳካል ተብሎ ታምኖበታል። በቪዲዮ የታገዘ ዳኝነትን (ቫርን) በዚህ ዓመት ተግባራዊ ለማድረግ ጨረታ ወጥቶ ነበረ ሲሆን ሁለት ድርጅቶችም ተወዳድረው ነበር። ሆኖም ግን ከወጪ አንፃር እንዲሁም ከተገኘው ምክረ ሀሳብ በመነሳት ጫናው ከባድ በመሆኑ በዚህ ዓመት ለጊዜው እንደቆመ ተነግሯል።


## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር 02/2015

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ባለስልጣን በክልለ ውስጥ በሚገኙ ሦስት ዞኖች ለመተከል ዞን፣ አሶሳ ዞን እና ካማሽ ዞን ውስጥ በመንገድ ከፈታ እና በመንገድ ጥገና ሥራ ላይ ለማሰማራት ዶዘር ብዛት 01፣ ግሬደር ብዛት 02 ፣ ሩሎ ብዛት 04 ሎደር ብዛት 02 ፣ የውሃ ቦቴ ብዛት 02፣ ገልባጭ መኪና ብዛት 06 ፣ ትንሽ መኪና ዳብል ጋቤና ብዛት 04 በግልጽ ጨረታ ለመከራየት ይፈልጋል፡፡ አንዱን ዶዘር በሰዓት ሂሳብ ለ1000.00 (አንድ ሺህ ሰዓት) ፣አንዱን ግሬደር በሰዓት ሂሳብ ለ1000.00 (አንድ ሺህ በሰዓት)፣ አንዱን ሎደር በሰዓት ሂሳብ ለ1000.00 (አንድ ሺህ ሰዓት)፣ አንዱን ሩሎ በሰዓት ሂሳብ ለ1000.00 (አንድ ሺህ በሰዓት) ፣ አንዱን የውሃ ቦቴ በቀን ሂሳብ ለ160 ቀናት፣ አንዱን ገልባጭ መኪና በቀን ሂሳብ ለ160 ቀናት፣ አንዱን የትንሽ መኪና ዳብል ጋቤና በቀን ሂሳብ 160 ቀናት አወዳድሮ ለመከራየት ይፈልጋል፡፡

በዚህም መሰረት :-

በመስኩ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው በ2015 በጀት ዓመት ያሳደሱ እና የዘመኑን ግብር የከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላችሁ እንዲሁም በአቅራቢነት የተመዘገባችሁ መሆናችሁ ማስረጃ ማቅረብ የሚችለ መሆን አለባቸው፡፡

1. በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና የተመዘገቡበትን ድረ ገጽ መግለጽ የሚችሉ ፤
2. የሚያከራዩን መሳሪያዎች የራሳቸው ለመሆኑ የባለቤትንት ማረጋገጫ ሊብሬ ማቅረብ የሚችሉ ወይም አግባብ ባለው ሙሉ የህግ ውክልና ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. የድርጅታቸውን (የቢሮቸውን) አድራሻ ማሳየት የሚችሉ ሆነው የጨረታን ዝርዝር የያዘ ሰነድ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመከፈል አስፈላጊውን ማስረጃ ከታደሰ ንግድ ፈቃድ ጋር በማድረግ አሶሳ በሚገኘው መንገድና ትራንስፖርት ባለስልጣን የግዥና ንብ /አስ/ዳሬክተር ቢሮ ቁጥር 10 በመቅረብ መውስድ ይችላሉ፡፡
4. ጨረታው ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ ለ15 ቀናት (አስራ ምስት ቀናት) በአየር ላይ የሚውል ሲሆን በ16ኛው (አስራ ስድስተኛ ቀን) ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ታሽጉ በዚሁ ቀን 8:30 ላይ ተጫራቾች ወይንም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ቀኑ የሥራ ቀne ካልሆነ ወይም ህዝባዊ በዓላቶች እንዲሁም ቅዳሜ ወይም እሁድ ከሆነ በቀጣዩ የሥራ ቀን እንዲከፈት ይደረጋል ፡፡
5. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በሰም በታሸ ኢንቨሎፕ በማድረግ አሶሳ በሚው መንገድና ትራንስፖርት ባለስልጣን የግዥና ንብ አስ ዳ ዳሬክተር ቢሮ ቁጥር 10 ውስጥ ተዘጋጅቶ ገተቀመጠው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ለመግዛት ሲመጡ የሚያከራዩትን ማሽን የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ኮፒውን እና የውክልና ደብዳቤ ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡
7. የጨረታው ሰነድ በሚገዙበት ወቅት የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) አሳይተው ካስመዘገቡት ማሽን ውጭ ጨረታ አንድ ዋጋ ሞልተው ቢያቀርቡ ተቀባይነት የለውም፡፡
8. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ በተመለከተ ለአንዱ ዶዘር ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/፤ ለአንዱ ግሬደር ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ ፤ ለአንዱ ሎደር ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ ፤ ለአንዱ ሩሎ ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር ፣ ለአንዱ ዉሃ ቦቴ ብር 20,000.00 / ሃያ ሺህ ብር ፣ ለአንዱ ገልባጭ መኪና ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር፣ ለአንዱ ትንሽ መኪና ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር በባንክ በተረጋገጠ CPO ብቻ በፖስታ በማሸግ ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ከባንክ ከተረጋገጠ CPO ውጭ የሚቀርብ የጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. መ/ቤታችን የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙለ ሆነ በከፊል የመሰረዝ ሙብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**የስልክ ቁጥር 0577752622**

## የቤ/ጉ/ክ/መ/የመንገድና ትናንስፖር ባለስልጣን